# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲዊ አንድነት መድረክ (መድረክ)

## መለስተኛ ፕሮግራም

ሰኔ 7 ቀን 2001 ዓ.ም

## መውጫ


i. <u>መግቢያ</u>

ii. <u>አጠቃላይ መርሆዎችና  አቋሞች</u>

Iii. <u>ክፍል አንድ፡- ፖለቲካዊ ጉዳዮች</u>

1. <u>ሰብዓዊ መብቶችን ስለማስከበር</u>
2. የእምነት ነፃነት
3. <u>ዴሞክራስያዊ መብቶች በተመለከተ</u>

ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት

የመደራጀት መብት

የመሰብሰብና ሰልፍ የማድረግ መብት

የመምረጥና የመመረጥ መብት

4. የሕግ የበላይነት እና የዳኝነት ነፃነት
5. የኢትዮጵያ አንድነት እና ሉኣላዊነት በሚመለከት
6. የብሄር፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች መብት በሚመለክት
7. የኢትዮጵያ መንግስት አወቃቀር
8. የሃገር መከላከያ ሰራዊትን በሚመለከት
9. የኢሚግሬሽን እና ድህንነት ባለስልጣንን በተመለከተ
10. ፖሊስን በተመለከተ
11. የውጭ ግንኙነት እና የአከባብያዊ ሰላም በተመለከተ
    11.1. ሚኒስቴር መስርያ ቤቱን እና አጠቃላይ ግንኙነታችንን በሚመለከት
    11.2. ከጎረቤት ሃገሮች ጋር ያሉትን የድንበር ጉዳዮች በሚመለከት

11.3. የባህር በርን በተመለከት

11.4 የወሰን ተሻጋሪ ወንዞችን በሚመለከት

Ìv፡ ክፍል ሁለት፡ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች

12. አጠቃላይ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችን በተመለከተ

12.1 የተመጣጠነ (balanced) የኢኮኖሚ ልማት ፖሊሲን መከተል፣

12.2 መንግሥት በልማት የሚኖረው ሚና በተመለከተ

12.3 የኢኮኖሚው ቀውስና መፍትሔዎቹ በተመለከተ

12.4 የባህር በር ባለቤት ባለመሆናችን በኢኮኖሚያዊ ልማታችን ላይ የሚያደርሰውን ተጽኖ መቋቋም

12.5 የበረሃነት መስፋፋት፣ የተፈጥሮ ሃብት መከላትና የአካባቢ ብክላን መከላከል በተመለከተ

13. የመሬት ጥያቄን በተመለከተ

14. በውጭ አገር ስለሚኖሩ ዜጎቻችን የልማት ተሳትፎ

vi፡ የሴክተር ፖሊሲዎች

15. የግብርና ልማት

15.1 አጠቃላይ የግብርና ልማት

15.2 ዘመናዊ እርሻዎችን ማስፋፋት

15.3 የደን ሀብት ልማት

16. ኢንዱስትሪ

17. ንግድን በተመለከተ

18. የከተማ ልማትን በተመለከተ

19. የውኃ ልማት

20. ኢነርጂ፡-

21. ማዕድን፡-

22. አገልግሎት ሰጭ ሰክተሮችን በሚመለከት፡-

22.1 ቴሌኮሙኒከሽን፡-

22.2 የፖስታ አገልግሎት

22.3 የትራንስፓርት አገልግሎት፡-

22.4 የፋይናንስ አገልግሎት፡-

23. ሠፈራ፡-

## vii፡ ክፍል ሦስት፣ ማሕበራዊ ጉዳዮች

24. ሥራ አጥነት

25. ድህነት ቅነሳ

26. የሰው ሀይል ፍልሰትና ስደት

27. ትምህርት

28. የጤና አገልግሎት

29. ማሕበራዊ ዋስትና

30. ሴቶችን በተመለከተ

31. ወጣቶችን በተመለከተ

32. አካል ጉዳተኞችን በተመለከተ

33. አረጋውያንና ህጻናትን በተመለከተ

34. ስነ ሕዝብን በተመለከተ

35. ቅርሶችና ብሄራዊ ፓርኮችን በተመለከተ

ì. **መግቢያ**

ባለንበት ዘመን ሰብአዊ መብት፣ የቡድን መብት፣ ነፃ የሃሳብና የመረጃ ልውውጥ፣ መድብለ ፓርቲያዊ ስርዓት፣ ነፃና ፍትሀዊ ምርጫ፣ ነፃ እና ገለልተኛ ዳኝነት፣ ወዘተ. የሚባሉት እሴቶች አብዛኛው የዓለማችን ሕብረተሰብ የሚያጣጥማቸው እና የሚቆምላቸው የመላ የሰው ልጆች እሴቶች እየሆኑ ነው፡፡ ድንበር የማይገድባቸው፣ ጉልበት የማይገታቸውና የሁሉም የሰው ልጅ እሴቶች መሆናቸውን በመገንዘብም፤ እነዚህ ነፃነቶች እና እሴቶች በሁሉም ዘንድ ይከበሩ እና ጥበቃ ያገኙ ዘንድ ዓለም አቀፉ ማሕበረሰብ ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እና መርሆዎችን ደንግጓል፤ አጽድቋል፡፡ ተግባራዊ መሆናቸውን የሚከታተሉ አለምአቀፍ ተቋማትንም አቋቁሟል፡፡ ሌላ ቀርቶ እነዚህን ነፃነቶች የሚጋፉትን ለመፋረድ የሚችል ዓለምአቀፍ ፍርድ ቤት ሰይሟል፡፡

የዘመኑ አምባገነኖች ከሚፈጽሙት የሰብአዊ እና ዴሞክራስያዊ መብቶች ጥሰት በተያያዘ ከአለም አቀፉ ማሕበረሰብ የሚመጣባቸውን ወቀሳና ትችት ለማጣጣል እየተጠቀሙበት ያለ ስልት "በሃገራችን ውስጣዊ ጉዳይ ጣልቃ አትግቡብን" እያሉ ሉአላዊነትን እንደመደበቅያ ዋሻ መጠቀምን ነው፡፡ ይህን ሲሉ ሊገነዘቡት ያልቻሉ አንድ እውነታ እንዳለ ግን ልንነግራቸው እንወዳለን፡፡ የገዛ ሃገሩን ዜጎች ነፃነትን እንደጦር የሚፈራና ለገዛ ሃገሩ ዜጎች በራስ ስለራስ የመወሰን መብት የማይቆም መንግስት ለሃገር ነፃነት እና ሉአላዊነት የሚታመን ሊሆን የሚቻለው አይደለም፡፡ ይህንን ለማስረዳት ምሳሌ ፍለጋ ሩቅ መሄድ አያስፈልገንም፤ በሰብአዊ መብት ጥሰት ሲከሰስ ሉአላዊነቴ ተደፈረ የሚለው የኢህአዴግ መንግስት የአገራችንን ሉአላዊነት ሲያስከብር አልታየም፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝቦች ያጋጠሟቸውን የተለያዩ የመብት ጥሰቶች ለመቀየር ብዙ መስዋእትነት ያስከፈለ ትግል አካሂደዋል፡፡ ሌላው ቀርቶ ከሰላሳ አምስት ዓመት በፊት ባካሄዱት ትግል ዘውዳዊው አገዛዝ የተገረሰሰበትን ሁኔታ ቢፈጥሩም የተፈጠረውን ምቹ ሁኔታ ተጠቅመው ስልጣን የያዙት ወታደራዊ መኮንኖች ለሰብአዊ መብት ጥበቃ፣ ለዴሞክራስያዊ መብቶች መከበር እና ለብሄር ብሄረሰቦች መብት መከበር የተደረገውን ትግል በመደፍጠጥ ሕዝቡን ተመልሰው ለከፋ ሥቃይና አፈና ዳርገውታል፡፡ የፖለቲካ ልዩነት ወንጀል ሆኖ ለቀይ ሽብር የተዳረገበት፤ የሰው ህይወት ዋጋና ክብር ያጣበት የደርግ ዘመን ዘግናኝ ታሪካችን አሁንም ድረስ ከዜጎች ህሊና ያልጠፋ ትዝታ ነው፡፡ ይህም ሆኖ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በነበረው አፈናና ወከባ ተደናግጠው ትግላቸውን አላቋረጡም፤ ይልቁንስ ትግላቸውን ይበልጥ በማጠናከር የደርግን ሃይል ማንኮታኮት ችለዋል፡፡ በደርግ ዘመን የተፈጸመው ሌላው የማይረሳው የታሪካችን ገፅታ ደግሞ በተቃዋሚ ድርጅቶች መካከል መቻቻልና መግባባት ጠፍቶ እርስ በእረሳቸው ያደረጉት ሽኩቻና ደም መፋሰስ ነው፡፡

በደርግ እግር የተተካው ኢህአዴግ ከደርግ በተለየ ሰብአዊ መብትን፤ የብሄር ብሄረሰብ መብትን ጨምሮ ሁሉም ዴሞክራስያዊ መብቶች፤ ስልጣን በነጻ ምርጫ እና ውድድር ብቻ የሚያዝበት መድብለ ፓርቲያዊ ስርዓት፤ በፌዴራሉ እና በክልል መንግስታት መካከል ግልጽ የስልጣን ክፍፍል ያለበት የፌዴራል ስርዓት፤ በሕግ አውጪው፣ በሕግ አስፈፃሚው እና በሕግ ተርጓሚው አካላት መካከል አንዱ ሌላውን የሚቆጣጠርበት ግልፅ የስልጣን ክፍፍል ያለበት ሕገ መንግስታዊ ስርዓት፤ ወዘተ እውን አደረጋለሁ ብሎ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቃል ቢገባም፣ በሕዝብ ልጆች ከፍተኛ መሥዋዕትነት ለስልጣን የበቁት የኢህአዴግ መሪዎች ብዙም ሳይቆዩ ላይመለስ ተቀብሮአል የተባለለትን አፋኝ አገዛዝ መልሰው በሕዝቡ ላይ ጭነውበታል፡፡

ኢህአዴግ የኢትዮጵያ ሕዝቦችን ከደርግ የአንድ ርእዮት እና የአንድ ፓርቲ የበላይነት አላቅቃለሁ እንዳላለ ይዞት የመጣው «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» የተሰኘው መስመር ግን ሌሎች አማራጭ አስተሳሰቦችን በጠላትነት የሚፈርጅ፤ በመድብለ ፓርቲ ስርዓት ፈንታ የአንድን ፓርቲ አምባገነንነት የሚያነግስ፤ በፌዴራላዊ ሕገ መንግስታዊ ስርዓት ፈንታ «ሁሉም አንድ ድምጽ ይስጥ፣ አንድ ቃል ብቻ ይናገር» የሚል ዴሞክራስያዊ ማእከላዊነት በሚባለው መርሕ ዲሞክራሲን ሸብቦ ማእከልነትን ብቻ የሚያነግስ ስርዓት አስፍኗል።

በመሆኑም በሃገራችን ዛሬም እንደቀድሞው የዜጎች ሰብአዊ እና ዴሞክራስያዊ መብቶች እየተረገጡ ናቸው፣ የሕግ የበላይነት እና ነፃና ገለልተኛ የፍትህ ስርዓት የለም፣ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ደብዛው እየጠፋ ነው። ሃሳብን በነጻ መግለጽ ከመታቀቡም ባሻገር የፖለቲካ ፓርቲ አደራጅቶ መታገል ለከፋ እንግልት የሚዳርግ ተግባር ሆኗል። ለዘመናት ሳይፈታ የኖረው የብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ጥያቄ ዛሬም መፍትሔ ሳያገኝ በመቅረቱ ጥያቄው ሃገራችንን የባሰ ውስብስብ ችግር ውስጥ እንዳይከታት የሚያሳስብበት ደረጃ ላይ ደርሷል። ስለሆነም በአብዛኛው የሃገራችን ክልሎች አዋሳኝ አካባቢዎች በሚኖሩ ሕዝቦቻችን መሃከል  ግጭቶች እየተከሰቱ፣ በሰው ሕይወትና ንብረት ላይ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ ይገኛል። የዜጎች በፈቀዱት አካባቢ ሠርቶ የመኖርን፣ የልማት ተግባር የማከናወን፣ መብት አለመከበር እና የስራ ዋስትና ያለመኖር በህዝቦች መካከል ሊኖር የሚገባውን መቀራረብ እያደፈረሰው እና የህዝቡንም የሃገሩንና የአካባቢውን ባለቤትነት መንፈስ እያደከመው መሄዱ  በራሱ የስጋት ምንጭ እየሆነ ይገኛል። በአጠቃላይ የኢህአዴግ አገዛዝ ሃገራችንን አስጊ የሆነ ሁኔታ ውስጥ ከቷት ይገኛል።

አብዮታዊ ዴሞክራሲ የወለዳቸው የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ከአስራ ስምንት ዓመታት የኢህአዴግ አገዛዝ በኋላም ቢሆን አገሪቱ ከምትታወቅበት የረሃብ እና የችጋር ገጽታ ፈቀቅ ሊያደርጉዋት አልቻሉም። «ግብርና መር ኢንዱስትርያላይዜሽን» ተብሎ የሚጠራው የልማት ስትራተጂ ራሱን ችሎ ለመቆም ያልቻለው ግብርና ሌሎቹን ሴክተሮች ይመራል ብሎ የተነሳ በመሆኑ ሌሎች ሴክተሮች ችላ እንዲባሉ ምክንያት ሆኗል። ግብርናውን ራሱ ከዝናብ ጥገኛነት ሊያላቅቀው የሚችል የመስኖ ማስፋፋት ፖሊሲ ድጋፍ ሳይበጅለት በመቅረቱ እጅግ ተለዋዋጭ ስርጭት ላለው ዝናብ ሙሉ በሙሉ ጥገኛ እንደሆነ ቀጥሏል። በዚህም ምክንያት የሃገራችን ሕዝብ ለረሃብ፤ በዚያውም ለውጭ እርዳታ ተጋላጭነቱ እንደቀጠለ ይገኛል። ኢህአዴግ አሁን ድረስ የኢንዱስትሪ ፖሊሲ የሌለው መሆኑ ይህ ሴክተር ምን ያህል እንደተረሳ ግልፅ ያደርገዋል።  ስለ ነጻ ገበያና በዚህም ውስጥ ስለ የግል ባለሃብት ድርሻ ብዙ እየተባለ ቢሆንም ኢህአዴግ በስመ ‹‹ልማታዊ መንግስት›› በኢኮኖሚው ላይ መንግሥት ያለውን ፍጹም የበላይነት አስጠብቆ ለመሄድ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ከዚህም አልፎ በፓርቲ ቁጥጥር ሥር ያሉት ኩባንያዎች ገበያውን ከነጻ የውድድር ስርዓት ውጭ እንዲቆጣጠሩ በማድረግ በአገሪቱ ኢኮኖሚ ህይወት ውስጥ ከፍተኛ መዛነፍን ፈጥሯል። በኢኮኖሚው ሥርዓት ተንቀሳቅሶ በረጅም ጊዜ የራስ ጥረት የተፈጠረውን ባለሃብት ‹‹ኪራይ ሰብሳቢ›› ብሎ በመፈረጅ፣ በእርሱ ፈንታ የኢህአዴግ ፖለቲካዊ መሰረት ሊሆን የሚችል ‹‹ልማታዊ ባለሃብት›› የሚባል ሌላ ሃይል ለመፍጠር የሃገርን ሀብት ከአግባብ ውጭ እያፈሰሰ ይገኛል። በእነዚህ ልማታዊ ባለሀብት በተባሉት ባለሃብቶች እና በኢህአዴግ ባለስልጣናት እና ካድሬዎች መሃከል በተፈጠረ የጥቅም ትስስር እጅጉን የተንሰራፋውን ሙስና ለመቆጣጠር መሞከር ለኢህአዴግ የግራውን እጅ በቀኙ እጅ መቁረጥ፤ ሄዶ ሄዶም የራስን ሕይወት በራስ ማጥፋት እንዲሆንበት አድርጎታል።

የኢህአዴግ የተሳሳቱ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ያስገኙት ድምር ውጤት አሁንም ረሃብ እና ችጋር፣ አስከፊ የኑሮ ውድነት፣ ስራአጥነትና ያፈጠጠ የኑሮ ልዩነት እና ድህነት ሲሆኑ፣ እነዚህ ተደማምረው የሕዝቦቻችንን ህልውና በእጅጉ እየተፈታተኑት ይገኛሉ። ይህ ሁኔታ በሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች በተለይ ደግሞ በወጣቱ ላይ እየፈጠረ ያለውን የተስፋ መቁረጥ ሁኔታ እጅጉን የከፋ አድርጎታል። እውነታው ይህ ሆኖ እያለ ኢህአዴግ አሁንም «ኢኮኖሚያችን በፍጥነት አድጓል» እያለ አሃዞች እየጠቀሰልን ነው። ይባስ ብሎም «በሚልዮን የሚቆጠሩ ሚልየነር ገበሬዎች ተፈጥረዋል» በማለት በሃገራችን አርሶ አደር ድህነት፣ ረሃብና ሰቆቃ ላይ ከማሾፍ ያልተናነሰ የሕዝብ ግንኙነት ስራ እየሰራ ነው። እነዚህ እውነታዎች የሚያመለክቱት የኢህአዴግ መንግስት የተደቀኑብንን ችግሮች መፍታት ይቅርና በትክክልም ለመገንዘብ እንዳይችል ያነገበው የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ርእዮት እጅጉን የገደበው መሆኑን ነው።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ኢህአዴግ ራሱን ከደርግ ጋር በማነጻጸር ከደርግ እሻላለሁ የሚል ክርክር ይዟል። ማነጻጸርያውን ትናንት ማድረጉ ኢህአዴግ ወደፊት ለማየት መቸገሩን ከማመልከቱም ባሻገር ደርግ የነበረበት እና አሁን ኢህአዴግ ያለበት ዘመን የተለያዩ መሆናቸውን የሳተ ነው። የደርግ ዘመን አምባገነኖች ከአንዱ ወይም ከሌላው ርእሰ ሃያል መንግስት ጉያ ተጠልለው ያለጠያቂ በገዛ ሕዝባቸው ላይ ያሻቸውን የሚያደርጉበት የቀዝቃዛው ጦርነት ዘመን እንደነበር፤ የአሁኑ ዘመን ግን መንግስታት ለመረጣቸው ህዝብ ተጠያቂ የሚሆኑበት፣ አለያም በዓለም ማሕበረሰብ ፊት ተጠየቁ የሚባሉበት ዘመን መሆኑን ኢህአዴግ ስቶታል። ያ ዘመን የበርሊን አጥር፣ የመረጃ አፈና /ጃሚንግ/፣ የሳንሱር ወዘተ ዘመን መሆኑ፤ የአሁኑ ዘመን ግን ድንበር የማይገድበው፣ አጥር የማይከለክለው፣ ሳንሱር የማይደርስበት፣ መጠነ ሰፊ የሃሳብ፣ የመረጃ እና የእውቀት ዝውውር የሚካሄድበት ዘመን መሆኑ፤ የድሮው ዘመን ሳይመለስ መቀበሩን ማነጻጸሪያው ከአሁኑ ዘመን እንጂ ካለፈው ጋር አለመሆኑን ኢህአዴግ ሊገነዘብ ይገባዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብም ሆነ ዘመኑ እየጠየቁ ያሉት በአንድ በኩል ሃሳብን በነጻ የመግለጽ መብት ነው እያለ በሌላ በኩል ነጻ ፕሬስን የሚገድልና ኢንተርኔትን የሚያፍን፣ ነጻ ምርጫ እያለ ኮሮጆ የሚገለብጥ፣መድበለ ፓርቲ ሥርዓትን እቀበላለሁ እያለ ተቃዋሚዎችን በጠላትነት ፈርጆ ካለጠፋኋችሁ የሚል ስሙን የቀየረ አመባገነናዊ አገዛዝን ከቶ አይደለም። ነጻነት እኩልነት እና ዴሞክራሲ የሚጠይቀውን መስዋእትነት ከመክፈል ወደ ኋላ ብሎ የማያውቀውን ታላቁን የኢትዮጵያ ህዝብ ለዴሞክራሲ አልበቃህምና ዴሞክራሲን የምትጎናጸፈው በሂደት ለዚህ ስትበቃ ነው ብለው የሚያሾፉበትን ዘመን-አመጣሽ አምባገነኖችን አይደለም።የኢትዮጵያ ህዝብ ዕድሉ ከተሰጠው ዴሞክራሲን በአግባቡ ለመጠቀም የሚችል ጨዋና በሳል ህዝብ መሆኑን በ1997 ዓም ምርጫና ከዚያም በፊት ባደረጋቸው ምርጫዎችና እንቅስቃሴዎች አስመስክሯል። አሁንም የኢትዮጵ ሕዝብ እየጠየቀ ያለው ላለፈው ታላቅ የነፃነት ተጋድሎው እና ለዘመኑ የሚመጥን መንግስት ነው። የኢትዮጵያ ህዝብ ይህን መቀዳጀት የነበረበት ትናንትና ነው፤ ኢህአዴግ እንደሚለው ከሁለትና ሶስት አስርት ዓመታት በኂላ አይደለም!!

የሃገራችን ኢትዮጵያ መሰረታዊ ችግሮች በኢህአዴግ ሪዕዮተዓለምና መስመር እንዲሁም በኢህአዴግ ዐቅም ብቻ ሊፈቱ እንደማይችሉ በመገንዘብ፣ ችግሮቹ ሁሉንም ባለድርሻዎች ባሳተፈ መልኩ እንዲፈቱ በተደጋጋሚ ቢጠየቅም በስልጣን ላይ ካለው የኢህአዴግ መንግስት ገንቢ ምላሽ ባለመገኘቱ ችግሮች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሱ መሄዳቸው ግልፅ ነው። ይህ በዚሁ እንዳለ የሃገራችን መሰረታዊ ችግሮች በሰላማዊ

የፖለቲካ ውድድር አሸንፌው በሚወጡ አማራጮች ለመፍታትና የመቻቻል ፖለቲካዊ ባህልን ለማዳበር የሚያስችልና የዴሞክራሲ ስርዓትን እውን ለማድረግ የትግል ትብብር መፍጠር የወቅቱ የኢትዮጵያ አንገብጋቢ ጥያቄ መሆኑን በመገንዘብ የኢትዮጵያ ሕዝብ የፖለቲካ ድርጅቶችን እንዲተባበሩ ሲወተውት የቆየበት ጉዳይ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ የሚንቀሳቀሱ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ቢያንስ በመለስተኛ ፕሮግራም ዙሪያ በመሰባሰብ የኢትዮጵያን ህዝብ አስተባብረው በሰላማዊ መንገድ የሚደረገውን ትግል በተጠናከረ ሁኔታ በመቀጠል፣ በፖለቲካዊው ውድድር አሸንፎ የሚወጣ አማራጭ ሆነው ለመቅረብ  እስካሁን ድረስ ያለመቻላቸውን መፍትሔ የሚሻ ድክመት መሆኑ በቂ ግንዛቤ ያገኘበት ደረጃ ላይ የደረስን መሆኑን እናምናለን፡፡

በኢትዮጵያ ተንሰራፍተው ያሉትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ችግሮች ለማስወገድና በተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅቶች ዙርያም ያለውን ተባብሮ ለመስራት ያለመቻል ድክመት ለመቅረፍ፤ መድረክ ለዲሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ/መድረክ/ የተባለውን ስድስት ፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሁለት ታዋቂ የፖለቲካ ሰዎች ሰኔ 2000 ዓ.ም ላይ መጀመራቸው፤ የካቲት 2001ዓ.ም ላይ ደግሞ ሌሎች ሁለት ፓርቲዎች ተጨምረውበት በጋራ መስራት መጀመራቸው ይታወሳል፡፡

የዚህ መድረክ መጀመር በኢትዮጵያውያን/ት ዘንድ ተስፋም ጥርጣሬም አጭሯል፡፡ እስካሁን ድረስ በተቃዋሚ ፓርቲዎች ሰፈር የታየው የመተባበር እና የመሰነጣጠቅ ታሪክ እና ምርጫ 97 ላይ የታየውን ሁኔታ በመገንዘብ የአሁኑ ሙከራ የተለየ ውጤት ማስገኘቱን የተጠራጠሩ፤ በመድረኩ ጥላ የተሰባሰቡት ድርጅቶች ብሄራዊ እና ሕብረ ብሄራዊ አደረጃጀት ያላቸው በመሆናቸው እና በእነዚህ ድርጅቶች መሃከል ያለው የፖለቲካ እና የአደረጃጀት ልዩነት ተቀራርቦ ለመስራት የሚፈጥረውን ችግር በማጤን የተጠራጠሩ እንደነበሩ ሁሉ እስካሁን ድረስ በተቃዋሚ ፖለቲከኞች ሰፈር የነበረው አለመግባባት ያስከተለውን ጉዳት በመገንዘብ፤ ካለፈው የትግል ሂደት ከተገኘው አወንታዊ ልምድ በመማር እና አሉታዊ ልምዶቹንም በማረም የተሻለ ውጤትን እና አዲስ የብሄራዊ እና የሕብረ ብሄራዊ ድርጅቶች መስተጋብር ሊወለድ ይችላል ብለው ተስፋ ያደረጉም ነበሩ፡፡

መድረኩ በተወሰኑ የጋራ መርሆዎች የተሰባሰበ ከመሆን ወጥቶ በመለስተኛ ፕሮግራም ዙርያ የተሰባሰበ እና ሕጋዊ እውቅና ያለው አደረጃጀት ወደ መሆን ይሸጋገር ዘንድ የካቲት 2001 ላይ ባደረገው ስብሰባ የጋራ መለስተኛ ፕሮግራም አርቃቂ ግብረሃይል አቋቁሞ ግብረሃይሉ ላለፉት አራት ወራት ባደረጋቸው ምክክር፣ ውይይት እና ድርድር የሁሉም ፓርቲዎች ተወካዮች ተስማምተውበት የመድረኩ መስራቾች ለሚፈጥሩት ሕጋዊ ጥምረት የጋራ ፕሮግራም ሆኖ እንዲወጣ ይህንን ሰነድ አቅርበዋል፡፡

ፕሮግራሙ የአገራችንን ፖለቲካዊ ስርዓት ከአብዮታዊ ዴሞክራሲ ርእዮት እንዲላቀቅ በማድረግ በህግ መንግስቱ የሰፈሩትን የዜጎች ሰብአዊ እና ዴሞክራስያዊ መብቶች እንዲከበሩ፣ ኢትዮጵያ አፅድቃ የተቀበለቻቸው ዓለምአቀፍ ስምምነቶች እና መርሆዎች ተግራዊ እንዲሆኑ፣ ይህንን የሚፃረሩ በስራ ላይ ያሉ ሕጎች እና አሰራሮች እንዲሻሩ ወይም እንደአስፈላጊነቱ ማሰተከካከያ እንዲደረግባቸው ያደረጋል፡፡ በብሄር ብሄረሰብ መብት መከበር እና በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ተቃርኖ እንደሌለ የጋራ ግንዛቤ ተወስዷል፣ ሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች ያለምንም ጣልቃ ገብነት ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብታቸው እንደሚጠበቅ በሁሉም ዘንድ ስምምነት አለ፣ ሁሉም መገንጠልን እንደማይደግፉ እና ለኢትዮጵያ አንድነት ሉኣላዊነት መከበር በጋራ

እንደሚቆሙ በመስራቾቹ መካከል መግባባት ላይ ተደርሶ መለስተኛ ፕሮግራሙ በዚሁ መንፈስ ተዘጋጅቷል፡፡ በኢህአዴግ ዴሞክራስያዊ ማእከልነት መርሕ የተሸበበው ፌዴራላዊ ስርዓት በትክክል ተግባራዊ እንዲሆን እና የሶስቱም የመንግስት አካላት የስልጣን ክፍፍል አንዱ ሌላውን በሚቆጣጠርበት መልኩ ተግባራዊ እንደሚሆን ተገልጿል፡፡ ይህንን ማሳካት እንዲቻል እስካሁን የታዩትን ጉድለቶች በመገምገም በሕግ አውጪው፣ በሕግ ተርጓሚው እና በሕግ አስፈፃሚው አካላት ውስጥ የሚደረጉ ማስተካከያዎች ተለይተው ተቀምጠዋል፡፡ ከዚህም ውስጥ ምርጫን፤ የመገናኛ ብዙኃንን፤ የመከላከያ እና የጸጥታ ተቋማትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ልዩ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል፡፡

የሃገራችን ችግሮች ውስብስብ መሆናቸውን በመገንዘብ መለስተኛ ፕሮግራሙ ኢህአዴግን ጨምሮ ሁሉንም ባለድርሻዎች በሚያሳትፍ መልኩ የሚፈቱበትን የብሄራዊ መግባባት እና የብሄራዊ እርቅ መርሆዎችን አስቀምጧል፡፡

በኢኮኖሚ ዘርፍ የኢህአዴግን የልማታዊ መንግስት እና የልማታዊ ባለሃብት ፈሊጥን በማስወገድ የሃገር ውስጥ ባለሃብቶችን እንደ አንድ የሃገር እሴት በመውሰድ ከአድልዎ እና ከሙስና የጸዳ ሁሉን አቀፍ ድጋፍ እንዲያገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ ግብርና መር ኢንዱስትርያላይዜሽን የተባለውን ስትራተጂ የማይሰራ መሆኑን በመገንዘብ ግብርናን ከዝናብ ጥገኝነት ለማላቀቅ እንዲቻል ለመስኖ ልማት ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ኢንዱስትሪን ጨምሮ ሌሎቹ ሴክተሮች የየራሳቸው ፖሊስ ተነድፎላቸው ራሳቸውን ችለው እንዲያድጉ እርስ በርስ በመደጋገፍም የተስተካከለ ሃገራዊ ልማት የሚያረጋግጥ የፖሊሲ ማእቀፍ እንደሚኖር ተመልክቷል፡፡ የውሃ ሃብታችንን ለሁሉን አቀፍ ልማት የሚያውል፤ የማእድን ሃብታችን ተጠንቶ እና ለምቶ ለኢንዱስትሪያዊ ልማታችን አስፈላጊውን ግብአት ሊያቀርብ የሚችልበት ሁኔታ የሚፈጥር ፖሊሲ ተቀመጧል፡፡

ትምህርት ከገዢው ፓርቲ ፖለቲካዊ አስተሳሰብ ተቀጥላነት ተላቆ፤ የወደፊት ትውልዶች እና የአገራችን እጣ ፈንታ የሚወስን ትልቅ የእሴት ግንባታ ስራ መሆኑን የተገነዘበ የፖሊሲ አቅጣጫ እንዲሚኖር ረቂቅ ፕሮግራሙ አመልክቷል፡፡ የከፍተኛ ትምህርት መርሃ ግብር መስፋፋት የተቋማቱን አቅም ከመገንባትና በቂ አስተማሪዎችን እና ግብአቶችን ከሚሟላት ጋር ዝርዝር እቅድ ተዘጋጅቶለት እንዲከናወን በማድረግ የሚመረቁት ወጣቶች በቂ እውቀት እና ክህሎት ያላቸው ሆነው እንዲወጡ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የግል የትምህርት ተቋማት ጥራቱን የጠበቀ ትምህርት በመስጠት ለአገራችን የተማረ የሰው ሃይል ግንባታ ተገቢውን አስተዋጽኦ ማድረግ ይችሉ ዘንድ ተገቢው ድጋፍም ክትትልም እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ጤናን በተመለከተ በሽታን መከላከል ውጤታማ እና ዘለቄታዊ ይሆን ዘንድ በሽታን በመከላከል ረገድ ቁልፍ ሚና ያላቸውን ተቋማት ለመገንባት ልዩ ተኩረት ይሰጣል፡፡ ከዚሁ በተጓዳኝ እጅጉን ወድቆ ያለውን በሽታን የማከም አቅም እንዲጠናከር ይደረጋል፤ የግል የሕክምና እና የምርመራ ማእከላት የሚጠይቁት ክፍያ ከተጠቃሚው የመክፈል አቅም እንዲቀራረብ ለማድረግ የሚያስችሉ በጥናት ላይ የተመሰረቱ ፖሊሲዎች እንዲወጡ ይደረጋል፡፡ ረቂቅ ፕሮግራሙ በማሕበራዊው ዘርፍ ከትምህርት እና ጤና በተጨማሪ እንደ ስራአጥነት፣ የምሁራን ፍልሰት እና መሕበራዊ ዋስትና የመሳሰሉ ጉዳዮችንም ዳስሷል፡፡

የአገራችን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና አስፈጻሚው ሚኒስቴር መስርያ ቤት አጠቃላይ የእይታ እና የአሰራር ለውጥ እንደሚያስፈልጋቸው መለስተኛ ፕሮግራሙ በአጽንኦት አመልክቷል፡፡ የአልጀርሱ ስምምነት የኢትዮጵያን ጥቅም የማያስጠብቅ ከመሆኑ ባሻገር በኤርትራ መንግስት የተጣሰ በመሆኑ ኢትዮጵያ ከዚህ ስምምነት ራሷን አለማግለሏ ስህተት መሆኑን፤ የኢትዮጵያን እና የኤርትራን ግንኙነት በዘለቄታው

ይስተካከል ዘንድ የባህር በርን ጨምሮ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የድንበር፣ ወዘተ የመሳሰሉትን የሁለቱን አገሮች ግንኙነት የሚመለከቱ ጉዳዮችን ያካተተ ሁሉን አቀፍ ድርድር መካሄድ እንዳለበት በመለስተኛ ፕሮግራሙ ተቀምጧል። መለስተኛ ፕሮግራሙ ድንበር ተሻጋሪ ወንዞችን በተመለከተ ኢትዮጵያ ልትከተል የሚገባትን ፖሊሲም አስቀምጧል።

ከፍ ብሎ እንደተገለጸው መድረኩ ከአንድ አመት በፊት ሲጀመር ከተወሰኑ የጋራ መርሆዎች ያለፈ ይህ ነው የሚባል የጋራ ፕሮግራም አልነበረውም። ከአንድ አመት የጋራ ጥረት እና ምክክር በኋላ የምክክር መድረኩ ይህንን የጋራ መለስተኛ ፕሮግራም ለኢትዮጵያ ህዝብ ለማቅረብ በቅቷል። በዚህ አጋጣሚ አስካሁን ድረስ በተስፋ እና በትዕግስት ለጠበቀን መላው ሕዝባችን ያለንን ታላቅ አክብሮት ለመግለጽ እንወዳለን። መለስተኛ ፕሮግራሙ ያልተሟሉ በርካታ ነገሮች እንደሚኖሩት እንገነዘባለን፣ የኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ግንባታ ስራ የመላ ኢትዮጵያውያን ስራ እንደመሆኑ መጠን ሁሉም ኢትዮጵያዊያን ለዚህ ፕሮግም መጎልበት እና ተፈጻሚነት የራሳቸውን ድርሻ እንዲያበረክትም በአክብሮት እንጠይቃለን።

መለስተኛ ፕሮግራሙ በስምንት ፓርቲዎችና በሁለት ታዋቂ ግለሰቦች ትብበር የተዘጋጀ ቢሆንም በአገራችን መቻቻልና መተባበር ይኖር ዘንድ ሌሎች ፓርቲዎችም የመድረኩ ዓላማ የሚኖረውን ፋይዳ ተመልክታችሁ በጋራ የምንሠራበት ሁኔታ □ንዲኖር ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የመድረኩ መስራች ፓርቲዎች አባላትና ደጋፊዎችም ፓርቲዎቻችሁ ይህንን መድረክ እንዲቀላቀሉ እና እንዲያጠናክሩ ላደረጋችሁት ትግል እና ድጋፍ በድጋሚ እናመሰግናለን። አሁንም የተራመድነው አንድ በጎ እርመጃ ብቻ መሆኑን ተገንዝባችሁ፤ ወደፊት ገና ብዙ የጋራ ጥረትና ሥራ እንደሚጠብቀን ልናሳስባችሁ እንወዳለን። በጋራ ጥረታችሁ ፕሮግራሙ ተግባራዊ እንደሚሆንም የጸና እምነታችን ነው።

የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎችም ከዚህ በፊትም እንደተናገርነው ሁሉ ዋናው ትኩረታችን የሃገራችንን ውስብስብ ችግሮች በሕብረት እና በመግባባት መንፈስ የሚፈታበትን መንገድ መሻት እንደሆነ፤ በማንኛውም መልኩ ኢህአዴግን ለማጥፋት ይሁን የአባላቱን እና የደጋፊዎቹን መብት ለመንካት አላማ እንዳላደረገ ከዚህ መለስተኛ ፕሮግራም ይዘት ለመገንዘብ ትችላላችሁ። በመሆኑም ፓርቲያችሁ ለሃገራችን ችግሮች መፈታት የበኩሉን ገንቢ አስተዋጽኦ ያደርግ ዘንድ የበኩላችሁን ገንቢ ሚና እንድትጫወቱ አሁንም ታሪካዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

በአገራችን የምትገኙ የውጭ የዲፕሎማሲ ማሕበረሰብም ፍላጎታችን የዜጎች ዴሞክራሲያዊና ሰብአዊ መብቶች የሚከበሩባት ብሄር ብሄረሰቦች መበቶቻቸው ተጠብቀው በመከባበር የሚኖሩባት የተረጋጋች የበለጸገችና ጠንካራ ኢትዮጵያ ለመገንባት መሆኑን ተገነዝባችሁ ይህንን ጥረታችንን ትደግፉ ዘንድ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

መንግስትም በበኩሉ ይህን ለአገራችን ይበጃል ያልነውን ፕሮግራም ተግባራዊ እናደርግ ዘንድ ያለበትን ሐላፊነት እንዲወጣ እንጠይቃለን።

## ii. **<u>አጠቃላይ መርሆዎችና አቋሞች</u>**

1. ለኢትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት በጽናት እንቆማለን። በቀድሞ የነበሩትንና በአሁኑ ጊዜ ያሉትን ኢፍትሃዊና አድሎአዊ አሠራሮች የተወገዱበት በመከባበር ላይ የተመሠረተ አንድነት እንዲጠናከር በጽናት እንቆማለን በመሆኑም መገንጠልን አንደግፍም።

2. የግለሰብ፣ የብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ህዝቦችና የቡድን መብቶች እኩል እንዲከበሩ ሳንታክት እንሠራለን።

3. ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች የሚከበሩባትና ማሕበረ-ኢኮኖሚያዊ ፍትሕ የሰፈነባት፣ በብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች እኩልነት ላይ የተመሠረተች፣ የበለጸገች ኢትዮጵያ ለመገንባት ጠንክርን እንንቀሳቀሳለን። ለዚህም

3.1 ሰብአዊ መብት በሁለንተናዊ መልኩ እንዲከበር

3.2 ገለልተኛ የፍትሕ ሥርዓት ተዘርግቶ የሕግ የበላይነት በተግባር እንዲገለጽ

3.3 ዴሞክራሲያዊ መብቶች ያለገደብ እንዲከበሩ ማለትም

ሀ. በነጻ የመደራጀትና የመንቀሳቀስ ያልተገደበ መብት

ለ. የመናገር፣ የመጻፍና ሀሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት

ሐ. ነጻና ፍትሓዊ ምርጫ በገለልተኛ የምርጫ አስፈጻሚዎች በተአማኒነት ማከናወን እና

መ. የመድብለ-ፓርቲ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ እውን የሚሆንበትን ስርዓት ለመገንባት በቆራጥነት እንንቀሳቀሳለን።

4 አንዱ የሌላውን ፖለቲካዊ አመለካከትና ርእዮተአለም በማስገደድ ለመቀየር ወይም ለማስቀየር ሳይሆን ሁሉም የየራሱን ፖለቲካዊ አመለካከት እና ርእዮተአለም በነጻነት የማራመድ መብቱ የሚከበርበት የሰለጠነ ፖለቲካ ለማካሄድ የሚያስችል ሁኔታ እንዲሰፍን ለማድረግ እንንቀሳቀሳለን።

5 በመሰረታዊ ሃገራዊ ጉዳዮች ላይ ብሄራዊ መግባባት መፍጠር ለሃገራችን እጅግ አስፈላጊና አንገብጋቢ በመሆኑ ለዚህ ዓላማ ተኩረት ሰጥተን እንራመዳለን ለተግባራዊነቱም እንታገላለን።

የብሄራዊ መግባባት ውይይት እንዲካሄድ ሁኔታዎችን እናመቻቻለን፤ በዚህም የብሄራዊ መግባባት ውይይት ላይ አሁን ሥልጣን ላይ ያለውን ገዢ ፓርቲ ጨምሮ በሃገር ውስጥ በሰላማዊ መንገድ የሚንቀሳቀሱትን፣ በውጭ ሃገር የሚንቀሳቀሱትን እና በትጥቅ ትግል ዓላማቸውን የሚያራምዱትን የፖለቲካ ድርጅቶችን፣ □ፅሞ □□ ሠላማዊ ትግሉ ተመልሰው በብሔራዊ መግባባቱ እንዲሳተፉ እናደርጋለን። የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎችን እና ብሄር ብሄረሰቦችም እንዲሳተፉ (እንዲካተቱ) እንደርጋለን። ህዝቡ መርጦን ለስልጣን ከበቃንም ሁሉንም የፖለቲካ ሓይሎች የሚያሳትፍ ብሄራዊ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ የአንድነት መንግስት እናቋቁማለን።

6 ዕርቅና ሰላም በሃገራችን መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ለማስማማት እና ለብሄራዊ መግባባት እንቅስቃሴ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው። በመሆኑም የሃገራችን ፖለቲካ ከቂም በቀል እና ከጥላቻ ስሜት እንዲሁም ከተለያዩ ቁርሾዎች የሚላቀቅበት ሁኔታ እንዲፈጠር እንታገላለን።

ለዕርቅና ሰላም ሲባል ዜጎች የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ አባል ወይም የአንድ መንግስታዊ ተቋም ባልደረባ በመሆናቸው ብቻ የማይወነጀሉበትና በግለሰብ ደረጃ የፈጸሙት ወንጀል እስከሌለ ድረስ መብታቸው በአግባቡ (በሙሉ) የሚከበርበት ሁኔታ ለመፍጠር እንሰራለን።

7 ሕገ መንግስታዊ ስርዓት እንዲኖር እና እንዲጠናከር እየሰራን ሕገ መንግስቱ ሁሉንም የፖለቲካ ሃይሎችና ሕዝቡን ባሳተፈ መልኩ ወይይት ተደርጎበት በሕዝበ ውሳኔ □ ምር የሚሻሻልበት ሁኔታ እንዲፈጠር ተግተን እንሰራለን፡፡

## Ì፡ **ክፍል አንድ፡- ፖለቲካዊ ጉዳዮች**

### 1. ሰብዓዊ መብቶችን ስለማስከበር

1.1. በሥራ ላይ ያለው ሕገ መንግስት በሃገራችን መሠረታዊ የሆኑ መብቶችና ነፃነቶች፣ ማለትም ሰብአዊና ዴሞክራስያዊ መብቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ የማይጣሱና የማይገፈፉ መሆናቸውን በግልፅ ቢያውጅም፤ ይህንንም በተመለከተ ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች (ማለትም እ.ኤ.አ. 1948 ዓ.ም. የጸደቀው አለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች አዋጅ (UN Human Rights Declaration)፣ እ.ኤ.አ 1976 ዓ.ም. የጸደቀው አለምአቀፍ የዜጎች እና የፖለቲካ መብቶች ኮንቬንሽን፣ የአፍሪካ የሰብአዊና የሕዝቦች መብቶች ቻርተር እና የኮተኑ ስምምነት፣ ወዘተ) የሃገሪቱ ሕግ አካል መሆናቸውንና፣ በሕገ መንግስቱ የተዘረዘሩት መሰረታዊ መብቶች እና ነፃነቶች ከእነዚህ ሕግጋት፣ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና ዓለም አቀፍ ሠነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ይተረጎማል ብሎ ቢደነግግም፤ ማንኛውም ዜጋ፣ የመንግስት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሌሎች ማሕበራት፣ እንዲሁም ባለስልጣኖቻቸው ሕገ መንግስቱን የማስከበርና፣ ለሕገ መንግስቱ ተገዢ የመሆን ኃላፊነት እንዳለባቸው በግልፅ ቢደነግግም፤ ኢህአዴግ እና እርሱ የሚመራው መንግስት እነዚህን የዜጎች መብቶች እና ነፃነቶች ማክበር ያለመቻል ብቻ ሳይሆን ራሱም በብዙ መልኩ እየጣሰና እየገፈፈ ቆይቶአል፡፡ በዚህም ምክንያት ዜጎች በግለሰብም ሆነ በቡድን ደረጃ ለከፍተኛ ጉዳትና እንግልት ተዳርገዋል፡፡

መድረኩ እነዚህ መብቶች በሁለንተናዊ መልኩ ይከበሩ ዘንድ በጽናት ይቆማል፡፡ ማንኛውም የመንግስት አካላት እንዲያከብሩዋቸው፤ ባያከብሩዋቸው ደግሞ ሁሉም በሕግ ተጠያቂ የሚሆኑበትን ስርዓት ያመቻቻል፡፡ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን የሚዘገቡበት፤ ምርመራ እና ማጣራት የሚካሄድበት፤ ግኝቱ ይፋ የሚሆንበት፤በዳዮች ለሕግ የሚቀርቡበት ተበዳዮችም ለደረሰባቸው በደል የሞራል እና የማተርያል ካሳ የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡ ለዚህ አላማ ተብለው የተቋቋሙት መንግስታዊ ተቋማት ሥራቸውን በብቃት ለማከናወን እንዲችሉ በሕግም በአደረጃጀትም ተመጣጣኝ ጉልበት እንዲኖራቸው ይደረጋል፤ በዚህ ዙርያ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችም ስራቸውን በተገቢው ያከናውኑ ዘንድ አስፈላጊው የሕግ ማዕቀፍ ይፈጠርላቸዋል፡፡

1.2. ማንኛውም ሰው የማይደፈር እና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር መብት አለው፡፡ በሕግ አስፈጻሚ አካላት ሕገ ወጥ እርምጃ ዜጎች ሕይወታቸውን የሚያጡበት ሁኔታ በማያዳግም ይቆም ዘንድ፤ መታሰራቸው እየታወቀ ሁኔታቸው ግን ያልታወቀ ዜጎች እና የተገደሉ ዜጎች ሁኔታ የሚዘገብበት፤ ምርመራ እና ማጣራት ተደርጎ አጥፊዎቹ የሚለዩበት እና ለሕግ የሚቀርቡበት ሁኔታ ይደራጃል፡፡ ይፈጠራል፡፡

ማንኛውም ባለስልጣን እና የሕግ አስፈፃሚው አካል ባልደረባ ለሚወስነው እና ለሚፈጽመው ሕገ ወጥ ድርጊት ኃላፊ እና ተጠያቂ ይሆናል፡፡ ባለስልጣናት

በሚመሩዋቸው ተቋማት አማካኝነት ለሚፈጸም የሰብአዊ መብት ጥሰት የመጀመርያ ኃላፊነት ተሸካሚዎች ይሆናሉ፡፡

1.3. ማንኛውም ሰው ንብረት የማፍራት መብት አለው፡፡ መንግስት ለግል ንብረት ተገቢውን ጥበቃ ይሰጣል፡፡ ማንኛውም ግለሰብ ካለራሱ ፈቃድ ወይም ከፍርድ ቤት ውሳኔ ውጪ ሃብቱ እና ንብረቱ አይወሰድበትም፡፡ ለሃገር የጋራ ልማት ወይም ደህንነት የግል ንብረት ለመንግስት አገልግሎት ማዋል ቢያስፈልግ ባለንብረቱ በወቅቱ የገበያ ዋጋ ተመጣጣኝ ካሳ ይሰጠዋል፡፡

1.4. መድረኩ ሽብርተኝነትን ይቃወማል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ኢህአዴግ የፖለቲካ ተቃዋሚዎቹን በአሸባሪነት የሚፈርጅበትን መመዘኛ እና በፀረ-ሽብር ትግል ሽፋን በሰላማዊ ዜጎች ላይ የሚፈጽመውን የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን አጥብቆ ይቃወማል፡፡

1.5. የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብት ኮሚሽን የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን ለመከታተል በሚያስችለው መልኩ ከአስፈጻሚው አካል ነፃ ሆኖ እንዲቋቋም እና እንዲደራጅ ይደረጋል፡፡ ተበዳይ ወገኖች እና መንግስታዊ ያልሆኑ የሰብአዊ መብት ድርጅቶች ጨምሮ ከማንኛውም ወገን የሚቀርቡትን የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን የሚመለከቱ አቤቱታዎችን እና ጥቆማዎችን ይቀበላል፤ ይመረምራል፡፡ የሚያስከስስ የሰብአዊ መብት ጥሰት ተፈጽሞአል ብሎ ሲያምን በበዳዩ ላይ ክስ ይመሰረት ዘንድ ጉዳዩን ለዓቃቤ ሕግ ይመራል፡፡ ኮሚሽኑ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያቀርበው መደበኛ ሪፖርት ውሰጥ ይህንንም ያካተተ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

ኮሚሽኑ በሚያከናውነው ስራ ውስጥ የሕግ አስፈጻሚውም ሆነ የሌላ አካላት ማንኛውም ጣልቃ ገብነት እንዳይኖረው የሚያስችል ሕግ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡ ለስራው የሚመጥን አመራር፤ አደረጃጀት እና የሙያተኛ ጥንቅር እንዲኖረው እና በቂ ባጀት እንዲመደብለት ይደረጋል፡፡ ኮሚሽኑ ይሕንን ሲያደርግ ስራው ከሙስና እና ከወገንተኝነት በጸዳ መልኩ ያከናውን ዘንድ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፈላጊውን ስርዓት እንዲያበጅ ይደረጋል፡፡

1.6. በሕገ መንግስት እንደተደነገገው ማንኛውም ሰው የግል ሕይወቱ፣ ግላዊነቱ የመከበር መብት አለው፡፡ በዚህ መሰረት የደህንነት ተቋማት በዜጎች የግል ሕይወት ላይ የሚያደርጉት ክትትል፤ በሕብረተሰቡ ውስጥ የፍርሃት ድባብ ለመፍጠር እየተደረጉ ያሉ የዛቻ እና የማስፈራርያ እንቅስቃሴዎች እንዲቆሙ ይደረጋሉ፡፡ በሰው የግል መኖርያ ቤት ይሁን የስራ ቦታ ያለፍርድ ቤት ትእዛዝ በዘፈቀደ ገብቶ ክትትል ይሁን ብርበራ እንዳይኖሩ ይደረጋል፡፡

ለሃገር እና ለሕዝብ ደህንነት ሲባል ይህንን ማድረግ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ ክትትሉም ሆነ ብርበራው የሚከናወነው በሕግ ስልጣን በተሰጠው አካል የጽሑፍ ትእዛዝ ወይም ፈቃድ ከተሰጠ ብቻ ይሆናል፡፡ አስፈጻሚው አካል ትእዛዙን የሚፈጽመው ከማንኛውም ማስፈራራት እና እንግልት በጸዳ መልኩ ይሆናል፡፡

1.7. በሕገ መንግስቱ እንደተደነገገው የዜጎች በሕግ ከተደነገገው ስርዓት ውጪ ነጻነታቸውን አያጡም፡፡ በመሆኑም፤

1.7.1. ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጪ ሊያዝ እና ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይገባውም፡፡ የተያዙ ሰዎች ምርመራ በሚደረግበት ጊዜ ድብደባን ጨምሮ ከማንኛውም ኢሰብአዊ ከሆነ እና ክብርን ከሚያያዋርድ ምርመራ የተጠበቁ ይሆናሉ፡፡

"ማንኛውም ሰው በራሱ ላይ እንዲመሰክር አይገደድም" የሚለውን ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ በመተላለፍ የሚፈጸሙት የማስገደድ እርምጃዎች እና ሁኔታዎች እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡

1.7.2 ማንኛውም ሰው በፖለቲካ አመለካከቱ ምክንያት አይታሰርም፡፡ በፖለቲካ አመለካከታቸው ምክንያት በእሰር የሚገኙ ወገኖችም እንዲፈቱ ይደረጋል፡፡

1.7.3. የተያዙ ሰዎች ወንጀል መስራታቸው በፍርድ እስኪረጋገጥ ድረስ ንጹህ እንደሆኑ ይቆጠራል፡፡ መንግስት የተያዙትን ሰዎች ጥፋተኛ ለማሰኘት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚያደርገው የሕዝብ ግንኙነት ስራ የተከለከለ ይሆናል፡፡

1.7.4. የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት አላቸው፡፡ በሕግ በተደነገገው መሰረት ዋስትና መፍቀድ አለመፍቀድ የሚወሰነው በፍርድ ቤት ይሆናል፡፡ መንግስት የተያዙ ሰዎች በዋስ መለቀቅ የለባቸውም ብሎ ካመነ ለፍርድ ቤት የማስረዳት ሽክሙን ይወጣል እንጂ ለፍርድ ቤቶች ሚዛናዊ ውሳኔ የተተወውን የዋስ መብት መጠበቅን ጉዳይ የሚጻረር ማንኛውም እርምጃ አይወስድም፡፡

መድረክ ኢህአዴግ የተያያዘውን መሰረታዊ የሆኑትን ሰብአዊ እና ዴሞክራስያዊ መብቶችን የሚፃረሩ ሕጎችን የማውጣት እንቅስቃሴ አጥብቆ ይቃወማል፡፡

1.7.5. የተያዙ ሰዎች ወደ ፍርድ ቤት የመቅረባቸው ጉዳይ በፖሊስ ፈቃድ የሚወሰን መሆኑ ቀርቶ በሕገ መንግስቱ በተደነገገው መሰረት በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ እንዲፈጸም ይደረጋል፡፡ ፖሊስ ለተጨማሪ ምርመራ ፍርድ ቤትን ተጨማሪ ጊዜ ሊጠይቅ ፍርድ ቤትም ሊፈቅድ ይችላል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ለተጨማሪ ምርመራ የሚሰጠው በጊዜው ርዝማኔ እና በቀጠሮዎቹ ብዛት የተገደበ እንዲሆን በማድረግ ተጨማሪ ጊዜ በመጠየቅ ሽፋን በተያዙ ሰዎች ላይ የሚደረገው መጉላላት እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

1.7.6. የተያዙ ሰዎች በሕግ በታወቀ እስር ቤት ብቻ ይቆያሉ፣ በአገራችን በሕግ ያልታወቀ ድብቅ እስር ቤት እንዳይኖሩ ይደረጋል፡፡ በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች ሰብአዊ ክብራቸው በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ ሕገ መንግስታዊ መብታቸው ይጠበቅ ዘንድ እድሜ፣ ፆታን እና የጤንነት ሁኔታን ባገናዘበ መልኩ፤ ምግብ፣ ሕክምና፣ በቂ ውሃ፣ መጸዳጃ እና ንጽሕና መጠበቅያ በተሟላበት ሁኔታ፤ በቂ ብርሃን፣ አየር፣ መንቀሳቀሻን ጨምሮ ለመኝታ የሚሆን በቂ ስፍራ በተዘጋጀበት እስር ቤት እንዲኖሩ በማድረግ አሁን በአገሪቱ እስር ቤቶች ያለውን ዘግናኝ የእስር ቤቶች ሁኔታ እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡

1.7.7. የታሰሩ ሰዎች በሕገ መንግስቱ የተደነገገውን ከትዳር ጓደኞቻቸው፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከሃይማኖት አማካሪዎቻቸው፣ ከሐኪሞቻቸው እና ከሕግ አማካሪዎቻቸው ጋር የመገናኝትና እንዲጎበኟቸው ዕድል የማገኘት መብት አላቸው፡፡

ማንኛውም የፖሊስ ጣብያ አዛዥ፣ የማረምያ ቤት አዛዥ እና መርማሪ ፖሊስ ከላይ የተገለጹት የማከበር ኃላፊነቱ የሚረጋገጥበት፤ ሕጉና የሙያው ስነ ምግባር ከሚፈቅደው ውጪ የሆነ ድርጊት እንዲያከናውን ከበላይ ኃላፊዎቹ የሚደርስበትን ጫና ይቋቋም ዘንድ ለራሱም ተገቢውን ጥበቃ የሚያገኝበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

## 2. የእምነት ነፃነት

2.1. ማንኛውም ዜጋ የፈለገውን ሃይማኖት የመከተል መብቱ የተጠበቀ ነው፤ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በእምነቱ ምክንያት ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ የተረጋገጠለትን መብትና ጥቅም አይነፈገውም፡፡

ሃይማኖት የግል ሃገር ግን የጋራ መሆናቸው ግንዛቤ አግኝቶ፤ መንግስት እና ሃይማኖት፣ ሃይማኖት እና ፖለቲካ እንዲለያዩ፤ መንግስታዊ ሃይማኖት እንደሌለ ሁሉ የመንግስትን ስልጣን ለመቆጣጠር የሚንቀሳቀስ ሃይማኖት አለመኖሩ እንዲጠበቅ መድረኩ አበክሮ ይሰራል፡፡

2.2. ሃይማኖቶች በመንግስት ፊት እኩል ናቸው፡፡ በመሆኑም መንግስት ሁሉንም በእኩል ያስተናግዳል፣ እኩል ጥበቃም ያደርግላቸዋል፡፡

2.3. በሃገራችን ኢትዮጵያ በሃይማኖቶች መካከል መቻቻል እና መከባበር እንዲኖር ተግተን እንሠራለን፡፡ ለተግባራዊነቱም የሃይማኖት ተቋማት፣ ምእመናን፣ መንግስት፣ ፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሲቪክ ማኅበራት በኃላፊነት መንፈስ በጋራ እንዲሠሩ እናደርጋለን፡፡

የእምነት ተቋማት ተቀራርቦ በመወያየት አንዱ ሃይማኖት በሌላው ሃይማኖት ጣልቃ መግባትንና የሚያስወግዱበት፤ በሃይማኖታዊ ትምህርትና ስብከት ሽፋን አንዱ የሌላውን እምነት የሚያጣጥልበት ሁኔታ እንዳይኖር የሚያደርጉበት ከተቻለ ይህንን ለማረጋገጥ የሚችል የጋራ የስነ ምግባር መርሆዎች ላይ መግባባት የሚደርሱበት ሁኔታ እንዲፈጠር መድረኩ የሚቻለውን ሁሉ ያደርጋል፡፡

## 3. ዴሞክራስያዊ መብቶች በተመለከተ

### 3.1. ሃሳብን በነፃነት የመግለፅ መብት

3.1.1. ሕገ መንግስቱ "ለፕሬስ ልዩ ጥበቃ ይደረጋል" ፣ "የመንግስት መገናኛ ብዙሃን ለሁሉም በእኩል ያገለግላሉ ቢልም፤ ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ እንደሚችል፤ ሃሳቡን የመግለጽ ነፃነት እንዳለው፤ ይህ ነፃነት በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሃሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶችን እንደሚያካትት ቢደነግግም ኢህአዴግ በታወጁ ሕግጋት እና ባልታወጁ ውስጣዊ መመርያዎች አማክኝነት እነዚህን ነፃነቶች እና መብቶች አፍኗል፡፡

ከአስር አመታት በፊት የወጣው የብሮድካስት አዋጅ ተግባራዊ ሳይሆን መክኖ እንዲቀር አድርጓል፤ የመንግስት መገናኛ ብዙኃን ነፃ የዜጎች ሃሳብ መንሸራሸርያ መሆናቸው ቀርቶ የኢህአዴግ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ርእዮት ማስረጽ ላይ እንዲጠመዱ ተደረገዋል፡፡ በማተሚያ ቤቶች በሚደረግ ስውር ጫና፣ በሕትመት ወረቀት ላይ በተጫነው ቀረጥ፣ በአዲሱ የፕሬስ ሕግ በኩል በጋዜጠኞች እና በአሳታሚዎች ላይ የተነጣጠረው አስፈሪ ቅጣት ምክንያቶች የግል ፕሬስ እንዲዳከም፣ በፍርሃት ራሱን በገዛ ራሱ ሳንሱር እንዲያደርግ እና ለመንግስትና ለኢህአዴግ እንዲያጎበድድ እየተደረገ ይገኛል፡፡

መድረክ ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት በሕገ መንግስቱ በሰፈረው መሰረት እና በሱ መሰረት ብቻ ተግባራዊ እንዲሆን ያደረጋል፤ ለሕገ መንግስቱ አላማና መንፈስ ተፃራሪ የሆኑት ሕጎች እንዲሻሩ እና በመትካቸው የሕገ-መንግስቱን መንፈስ እና አለማ የሚያነጸባርቁ ሕጎች እንዲወጡ፡፡ የሚወጣውን ሕግ በትክክል ተግባራዊ የሚያደርጉ ተቋማት እንዲቋቋሙ ያደርጋል፡፡ ተቋማቱን ለመምራት የሚሾሙት ሰዎች ለዚሁ ሃገራዊ ኃላፊነት የሚመጥን ሙያዊ ብቃት ያላቸው እና ከፖለቲካዊ ወገንተኝነት ገለልተኛ ሆነው የሚሰሩ ሰዎች እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡

3.1.2. ሕትመት ለሃገር ሰብአዊ ሃብት እድገት ላይ ያለውን ግዙፍ አስተዋጽኦ በመገንዘብ፤ የሕትመት ዋጋ በእውቀትና ሃሳቦች ስርጭት መስፋት እና መጥበብ ላይ ያለውን ስፍራ በማጤን፤ ከሕትመት ጋር ተያያዥ የሆኑ ወጪዎች እንዲቀነሱ ወይም ተማጣጣኝ እንዲሆኑ በማድረግ የሕትመት ውጤቶች ለአንባብያን በዋጋ ተደራሽ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

3.1.3. በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠውን የዜጎች ሃሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት የሚያረጋግጡ የፕሬስ እና የብሮድካስት አዋጆች እንዲወጡ እና ሥራ ላይ እንዲውሉ እናደርጋለን፡፡ በዚህም ከመንግስት በተጓዳኝ በፕሬሱም ሆነ በኤሌክትሮኒክ ሚድያው ጠንካራ የግሉ ሴክተር ተሳትፎ እንዲኖር ይደረጋል፡፡

3.1.4. የመንግስት መገናኛ ብዙሃን የገዢው ፓርቲ ፖለቲካ መጥመቅያ ከመሆን ተላቀው ከፖለቲካ ፓርቲ ወገንተኝነት በጸዳ መልኩ አገልግሎታቸውን እንዲሰጡ ይደረጋል፤ ለፓርቲዎች ያላቸው ተደራሽነትም በእኩልነት እና በፍትሃዊነት መርሕ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

እንደወረዳ ኔት እና ስኩል ኔት የመሳሰሉት በመንግስት ሃብት የተገነቡት መገናኛ ዘዴዎች ለገዢው ፓርቲ ፖለቲካ አላማ ማሰራጫነት መዋላቸው ቀርቶ ለተቋቋሙለት አላማና ለሕዝብ መረጃ ማሰራጫ አገልግሎት እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

3.1.5. በኢንተርኔት እና በቴሌፎን በኩል የሚደረገው ግንኙነት ቴክኖሎጂው የፈቀደውን ያክል አሟጦ በመጠቀም ዜጎች የሚያስፈልጋቸውን መረጃ ያለአንዳች ስጋት የመያገኙበት እና የሚለዋወጡበት እንዲሆን ይደረጋል፡፡

መድረክ መረጃን በመከልከል ሳይሆን እድገት እና ሰላም የሚረጋገጠው ዜጎች ይበልጠውኑ ለመረጃ እና ለእውቀት ቅርብ እንዲሆኑ በማደረግ ነው ብሎ ያምናል፡፡ ከዚህ በመነሳትም ይህንኑን ቴክኖሎጂ መልሶ ዜጎችን ለመሰለያነት እና ነጻ የመረጃ እና የሃሳብ ልውውጥን ለመገደብ የማዋሉ አፋኝ እንቅስቃሴ እንዲቆም ያደረጋል፡፡ በዚህም መሰረት እንደጃሚንግ፤ የኢንተርኔት ጣብያዎች አፈና እና የስልክ ጠለፋ የመሳሰሉት ሕገ ወጥ ተግባራት እንዲቀሩ ያደረጋል፡፡

3.1.6. ሃሳብን የማሰራጨት ነፃነት በስነ-ጽሕፍ፣ በትያትር፣ በሙዚቃና ዘፈን፣በፊልም እና በስዕል፣ እንዲሁም በስነ ቅርፅ መልክ የሚደረገውን ስርጭት ይጨምራል፡፡ እንደፕሬስ እና ኤሌክትሮኒክ ሚድያ ሁሉ በእነዚህ ዘርፎች የሚደረገው ስውር ሳንሱር እና ክልከላ ይወገዳል፡፡

3.1.7. መድረክ፤ ሃሳብ ከመግለጽ ነፃነት ጎን ለጎን የሃገርን ነፃነት እና ጥቅም የማስጠበቅ፤ የሕዝብን ባህል እና ወግ ከማክበር፤ ለራስ ክብር እና ነፃነት ቀናኢ የመሆን ያክል ለሌሎች ወገኖች ነፃነት እና መልካም ስም ጥበቃ የማድረግ፤ እንዲሁም ሕገ መንግስቱንና ሌሎች የሃገሪቱን ሕጎች የማክበር ግዴታዎችም አብረው እንደሚኖሩ ይገነዘባል፡፡ በመሆኑም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር እነዚህ ግዴታዎች የሚከበሩበት ሁኔታ እንዲኖር አበክሮ ይሰራል፡፡

### 3.2. የመደራጀት መብት

3.2.1. ገዢው ፓርቲ ለሕዝብ ነጻ እንቅስቃሴ እና ነጻ አደረጃጀት ካለው ስጋት እና ፍርሃት በመነጨ ምክንያት ሁሉን የሕዝብ አደረጃጀት በቁጥጥሩ ስር የማደረግ፤ ይህንን ድርጊቱን የማይቀበሉትን የማፍረስ እና እምቢ ባለው ላይ ሌላ ተቀናቃኝ ድርጅት ሲፈጥር ቆይቷል፡፡ ይባስ ብሎ ደግሞ ከሱ ድምጽ ሌላ ድምጽ የሚያሰሙትን፤ ለእርሱ ድጋፍ ከመስጠት ተቆጥበው ለቆሙለት አላማ እና ለአቋቋማቸው አባል መብት እና ጥቅም የሚቆሙትን ድርጅቶች የገቢ ምንጭ አጥተው እንዲቀጭጩ የሚያደረጉ ሕጎችን ማውጣት ስራ ላይ ተጠምዶ ይገኛል፡፡

መድረክ ነጻ እና ሰፊ የሕዝብ ተሳትፎ ያላቸው፤ ለሰላምና ለገንቢ አላማ የሚታገሉ ድርጅቶች በአገሪቱ መገኘት ለዜጎች ነጻነት መከበር አስኝታ እንደሆነ እና የዜጎች ነጻነት ለመከበሩ ማረጋገጫ እንደሆነ ያምናል፡፡ በመሆኑም በሕገ መንግስቱ የተደነገገው የመደራጀት መብት ያለአንዳች መሰናክል እንዲከበር እና በመደራጀት መብት ላይ ሳንካ ለመፍጠር የወጡት ሕጎች እንዲሻሩ እና እንዲስተካከሉ ይታገላል፡፡

3.2.2. ማንኛውም ግለሰብ ሃሳቡንና ፍላጎቱን ከሌሎች ጋር በሰላማዊ መንገድ ለመተግበር በሙያ፣ በትምህርት፣ በብዙሃን ማህበር፤ በፖለቲካ የመደራጀት መብቱ የተጠበቀ ይሆናል፡፡ የመብት አጠቃቀሙ በግለሰቡና በተደራጀበት ተቋም ፈቃድ እና በሕገ መንግስቱ ብቻ ይወሰናል፡፡

ማንኛውም ፖለቲካዊ ያልሆነ አደረጃጀት በፖለቲካ ጉዳይ አቋም ለመውሰድ ሳይገደድ ለቆመለት አላማ እና ለአቋቋሙት አባለት መብት የመቆም እና የመከራከር መብት አለው፡፡

3.2.3. በስራ ላይ ያሉት የፓርቲ፣ የሲቪክ ማሕበረሰብ እና ሌሎች የሕዝብ አደረጃጀትን የሚመለከቱ ሕጎች ለቆሙለት ዓላማ እና ለአባላቱ ያለባቸውን ግዴታ በሚያስጠብቅ እና የመደራጀት መብትን በማይገድብ መልኩ እንዲከለሱ ይደረጋል፡፡

መንግስት ከፖለቲካ ወገንተኝነት በፀዳ መልኩ የሕዝብ አደረጃጀቶችን ጥያቄዎች የማስተናገድ እና የማስተዳደር ግዴታ ይኖረዋል፡፡ ለእነዚህ ተቋማት ከመንግስት የሚቀርብ ድጋፍ በሚኖርበት ጊዜ እና ሁኔታ አቅርቦቱ ፍተሃዊ በሆነ መንገድ ለሁሉም ስንዲደርስ ይደረጋል፡፡

3.2.4. የሴቶች፣ የወጣቶች፣ የገበሬዎችና የንግዱ ማሕበረ-ሰብ □ሙ□ ማሕበራት ከመንግስት እና ከገዢው ፓርቲ ጥገኝነትና ተጽእኖ ነፃ ሆነው በሲቪክ ማሕበርነታቸው ለአባሎቻቸው ፍላጎትና ለሕግ ብቻ ተገዥ በመሆን እንዲደራጁ እና እንዲንቀሳቀሱ ሁኔታው ይመቻቻል፡፡ ህዋሶችና ሌሎች የፓርቲ መዋቀሮች በነዚህና በሌሎች ሲቪክ ማሕበራት ውስጥ ማደራጀትም ሕገ ወጥ ይሆናል፡፡ እነዚህ ነፃ መሕበራት በነፃ መሕበርነታቸው ከመንግስት የሚያገኙት አገልግሎት እንደማንኛውም የኢትዮጵያ ማሕበራት ይሆናል፡፡

በፓርቲ መዋቅሮች የሚደራጁት የሴቶችም ሆኑ የወጣቶች ማሕበራት ግን የፓርቲያቸው አካላት ስለሆኑ መላውን ሴቶችን ወይም ወጣቶችን እንደሚወክሉ በማስመሰል ገዥው ፓርቲ የመንግስት ሃብት ያለአግባብ እንዲጠቀሙ የሚያደርግበት አሰራር አድሎአዊ አሰራር በመሆኑ እንዲቀር ይደረጋል፡፡

### 3.3. የመሰብሰብና ሰልፍ የማድረግ መብት

3.3.1. ሕገ መንግስቱ ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣርያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነት እና አቤቱታ የማቅረብ መብት እንዳለው ቢደነግግም፤ የመንግስት አካላት ይህንን አውቀው ለጥበቃ አስፈላጊውን ቅድም ዝግጅት ያደርጉ ዘንድ ከሰብሰባ እና ሰልፍ አዘጋጆች በኩል የሚጠበቀው ተፈላጊውን መረጃ መስጠት እና ማሳወቅ ብቻ መሆኑ በሕግ ቢደነገግም ኢህአዴግ በተግባር ይህንን የማሳወቅ ግዴታ ፈቃድ ወደ መጠየቅ ግዴታ እንዲቀየር አድርጎታል፡፡ ፈቃድ መጠየቁንም ለራሱ መሰብሰብያ ቦታ ከማገኘት እና ከመከራየት፤ መከራየቱንም ራሱ ተመልሶ ፍቃድ ከማግኘት ጋር እንዲቆላለፍ በማደረግ በአገሪቱ ስብሰባ ይሁን ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ የማይቻል ወይም በጣም አስቸጋሪ እንዲሆን በማድረግ ዜጎች በዚህ መብታቸው እንዳይጠቀሙ ክልከላ አበጅቶባቸዋል፡፡

መድረክ በሕገ መንግስቱ ውስጥ የሰፈረውን መብት እና ነፃነት የሰፈረበትን መንፈስና አለማ በመገንዘብ ያላንዳች መሸራረፍ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል፡፡ እንቅፋት የሆኑትን ሕጎችና አሰራሮች እንዲሻሩ ያደረጋል፡፡ በዚህ ሕገ መንግስታዊ መብት ላይ እንቅፋት የሚፈጥሩ የፌዴራል እና የክልል መንግስታት ባለስልጣናት አስፈላጊው የእርምት እርምጃ እንዲወሰድባቸው ይታገላል፡፡

3.3.2. በሕግ ግድ የሚለውን መረጃ አሟልቶ ሰለማዊ ሰልፍ ወይም የሚደረግ መሆኑን ለሚመለከተው የመንግስት አካል ማሳወቅ፣ የእንቅስቃሴው ዓላማና የስልቱ ሰላማዊ መሆን ለተሳታፊዎቹ ማሳወቅ እና መቀስቀስ የአዘጋጆቹ የስራ ድርሻ ይሆናል፡፡ ይሕ ተደርጎም በሰልፉ እና በስብሰባው ሂደት ላይ በሰርጎ ገቦች እና መሰል አፍራሽ አካላት ምክንያት ሂደቱ ቢታዎክ ፀጥታውን የማስጠበቅ እና አጥፊዎችን ለይቶ የመያዝ ኃላፊነት የመንግስት ፀጥታ ሃይሎች ይሆናል፡፡ ይህንን በመፃርር ሂደቱ ቢታወክ ሃላፊነቱን ሙሉ በሙሉ በአዘጋጆች እንዲወድቅ የሚያደረግ አሰራር ሰዎች በፍርሃት ምክንያት በመብታቸው እንዳይጠቀሙ የሚያደረግ እጅ አዙር ክልከላ ነው ብሎ መድረክ ያምናል፡፡

በመሆኑም አዘጋጆቹም ሆኑ የፀጥታ አስከባሪ ሃይሎች በተቀመጠው የስራ ድርሻ መሰረት የሚሰሩበት ሁኔታ በመፍጠር ዜጎች ያለአንዳች መሸማቀቅ የመሰብሰብ፤ ሰልፍ የማድረግ እና አቤቱታ የማቅረብ ሕገ መንግስታዊ መብታቸው ተግባራዊ አንዲያደረጉ ይደረጋል፡፡

3.3.3. አደራሽ የሚያከራዩ ወገኖች ያለአንዳች መሸማቀቅ አገልግሎታቸውን ቀድሞ የመጣ ቅድምያ ያገኛል በሚልህ መርህ እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡ የመንግስት ልማት ድርጅቶች እና የመንግስት መስርያ ቤቶች የሚከራይ መሰብሰብያ አዳራሽ እስካላቸው ድረስ ቀድሞ ለመጣ ቅድምያ ያገኛል በሚል መርህ እንዲያከራዩ የሚያስችል ስርአት እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡ በመላ ሃገሪቱ ወጥ የሆነ በሕገ መንግስት ድንጋጌዎች የመፈጸም ልምድ ይኖር ዘንደ ይህ አሰራር በፌዴራልም ሆነ በክልል መንግስታት ተፈፃሚ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

### 3.4. የመምረጥና የመመረጥ መብት

3.4.1. በሃገራችን ተንሰራፍቶ የቆየው በሃይልና በደም መፋሰስ ስልጣን የሚያዝበትን እና የሚለቀቅበትን ሁኔታ ማስቀረት እንዲቻል፤ ያለህዝብ ይሁንታ ስልጣን የጨበጡት አገዛዞች ከሕዝቡ በኩል የመጣባቸውን ተቃውሞ ለማረገብ ሲጠቀሙበት የቆየው የሃይል መልስ በሃገራችን ያስከተለውን ደም መፋሰስ እና ጦርነቶች በማስቀረት የሃገራችን ውሱን ሃብት ለልማት ማዋል የሚቻልበትን ሁኔታ

ለመፍጠር እንዲቻል፤ ኢትዮጵያውያን ተወካዮቻቸውን በቀጥታ በመምረጥ በሚያደርጉት ዴሞክራስያዊ ተሳትፎ አማካኝነት የመረጡትን መንግስት እንደሚቀይሩ፤ ከዚህ ውጭ በማናቸውም አኳኋን የመንግስት ስልጣን መያዝ እንደማይቻል በኢፌድሪ ሕገ መንግስት እንዲደነገግ ሆኗል፡፡

ኢህአዴግ ይህ እውን ይሆን ዘንድ እርሱንና ተፎካካሪዎቹ ፓርቲዎችን በእኩልነት የሚያስተናግድ የምርጫ ስርዓት የማደራጀት ሕገ መንግስታዊ ግዴታ ቢጣልበትም፤ በዴሞክራሲያዊ ምርጫ ተወዳድሮ ስልጣን እንደያጣ ካለው ስጋትና ስልጣንን ሁሌም ለመያዝ ካለው ፍላጎት በመነሳት ይህን ግዴታውን ሊወጣ አልቻለም፡፡

በዚህ መንገድ ስልጣንን እንደያዘ ለመቀጠል ኢህአዴግ ይዞት ያለው አካሄድ በሕገ መንግስቱ ከተደነገገው ስልጣን ከሚያዝበት አኳኋን ውጪ የሆነ አኳኋን ነው ብሎ መድረኩ ያምናል፡፡ በሃገራችን ኢትዮጵያ ስልጣን በሕገ መንግስቱ በተደነገገው አኳኋን ብቻ የሚያዝበት እና በሕገ መንግስቱ በተደነገገው አኳኋን ብቻ በስልጣን ለመቆየት የሚቻልበት ሁኔታ ይፈጠር ዘንድ ሰላማዊ እና ሕጋዊ ትግሉን ይቀጥላል፡፡

3.4.2. ነፃ፣ፍትሃዊ እና ርትኣዊ ምርጫ ይደራጅ ዘንድ፤

3.4.2.1. መከናወን ያለበት የመጀመርያ ቁልፍ ተግባር ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ መኖር መሆኑ መድረኩ ያምናል፡፡ እስካሁን ድረስ በታዩት የምርጫ ሙከራዎች እና ምርጫ ነክ እንቅስቃሴዎች ውስጥ በሃገራችን የኢህአዴግን ፍላጎት ከማስፈጸም ያለፈ ገለልተኛ የምርጫ ቦርድ አልታየም፡፡

መድረክ በመራጩ ሕዝብ እና በተቃዋሚ ፓርቲዎች ጭምር እምነት የሚጣልበት፤ በሚመለከታቸው ወገኖች ምክክር ተመልምለው ለሹመት የሚበቁ የቦርድ አባላት እንዲኖሩ አበክሮ ይሰራል፡፡

3.4.2.2. ከቦርዱ ጽሕፈት ቤት ጀምሮ እስከ ታችኛው እርከን ድረስ በሚዘረጋው የምርጫው አስፈጻሚ መዋቅር ውስጥ የሚሾሙት የስራ ኃላፊዎች እና የሚቀጠሩት ሰራተኞች የገዢው ፓርቲ አባላት እና ደጋፊዎች ያልሆኑ፤ የተሰጣቸውን ታላቅ የሃገር ተልእኮ ከአድልዎ በጸዳ መልኩ ማከናወን የሚችሉ ይሆኑ ዘንድ ምልመላቸው በችሎታ ላይ የተመሰረተ እና ለማንኛውም ኢትዮጵያዊ ግልጽ እና ክፍት በሆነ መልኩ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በዚህም መሠረት ምልመላና ቅጥሩ ጉዳዩ የሚመለከታቸውና በአካባቢው የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ሌሎች አካላት በሚሳተፉበት ሁኔታ እንዲፈፀም □□ረ□ል፡፡

3.4.2.3. ምርጫ ተኣማኒነት ይኖረው ዘንድ የሃገር ውስጥ እና የውጪ ታዛቢዎች በስፋት የመሳተፋቸው ጉዳይ ትልቅ ስፍራ ያለው እንደመሆኑ የሃገር ውስጥ ታዛቢዎች ገለልተኛ እንዲሆኑ፣ የሕዝብ ታዛቢዎች በተለይ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ተወካዮች ባሉበት በሕዝቡ ምርጫ የሚከናወን እንዲሆን እና በዚሁ መልኩ ተዛቢዎች በብዛት እንዲሳተፉ መመቻቸት ይኖርበታል፡፡ ከየት እና እነማን እንደሚሳተፉ ገደብ በሌለው መልኩ የውጭ ታዛቢዎች በብዛት መጥተው ምርጫውን ይታዘቡ ዘንድ ሁኔታዎች መመቻቸት እንዳለባቸው መድረኩ ያምናል፡፡

3.4.2.4. የሃገሪቱ ሃብት እና አሴቶች በተለይ ደግሞ በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉት የመንግስት መገናኛ ብዙሃን ያለአድልዎ ለሁሉም ተፎካካሪ ወገኖች የሚዳረሱበት ድልድል እንዲኖር መደረግ ይኖርበታል፡፡

የገዢው ፓርቲ አባላት የመንግስት ገንዘብ፣ የመንግስት ተሽከርካሪ፣ ቢሮ እና ስልክ እየተጠቀሙ የሚንቀሳቀሱበት፤ በሌላ በኩል ደግሞ ተቃዋሚዎች ለዚህ የአገር

ሃብት እንደእንጀራ ልጅ የሚታዩበት ሁኔታ ቀርቶ ሁሉም ወገን ተመጣጣኝ ድርሻ የሚያገኝበት ሁኔታ መፈጠር አለበት ብሎ መድረኩ ያምናል፡፡

ተቃዋሚዎችን በመወከል በምርጫ እንቅስቃሴ ተሳተፊ የነበሩ ዜጎች ተቃዋሚን ደግፋችኋል ተብሎ ከምርጫ በኋላ የሚከናወነው ከስራ የማፈናቀል እና የማሳደድ ተግባር መቆም ይኖረበታል፡፡ ለምርጫ ተወዳድረው የነበሩ የሲቪል ሰረቪስ አባላት ምርጫውን ሳያሸንፉ በቀሩበት ሁኔታ ወደ ነበሩበት ስራ እንዲመለሱ ወይንም ተመጣጣኝ ሥራ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

3.4.3. በህዝብ እንደራሴነት ሲያገለግሉ የነበሩ ወገኖች አገልግሎታቸውን ባጠናቀቁበት ወቅት ለአገልግሎታቸው ክብር ተሰጥዋቸው ወደ ነበሩበት ስራ እንዲመለሱ ወይንም ተመጣጣኝ ሥራ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

3.4.4. በምርጫ ውጤት ላይ በሚፈጥሩት አላስፈላጊ መንተት እና ውዝግብ ለማስወገድ እንዲቻል እና የመራጮችን መብት ለማስከበር ሲባል የሚከተሉት ለውጦች እና ማስተካከያዎች እንዲኖሩ መድረኩ ይታገላል፡፡

3.4.3.1. ምርጫው በሕግ የተቀመጠውን ጊዜ ሳያዛንፍ በሁሉም ክልሎች በአንዴ መካሄድ ይኖርበታል፡፡

3.4.3.2. የምርጫ ውጤት ቢበዛ በሰባ ሁለት ሰዓት ውስጥ ለሕዝብ ይፋ መሆን ይኖርበታል፡፡

3.4.3.3. የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ለመጡበት የምርጫ ክልል ብቻ ይምረጡ መባሉ ቀርቶ ዩኒቨርሲቲው ባለበት ክልል ወይም ለመጡበት ምር□ ክልል፤ ከሁለቱ አንዱ እንዲመርጡ ውሳኔው ለእነሱ ሊተውላቸው ይገባል፡፡

3.4.3.4. በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ባሉበት ሆነው በምርጫ የመሳተፍ መብታቸው የሚከበርበት ሁኔታ እንዲመቻች ይደረጋል፡፡

3.4.3.5. የምርጫ ጉዳዮችን የሚዳኙ ልዩ ችሎቶች እንዲቋቋሙ ይደረጋል፡፡

3.4.4. አንድ የሕዝብ ተመራጭ የመራጩ ሕዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ በህዝቡ ጥያቄ የሕዝብ ተወካይነቱን የሚያጣበት ሁኔታ በሕጎች ተደንግጓል፡፡ የሕዝቡን አመኔታ ያጣ የሕዝብ ተወካይ በሕጉ መሰረት ከተወካይነቱ መነሳቱ መኖር የለበት ተገቢ ስርዓት ነው ብሎ መድረክ ያምናል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ እስካሁን ከታየው ልምድ ገዢው ፓርቲ ይህንን ስርዓት ሕገ ወጥ በሆነ መንገድ ከውስጡ የሚነሱትን ተቃዋሚዎች እና ከተቃዋሚ ፓርቲዎች በኩል ጠንካራ ትችት የሚሰነዝሩበትን ተወካዮች ማስወገጃ በመሳርያነት እየተጠቀመበት ነው፡፡ ይህንን ለማስወገድ የሚከተሉት መርሆዎች ሊከበሩ እንደሚገባ መድረኩ ያምናል፤

3.4.4.1. በአንድ የሕዝብ ተወካይ እና በፓርቲው መሃከል የሃሳብ ልዩነት በሚከሰትበት ሁኔታ፤ የበላይ የሚሆነው የፓርቲው ውስጣዊ አሰራር እና ደንብ ሳይሆን የምክር ቤቱ አባላት የመላው ሕዝብ ተወካይ እንደመሆናቸው፤ ተገዢነታቸውም ለሕገ መንግስቱ፣ ለሕዝቡ እና ለሕሊናቸው ብቻ ይሆናል የሚለው ሕገ መንግስታዊ ድንጋጌ ይሆናል፡፡

3.4.4.2. አንድ ተመራጭ በፓርቲው ስም ቢወዳደርም የሕዝብ ተወካይ የሚሰኘው ሕዝብ ከመረጠው በኂላ እንደመሆኑ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወንበሩን የሚያጣው የሕዝብ አመኔታ ሲያጣ እንጂ የፓርቲው አመኔታ ሲያጣ አይሆንም፡፡ በመሆኑም የይነሳልን ጥያቄ በመረጠው ሕዝብ ወይም በዕጩነት ባቀረበው ፓርቲ

በሚነሳበት ወቅት ጉዳዩ የሚወሰነው በምርጫ ክልሉ የመረጠው ሕዝብ በሕጉ መሰረት በሚሰጠው ድምፅ ይሆናል።

3.4.4.3. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ በአንድ የሕዝብ ተወካይ ላይ ከተወካይነት ወንበሩ ይነሳ የሚል ጥያቄ በተነሳበት ሁኔታ የማንሳቱ ሂደት በሕጉ እና በሕጉ ብቻ መከናወኑን የሚከታተልበት የራሱ ስርዓት ሊኖረው ይገባል።

## 4. የሕግ የበላይነት እና የዳኝነት ነፃነት

4.1. በኢህአዴግ መንግስት ሕግ የሚወጣበት ዓላማና ሕግ የማውጣቱ ስርዓት እጅጉን ፈር የለቀቀ ሆኗል። ሰዎችን ለማጥቃት እና ለመጉዳት ሆን ተብሎ ሕግ ይወጣል፣ ሕግ በነጋሪት ጋዜጣ ሳይታተም በፊት ተግባራዊ ይሁን ይባላል። ይህ መታረም ይገባዋል።

የዳኞት ምልመላ እና ሹመት በሕግ እውቀት፣ ልምድና ሃቀኛነት መመስረቱ ቀርቶ ለገዢ ፓርቲው ባለ ቅርበት እና የእርሱን ፍላጎት እና ተጽእኖ ለመቀበል ባለ ፈቃደኝነት እየተመሰረተ በመሄዱ የዳኝነት ስርዓቱ ነጻነት የለም ከሚባልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። በዚህም ምክንያት ሕብረተሰባችን በዳኝነት ላይ የነበረውን እምነት እና ለዳኝነት ይሰጠው የነበረው አክብሮት ወርዷል። በዚህ ላይ ዳኞች በቁጥር አነስተኛ በመሆናቸው በቂ ችሎቶች የሉም፤ ባሉት ላይም ከፍተኛ የስራ ጫና ይታያል፤ ለዳኞች የሚሰጠው ጥቅማ ጥቅም አነስተኛ በመሆኑ ዳኞች ራስን ዝቅ ለሚያደርግ ስነ ምግባር የተጋለጡበት ሁኔታም ይታያል።

ነፃ፣ ቀልጣፋ እና በሃቀኝነት የሚሰራ የፍትህ ስርዓት መኖሩ ለአንድ አገር መረጋጋት መሰሶ፤ ዜጎች በፖለቲካ ስርዓቱ ለሚኖራቸው አመኔታ መሰረት እንደመሆኑ አሁን በዳኝነት ስርዓቱ ያሉት ችግሮች ተወግደው በሃገራችን ተአማኒነት ያለው የዳኝነት ስርዓት ይኖር ዘንድ መድረኩ አበክሮ ይሰራል።

4.2. በአገራችን የሕግ የበላይነት ለማስፈን ይቻል ዘንድ የሚከተሉት እውን እንዲሆኑ ይደረጋል፣

4.2.1. በሶስቱም የመንግስት አካላት (ሕግ አውጪው፣ ሕግ ተርጓሚው እና ሕግ አስፈፃሚው) መሃከል ግልፅ የስልጣን ክፍፍልና አንዱ ሌላውን የሚቆጣጠርበት ስርዓት (check and balance) እንዲኖር፤ ይህንኑም በጥብቅ ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል። ሕግ ተርጓሚው አካል ከሕግ አስፈፃሚ አካል ተጽእኖ ይላቀቅ ዘንድ ለዳኞች ምልመላና እድገት መመዘኛ የሚሆኑት መለኪያዎች እና አፈጻጸማቸው ከፖለቲካ ወገንተኝነት የጸዳ እንዲሆን የሚያስችል ስርአት እንዲተከል ያደረጋል። የዳኝነት ስርዓቱ ባጀት፤ የሰው ሃይል ቅጥር እና የመሳሰሉት ስራዎች ከሕግ አስፈፃሚው ተፅእኖ እንዲላቀቁ ይደረጋል። ገለልተኛ እና ጠንካራ ዳኞች ስራቸውን እንዲለቁ ወይም ለሕግ አስፈፃሚው ፍላጎች እንዲያጎበድዱ የሚደረግባቸውን ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆነ ጫና የሚወገድበት፤ ይልቁንም ጠንካሮቹ በስራቸው ተረጋግተው አገራቸውን የሚያገለግሉበት ሁኔታ እንዲፈጠርላቸው ይደረጋል።

4.2.2. የዳኝነት ስርዓቱ ነፃነት መገፈፍን ጨምሮ በአገራችን በጠቅላላ ሕገ መንግስቱ የደነገገው የስልጣን ክፍፍል ተግባራዊ እንዳይሆን ጠንቅ እየሆነ ያለው ችግር የፓርቲ ስራ እና የመንግስት ስራ ተለይቶ አለመቀመጡ መሆኑን በመገንዘብ መድረኩ የፓርቲ ስራ እና የፓርቲ መዋቅር ከመንግስት ስራ እና መንግስታዊ መዋቅሮች ተለይተው የሚሰሩበት ይህም በማንኛውም ሕጋዊ ፓርቲ ላይ ተፈጻሚ የሚሆንበት ስርዓት ይዘረጋል።

4.2.3. የአቃቤ ሕግ ቢሮ ራሱን ችሎና ከፍትሕ ሚኒስቴር ከሌሎችም አስፈፃሚ አካላት  ነፃ ሆኖ እንዲደራጅ ይደረጋ። የአቃቤ ሕጎች ተልእኮ ሕግን ማስከበር እንጂ የመንግሥትን ፖለቲካዊ ፍላጎት ብቻ ተከትሎ መሄድ እንዳይሆን፤ ወንጀል ተፈጽሟል ብለው ባመኑበት ሁኔታ ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል ባለስልጣናትን ጨምሮ በማንኛውም ወገን ላይ በራሳቸው ተነሳሽነት ክስ የመመስረት ስልጣን እንዲኖራቸው ይደረጋል።

4.3. ሕግ ከማመንጨት፤ ከማጽደቅ እና ተግባራዊ እንዲሆን ከማድረግ ጋር በተያያዘ ያለውን ብልሹ ሁኔታ ለመለወጥ የሚከተሉት ተግባራዊ ይደረጋሉ፣

4.3.1. ሕግ ማመንጨት እና ማውጣት በሕግ የወጣውን መጣስ የሚያስቀጣ መሆኑን አስቀድሞ ለዜጎች በማሳወቅ ጥፋትን እና ወንጅልን አስቀድሞ በመከላከል መርህ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ይደረጋል። ገዢው ፓርቲ ተቃዋሚዎችን ለመቆጣጠርና ለማጥቃት አልሞ የሚያወጣቸው ሕጎች እንዳይኖሩ ይደረጋል።

4.3.2. ሕጎች ከምክር ቤቱ ራሱ፤ እንዲሁም ከሕዝብ የሚመነጩበት ሁኔታ ይመቻቻል። ምክር ቤቱ ከሕግ አስፈፃሚው አካል የሚመጡለትን አጽድቄአለሁ ብሎ ማሕተም የሚመታ ምክር ቤት መሆኑ ቀርቶ በሚቀርቡለት የሕግ ረቂቆች ላይ ጊዜ ወስዶ የሚወያይበትና የሚመክርበት ሁኔታ ያመቻቻል። አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በጉዳዩ አስተያየትና እውቀት ያላቸውን ዜጎች አቅርቦ የተሸለ ግንዛቤ ይዞ ውሳኔ ላይ የሚደርስበት ሁኔታ እንዲኖረው ይደረጋል።

4.3.3. ሕጎች በነጋሪት ጋዜጣ ሳይወጡ በፊት እና ሕዝቡን በይፋ ሳያሳውቁት በፊት ተግባራዊ እንዳይሆኑ ይደረጋል። ሕጎች እንደአወጣጣቸው ቅደም ተከተል ይፋ የሚሆኑበት ገዢው ፓርቲ እንደፈቀደ የሚያዘገያቸው ወይም የሚያጣድፋቸው መሆኑ ያበቃል። በነጋሪት ጋዜጣ ከወጡ በኋላ ሕግ አስፈሚው አካል ወደደም ጠላም ሁሉም ሕጎች ተግባራዊ የሚሆኑበት ሁኔታ ይመቻቻል። ሕግ አውጪው አካል ላጸደቃቸው ሕጎች በወቅቱ ይፋ ስለመሆናቸው እና ተፈጻሚነት ሰለማግኘታቸው ሃላፊነት ወስዶ እንዲከታተል የሚያስችለው ጉልበት እና አደረጃጀት እንዲኖረው ይደረጋል

4. ሕዝብ ቀልጣፋ እና ሃቀኛ ፍትህ ያገኝ ዘንድ ከላይ በቁ.3. ከተቀመጡት በተጫማሪ የሚከተሉት ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል፣

4.1. የሃገራችንን ሕዝብ ብዛት እና ጂኦግራፍያዊ አሰፋፈር ግምት ውስጥ በማስገባት የችሎቶች ብዛት ቀመር ተዘጋጅቶ በዚሁ መሰረት ችሎቶች ተሟልተው እንዲቋቋሙ ይደረጋል። የጉዳዮች ውስብሰብነት እና የሚጠይቁት የውሳኔ ክብደት ግምት ውስጥ በማስገባት በችሎት የሚሰየሙት ዳኞች ብዛት እንዲስተካከል ይደረጋል። ዳኞች ጎደሉ ችሎት አልተሟላም በሚሉና በመሳሰሉት ምክንያቶች ዳኝነት እንዳይስተጓጎል ዳኞች ተጠባባቂዎችን ጨምሮ (ከነሪዘርቡ) እንዲመደቡ ይደረጋል።

4.2. ለዳኝነት ስርዓቱ የሚመደበው ባጀት የተቋሙ መጠናከር በአገር መረጋጋትና ዜጎች በመንግስት ላይ ከሚኖራቸው እምነት ላይ ትልቅ ስፍራ ያለው ጉዳይ መሆኑን ከመገንዘብ የሚነሳ መሆን ይኖርበታል።

በዚህ መሰረት የዳኝነት ስርዓቱ ተልእኮውን ያሳካ ዘንድ በቂ ሃብት ይመደብለታል፤ ዳኞች ስራቸውን በሃቀኝነት እና በታታሪነት ለማከናወን እንዲችሉ በቂ ደመወዝ እና ጥቅማ ጥቅም እንዲቆረጥላቸው ይደረጋል። ለአቃቤ ሕጎችም እንደዘሁ ይደረግላቸዋል።

መንግስት ለተለያዩ ጉዳዮች ያለአግባብ ብዙ ሃብት በሚያባክንበት ሃገርና ሁኔታ ለዳኝነት ስርዓቱ በቂ ባጀት አለመመደቡ ተገቢ አይደለም።

4.3. በሃገራችን የቆየው ባህላዊ የፍርድ አሰጣጥ እና ግጭት አፈታት ሽምግልና የመሳሰሉ በጎ እሴቶች የሕግ የበላይነትንና የሃገሪቱን ሕጎች እስካልተጻረሩ ድረስ ይበረታታሉ። አስፈላጊ ሙያዊና ማቴርያላዊ ድጋፍም ይደረግላቸዋል።

4.4. ማኅበራዊ ፍርድ ቤቶች አሁን ኢህአዴግ ከሚጠቀምበት የፓርቲ ወገንተኛ አሰራር ተላቀው በገለልተኝነት አገልግሎታቸውን እንዲሰጡ ይደረጋል። ሥልጣንና ሓላፊነታቸው በማሕበራዊ ነክ ጉዳዮች ዙርያ እንዲወሰን ይደረጋል። በሕግ ከሚፈቅድላቸው ውጭ በመደበኛው ፍርድ ቤት መታየት ያለባቸውን ጉዳዮች እንዳያዩ ይደረጋል። ሙያና እውቀት እንዲኖራቸው የሚያስችል ሥልጠና እየተሰጣቸው የዜጎችን ሰብአዊ መብቶች እንዳይጥሱ ሆኖ በሕግ መሰረት ስራቸውን እንዲያከናውኑ ይደረጋል።

## 5. የኢትዮጵያ አንድነት እና ሉኣላዊነት በሚመለከት

ለኢትዮጵያ ዳር ድንበር፣ ነፃነት፣አንድነት እና ሉአላዊነት የተጠበቀ እና የተከበረ ይሆን ዘንድ በጋራ እንቆማለን። እያንዳንዱ ብሄር፣ ብሄረ-ሰብና ህዝቦች ለኢትዮጵያ ዳር ድንበር፣ ነፃነት፣ አንድነት፣ ሉአላዊነት፣ የሌሎች ብሄር ብሄረ ሰቦች መብት መከበርን ጨምሮ የጋራ ለሆኑት ጥቅሞች እና እሴቶች እንዲቆሙ እንታገላለን።

በኢትዮጵያ አንድነት ላይ ለሚደቀኑ ፈተናዎች መፍትሄው በአንድነት ዙርያ ሆኖ ዴሞክራሲን ማስፋት እንጂ መገንጠል እንዳልሆነ እናምናለን። በዚህ መሰረት ሁላችንም ለኢትዮጵያ አንድነት እና ለብሄር ብሄረ ሰቦች መብት መከበር በፅናት እንቆማለን።

## 6. የብሄር፣ ብሄረሰቦችና ሕዝቦች መብት በሚመለክት

6.1. ሃገራችን ኢትዮጵያ ሕብረ-ብሄር ሃገር ነች። ቀደምት የሃገራችን አገዛዞች የብሄር በሄረሰቦችን ህልውናና መብቶች ባለመቀበልና ባለማክበር አምባገናናዊ አሃዳዊ አገዛዝ በማስፈናቸው አገዛዞቻቸው ለሃገራችን ሰላም መታጣትና አለመረጋጋት አስተዋጽኦ ሲያደርጉ ቆይተዋል።

አሁን በስልጣን ላይ ያለው የኢህአዴግ አገዛዝም በአፋኙ አሃዳዊ አገዛዝ ፋንታ መገንጠልን ጨምሮ የብሄር ብሄረሰቦች መብቶች የሚከበሩበት ፌዴራላዊ ዴሞክራስያዊ ሪፓብሊክ ስርዓት እውን አድርጌአለሁ ቢልም በተግባር ግልጽ ሆኖ የታየው ግን ስርዓቱ እውነተኛ ፌዴራላዊም ዴሞክራስያዊም አለመሆኑ ነው። በብሄር ብሄረሰብ መብት መከበር ሽፋን ተግባራዊ እየሆነ ያለው ከፋፍሎ መግዛት ነው፤ በዴሞክራሲ ስም በሃገሪቱ ሰፍኖ ያለውም የዜጎች መብቶች አፈና ነው።

የቀደምቶቹም ሆኑ የአሁኑ የአፈና አገዛዞች የብሄር በሄረሰቦች መብት የተከበረበት ዴሞክራስያዊ ስርዓት በሃገራችን እንዳይኖር ማድረጋቸው የሃገራችንን አንድነት ስጋት ላይ እንዲወድቅ አድርገዋል። በመሆኑም በዚህ መድረክ የተሰባሰብነው ሃይሎች እስካሁን ድረስ ከታዩት አካሄዶች በመማር እና የታዩትን ሰህተቶች በማረም፤ በሃገራችን የብሄር ብሄረሰቦች እኩልነትና መከባበር የሰፈነበት ዘላቂ አንድነት ይረጋገጥ ዘንድ እንታገላለን።

6.2. የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ማንነታቸው የታወቀና እኩልነታቸው የተከበረ ይሆናል። እያንዳንዱ የኢትዮጵያ በሄር በሄረሰብ ቋንቋውን፣ ባህሉን እና ታሪኩን የመጠቀም፣ የመጠበቅና የማዳበር እንዲሁም የማስተዋወቅ መብት ይኖረዋል። ሁሉም

በአካባቢያቸው ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብታቸውም የተከበረ ይሆናል፡፡ የፌዴራልም ሆነ የክልል መንግስታት ለእነዚህ መብቶች መከበር ሓላፊነትና ግዴታ ይኖራቸዋል፡፡

6.3. ሁሉም ብሄር ብሄረሰቦች በሃገሪቱ በሚካሄደው ልማት ተሳታፊ እና ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ የልማት ተጠቃሚነታቸው ለመረጋገጡ የፌደራልም እና የሚመለከተው ክልል መንግስታት ተገቢውን ክትትል ያደርጋሉ፡፡

በእድገት ወደ ኋላ በቀሩ አካባቢዎች ለሚኖሩ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ልማት ልዩ ተኩረት ይሰጣል፡፡

6.4. በቁጥር ብዙሃን በሆኑ ብሄር ብሄረሰቦች መካከል የሚኖሩ በቁጥር አናሳ የሆኑ ብሄር ብሄረሰቦች ሕልውናና ሁለንተናዊ መብታቸው የተጠበቀ ይሆናል፡፡ እነዚህ በብዙሃን ብሄር ብሄረ ሰቦች መካከል የሚኖሩ በቁጥር አናሳ የሆኑ ብሄር ብሄረ ሰቦች የራሳቸው አካባቢ መሥርተው በሚኖሩባቸው ሁሉ በቀበሌዎች፣ በወረዳዎች ወይንም በዞኖች በማደራጀት ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት ይኖራቸዋል፡፡ በየደረጃው ባሉት የበላይ አካላትም የመወከል መብታቸው የተከበረ ይሆናል፡፡

6.5. በአንድ ብሄር ብሄረ ሰብ መስተዳደር በተመሰረተበት ውስጥ የሚኖሩ የሌላ ብሄር ብሄረ ሰብ ተወላጆች መምረጥ እና መመረጥን ጨምሮ ሁሉም የዜግነት መብታቸው የተከበረ ይሆናል፡፡

6.6. ሃገሪቷ የተቀበለቻቸው የግለሰብ እና የብሄር ብሄረሰብ መብቶችን የመሳሰሉ አለማቀፋዊ ሰብአዊ እና የሲቪል መብቶች እንዲከበሩ በጋራ እንታገላለን፡፡

6.7. ከአማርኛ በተጨማሪ በበርካታ የአገሪቱ ህዝብ የሚነገር ሌላ ቋንቋ የፌደራሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 7. የኢትዮጵያ መንግስት አወቃቀር

7.1. ሃገራችን የምትከተለው የመንግስት አወቃቀር በፌዴራል እና በክልል መንግስታት የተመሰረተ ፌዴራላዊ አወቃቀር እንደሆነ፤ ሁለቱም ተጠሪነታቸው ለመረጣቸው ለሃገሪቱ ሕዝብና ለክልሎቹ ሕዝቦች እንደሆነ፤ ሁለቱም ሕዝብ በነጻነት የመረጣቸው የየራሳቸው ሕግ አውጪዎች እንደሚኖራቸው እና አንዱ በሌላው ላይ ጣልቃ ሳይገባ ሁለቱም በሕገ መንግስቱ በተደነገገው የስልጣን ክፍፍል እንደሚሰሩ ቢደነገገም ኢህአዴግ አገሪቱን እየመራ ያለው ግን በፌዴራላዊው ድንጋጌ እና መርህ ሳይሆን በአብዮታዊ ዴሞክራሲ ዴሞክራስያዊ ማእከልነት መርህ ነው፡፡

መድረክ በፌዴራል መንግስትና በክልል መንግስታት መካከል የሚኖረው የስልጣን ክፍፍል እና ግንኙነት ትክክለኛውን የፌዴራሊዝም መርህ የተከተለና በትክክልም ስራ ላይ የሚውል እንዲሆን ያደረጋል፡፡

7.2. የፌዴራል መንግስት የሕግ አውጪ አካል ባለሁለት ምክር ቤቶች (Bi-cameral) ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት የሕግ መምርያ (የሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት) እና የሕግ

መወሰኛ (የፌዴሬሽን ምክር ቤት) የሚባሉ አካላት ያሉት ፓርላማ በሕዝቡ ቀጥተኛ ተሳትፎና በነጻና ፍትሓዊ ምርጫ በተመረጡ የሕዝብ ተወካዮች እንዲቋቋሙ ይደረጋሉ፡፡

የፌዴሬሽን ምክር ቤት ከሚሰራቸው ስራዎች አንዱ በተወካዮች ምክር ቤት የሚወጡ ሕጎች ሕግ ሆነው ከመውጣታቸው በፊት በሕገ መንግስቱ መሰረት የወጡ መሆናቸውን መርምሮ ማጸደቅ ይሆናል፡፡ በዚህም መሰረት በሕግ ማውጣቱ ስራ የሚሳተፍ አካል ይሆናል፡፡

ሕገ መንግስቱን የመተርጎም ስራ ከፌዴሬሽን ምክርቤቱ ስልጣን ይወጣል፡፡ በምትኩ ይህንኑ ሥራ የሚሰራ ሕገ መንግስታዊ ፍርድቤት ይደራጃል፡፡

7.3. የአገሪቱ ፕሬዝዳንት ያልተስማማበትን የሕግ ረቂቅ ለፓርላማ የመመለስና እንደገና ውይይት እንዲደረግበት የማድረግ መብት ይኖረዋል፡፡ ፕሬዝደንቱ እንደገና እንዲታይ የመለሰው የሕግ ረቂቅ በተወካዮች ምክር ቤትና በፌደሬሽን ምክር ቤት በሦስት አራተኛ ድምጽ ከተደገፈ ፕሬዝደንቱ ባይስማማበትም ሕግ ሆኖ ይወጣል፡፡

7.4. በፌዴራል መንግስትም ሆነ በክልል መንግስታት ከነጻና ፍትሃዊ የሕዝብ ምርጫ ውጪ የሚያዝ ስልጣን አይኖርም፡፡ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ያለሕዝቡ ቀጥተኛ ምርጫ በብሔር በሔረሰብ ስም ከየክልሉ በመላክ የሚያቀቋቋምበት አሰራር ቀርቶ የምክር ቤቱ አባላት የሃገሪቱ ብሔር ብሔረሰብና ሕዝቦች በነጻና ፍትሓዊ ምርጫ በቀጥታ የሚመርጡዋቸውና የሚወክሉዋቸው ይሆናሉ፡፡

በዞኖች በወረዳዎች እና በቀበሌዎች የሚኖሩት አስፈጻሚ አካላት የስልጣን ምንጭ ነጻና ፍትሃዊ የሕዝብ ምርጫ ብቻ ይሆናል፡፡ በአሁኑ ወቅት በአማራ ክልል ከሚገኙት ጥቂት ዞኖችና በደቡብ ክልል ከሚገኙ ዞኖች በስተቀር የተቀሩት የዞን ሹማምንት ያለሕዝብ ምርጫ ከዴሞክራስያዊ አሰራርና ከሕገ መንግስቱም ውጭ በገዢው ፓርቲ እየተሾሙ ስልጣን የሚይዙበት አሰራር እንዲቀር ይደረጋል፡፡

7.5. በሕግ አስፈጻሚ አካል ውስጥ በፖለቲካ ሹመትነት የሚመደቡት ኃላፊነቶች ተለይተው እንዲታወቁ ይደረጋል፡፡ ማንኛውም የፌዴራል መንግስት የፖለቲካ ሹመት በሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት፣ ማንኛውም የክልል መንግስታት የፖለቲካዊ ሹመት ደግሞ በክልሉ ምክር ቤት ብቻ የሚወሰኑ ይሆናሉ፡፡ ሹመቱን የማጽደቁ ስራ የእያንዳንዱ እጩ ብቃት በነጠላ በመመርመር ይከናወናል፡፡ ከዚህ ውጪ ያሉት ኃላፊነቶች እና የስራ መደቦች በሙያ ብቃት እና በአገልግሎት የሚሰጡ፣ ከፖለቲካ ወገንተኝነት በጸዳ መልኩ ለዜጎች ክፍት ይሆናሉ፡፡ በዚህ መልኩ በሲቪል ሰርቪሱ ሰፍኖ ያለው የፓርቲ እና የመንግስት መደበላለቅ እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡

የፌዴራል መንግስት አስፈፃሚ አካላት ብሄራዊ ተዋፅኦንና ሙያዊ ብቃትን በአካተተ መልኩ ለሁሉም ኢትዮጵያውያን ክፍት ይሆናሉ፡፡ የክልል መንግስት አስፈጻሚ አካላትም በክልሉ ለታቀፉ ዜጎች ሁሉ ክፍት ይሆናሉ፡፡

7.6. የሚኒስቴር መስርያ ቤቶች፣ ኮሚሽኖሮችና ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቶች □ላፊዎችና አምባሳደሮች ስልጣንና ኃላፊነት በግልጽ ተለይቶ እንዲቀመጥ እና በሕግ አውጪው እንዲጸድቅ ይደረጋል፡፡ ሚኒስትሮች እና ሌሎች ተሹዋሚዎች መብታቸውና

ግዴታቸው በሕግ የተወሰነና የተጠበቀ ሆኖ ስራዎችን በሕገ መንግስትና በሕግ ላይ ተመስርተው በኃላፊነት እና በተጠያቂነት መንፈስ የሚመሩበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

7.7. በመድረኩ የጋራ ፖለቲካ እንቅስቃሴ ወቅት የሃገራችን ፖለቲካዊ ስርዓት ፓርላሜንታሪ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ አንድ ፓርቲ በተከታታይ አሸንፎ ስልጣን የሚይዝበት ሁኔታ ቢፈጠር፤ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሁለት የፓርላማ ዘመን በላይ እንዲመራ የማይፈቀድ ይሆናል፡፡

## 8. የሃገር መከላከያ ሰራዊትን በሚመለከት

8.1. የሃገር መከላከያ ሰራዊት ለሕገ መንግስት ተገዢ ሆኖ ከፖለቲካዊ ድርጅቶች ወገናዊነት በፀዳ መልኩ ተግባሩን እንደሚያከናውን ሕገ መንግስቱ ቢደነግግም የኢህአዴግ መንግስት ግን ይህንን በተገቢው አላረጋገጠም፡፡ ይህ አለመሆኑ በሠራዊቱ እና በሕዝቡ መካከል ሊኖር የሚገባውን ግንኙነት እንዳይኖር አሉታዊ አስተዋፅኦ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

የሃገር መከላከያ ሰራዊት መንግስት በተቀያየረ ቁጥር የማይቀየር እንደተቋም ቋሚ ሆኖ የመቀጠል ዋስትና ይኖረው ዘንድ ሰራዊቱ ከኢህአዴግም ሆነ ከሌላ ማንኛውም ፖለቲካዊ ፓርቲ ያልወገነ የሃገር አለኝታ ይሆን ዘንድ መድረኩ ይሰራል፡

8.2. የሃገር መከላከያ ሰራዊት ተልእኮ የሃገርን ሉአላዊነትና ዳር ድንበር ማስጠበቅ ይሆናል፡፡ ፀጥታን በማስጠበቅ ሽፋን የአገር ውስጥ የፖለቲካ ልዩነቶችን በሃይል ለማርገብ አይሰለፍም፡፡ አስቸኳይ አዋጅ በተደነገገበት ሁኔታ፤ ሰራዊቱን ከዚሁ ለተያያዘ ስራ ማሰማራት የግድ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜ፤ ለሰራዊት የሚሰጡት ተግባራት በአዋጁ ውስጥ በግልፅ ተለይተው መቀመጥ ይኖርባቸዋል፡፡

ከዚህ ውጪ ሰራዊት የፖሊስ ስራ እንዲሰራ የሚደረግበት ሁኔታ አይኖርም፣ በአስተዳደር ስራ አይገባም፣ ሰላማዊ ሰዎችን በማሰር እና እስርቤቶችን በመጠበቅ ስራ አይሰማራም፡፡ የኮንትሮባንድ ስራን በመከላከል ይሁን በማንኛውም ከንግድ ስራ የተያያዘ ስምሪት ውስጥ እንዲገባ አይደረግም፡፡

ይህንን በማረጋገጥ ሰራዊቱ ከግዳጁ ውጪ በሆነ ስራ በማሰማራት ሲፈጠሩ የቆዩት የሰራዊቱንና የሕብራተሰቡን ግንኙነት በማበላሸት አስተዋጽኦ የሚያደረጉ ሁኔታዎች እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡

8.3. የሃገር መከላከያ ሰራዊት የሰው ሃይል እና አስተዳደር በሚመለከት የሚከተሉት ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል፤

8.3.1. በሁሉም እርከኖች የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረ ሰቦች ሚዛናዊ ተዋፅኦ የጠበቀ የሰው ሃይል እንዲኖረው ይደረጋል፡፡ በበላይ የመኮንኖች እርከን ያለው ያልተመጣጠነ ሁኔታ ብቃትን በጠበቀ መልኩ ተገቢው መስተካከል ይደረግበት ዘንድ ልዩ ተኩረት ይሰጠዋል፡፡

8.3.2. የአገር መከላከያ ሰራዊትን በመቀላቀል ለአገር ዳር ድንበር እና ሉኣላዊነት ጥበቃ የራስን ሕይወት ለመስዋእት ፈቃደኛ ሆኖ መገኘት ታላቅ አክብሮት ሊሰጠው የሚገባ አገልግሎት እንደመሆኑ፤ መንግስት ለተቋሙ አባላት የሚገባውን እንክብካቤ እና የመብት ጥበቃ ያደርጋል፡፡ አገልግሎቱ ለማንኛውም ብቃቱ ላለው ኢትዮጵያዊ

ክፍት ከማድረግ ባሻገር፤ የአባላቱ የስራ እና የኑሮ ዋስትና የሚጠበቅበት፤ የእድገት እና የሙያ ማሻሻያ እድል ከአድልዎ በጸዳ መልኩ ለሁሉም ክፍት የሚሆንበት፤ የሰራዊቱ ውስጣዊ መስተዳደር ሙያው የሚጠይቀው ደረጃ ያሟላ እና ፍትሃዊ የሚሆንበት ሁኔታ እውን እንዲሆን ይደረጋል፡፡

8.3.3. ወታደራዊ ሙያ አገርን እያገለገሉ ራስንም ቤተሰብንም የሚመሩበት ቋሚ የስራ ቅጥር መሆኑ ታውቆ የመለዮ ለባሹ ስራ ዋስትና ያለው መተዳደርያነቱ እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡ በሕግ በተደነገገ ወንጀል ከሚሰናበቱት በስተቀር ማንኛውም የሰራዊቱ አባል ከሰራዊቱ የሚሰናበተው በግልጽ በሚታወቅ የብቃት እና የአካል መመዘኛ፤ከፖለቲካ ወገንተኝነት እና አድልዎ በጸዳ መልኩ ይሆናል፡፡ የሚሰናበቱት አባላት ባለውለታነታቸው ታውቆ፤ ከተቋሙ የሚያገኙት ጥቅም እና ክብር ተጠብቆ፤ የሚዘልቅበት ስርአት ይደራጃል፡፡

8.3.4. በጦር ጉዳተኝነት የሚሰናበቱት የወደፊት ኑሮአቸው የተስተካከለ እና ለውርደት የማይዳርግ ይሆን ዘንድ ማጣት የሌለባቸውን ጥቅሞች ተለይቶ እንዲቀመጥ እና እንዲጠበቅላቸው ይደረጋል፡፡ በግዳጅ የወደቁ የሰራዊት አባላት ወራሾች ማግኘት ያለባቸውን ጥቅም እና ክብር እየተጠበቀ ክትትል የሚያደርግ ስርዓት በማደራጀት የአገሪቱ ባለውለታዎች የማይዘነጉበት ሁኔታ እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ □ንደዚሁም በምርኮ በጠላት □ፀ □□□ቁ □ሠራዊት አባላት ለሰብአዊ መብታቸውና ደህንነታቸው በዓለም አቀፍ ኮንቬንሽን መሠረት መጠበቃቸውን ለማረጋገጥ አስፈላጊው ሁሉ ይደረጋል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩትን በማከናወን የመለዮ ለባሹ ክብር እና ሞራል እንዲጠበቅ፣ የመላ ኢትዮጵያውያን አለኝታነቱ እንዲታወቅ ይደረጋል፡፡

8.4. የአገራችን መከላከያ ሰራዊት የአገሪቱን ስጋቶች፤ የአከባቢያችን ጂኦ ፖለቲካዊ ሁኔታዎች እና የአገሪቱን አቅም ባገናዘበ መልኩ እንዲገነባ፤ ሙያዊ ጥራቱ ወቅቱን የጠበቀ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ለዚሁም አስፈላጊው ጦር መሳርያ እና ድርጅት እንዲቀርብለት፤ ጥራት ያላቸው ማሰልጠኛ ተቋማት ኖሮውት በቀጣይነት ለግዳጁ የሚመጥን ብቃት እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

ለሰራዊቱ የሚያስፈልገውን ጦር መሳርያ እና ትጥቅ በአገር ውስጥ ለማምረት ይቻለን ዘንድ የመከላከያ ኢንዱስትሪያችን ትኩረት አግኝቶ እንዲያድግ ይደረጋል፡፡ የመከላከያ ኢንዱስትሪ ግንባታ ፕሮግራሙ የቅርብ ርቅት ስጋቶች ብቻ ሳይሆን የረጅም ጊዜ ስጋቶችንም ግምት ውስጥ ያስገባ እና ስጋቶችን የሚመጥን፤ ከማንኛውም ጥቃት ራስን ለመከላከል የሚያስችል እና በምርምር የተደገፈ እንዲሆን፤ ይደረጋል፡፡

8.5. ሕግ አውጪው ሃገርን መከላከል በሚመለከቱ ጉዳዮች ተገቢው ሚናውን ይጫወት ዘንድ የሚከተሉት ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል፤

8.5.1. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በህዝብ ወኪልነቱ በሃገር መከላከልና ሃገር ደህንነት ጉዳዮች ተገቢውን ቁጥጥር እና ክትትል ማድረግ ይቻለው ዘንድ አሁን ያለው የመከላከያ እና የውጭ ጉዳይ ኮሚቴ መልሶ እንዲቋቋም ያደርጋል፡፡ በቂ ስልጣን እንዲኖረው እና ግልጽና በተጨባጭ የሚለካ ብቃት ያላቸው የአባላት ጥንቅር እንዲኖረው ያደርጋል፡፡

8.5.2. ሕግ አውጪው በሕግ አስፈጻሚው የሚቀርቡለትን የሃገር መከላከያ እና ደህንነት ነክ ፖሊሲዎችን መርምሮ በማጽደቅ ብቻ ራሱን ሳይወስን፤ በገዛ ራሱም ለሃገር መከላከል እና ደህንነት አስፈላጊ ናቸው ያላቸውን

ፖሊሲዎች እና ሕጎች ያመነጫል ያጸድቃል። የሚወጡት ሕጎች እና ፖሊሲዎች አፈጻጸም ይከታተላል። አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም ምርመራ ያደርጋል።

8.5.3. የሃገር መከላከያ የግንባታ እቅዶችን እና ለዚህ የሚያስፈልገውን በጀት ያጸድቃል። የተመደበው ሃብት ከሙስና እና ከብክነት በጸዳ መልኩ ለታቀደለት አላማ እየዋለ መሆኑን ይከታተላል። ለመከላከያ ኢንዱስተሪ ግንባታ እና ለትላልቅ የጦር መሳርያ ግዢ ውሎችን ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ይከታተላል።

8.5.4. ከኢትዮጵያ ውጪ፤ ለሰራዊታችን የሚሰጥ ማንኛውም ግዳጅ ሕግ አውጪው አስፈላጊነቱን መርምሮ ከነማስፈጸምያ መመርያዎች ጋር እንዲያጸድቀው ይደረጋል፤ ከዚህ ውጪ የሚደረግ ስምሪት እንዳይኖር ይደረጋል። ከኢትጵያ ውጭ ግዳጆች ሲከናወኑ የአገሪቱን ብሄራዊ ጥቅም ማስጠበቃቸውን ያረጋግጣል። ለእንደዚህ ዓይነት ግዳጅ የሚሰማራው የመከላከያ ሃይል አስፈላጊውን ትጥቅ እና ድርጅት የቀረበለት መሆኑን እና መብትና ጥቅሙ የተጠበቀለት መሆኑን ያረጋግጣል።

8.5.5. ከውጪ መንግስታት ጋር የሚደረጉ ወታደራዊ ስምምነቶች፣ የውጭ ሃገር ሰራዊት በሃገራችን ውስጥ የሚሰፍርበት እና የሚንቀሳቀስበት ሁኔታ ቢኖር ሕግ አውጪው አስቀድሞ ያወቀው እና ያጸደቀው ብቻ ይሆናል።

8.6. ከሃገር መከላከል እና ደህንነት ጋር የተያያዙ የሕግ አስፈጻሚው የአመራር አካላት ስልጣን እና ኃላፊነት በግልጽ ተለይቶ እንዲቀመጥ በማድረግ ተጠያቂነት በግልጽ እንዲለይ ይደረጋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ የጦር ሃይሎች ጠቅላይ አዛዥ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የሃገሪቱን የመከላከያ እና ደህንነት ጉዳዮች የሚከታተል እና አስፈላጊ የሆኑትን የፖሊሲ እርምጃዎች የሚነድፍ የሃገር መከላከያ እና ድህንነት ምክር ቤት በሕግ እንዲቋቋም ይደረጋል። በዚህ የግድ መሳተፍ ያለባቸው ተቋማት እና ገለሰቦች ተለይተው ይቀመጣሉ። የመከላከያ ሚኒስትሩ ስልጣን እና ኃላፊነትም እንደዚሁ ተለይቶ ይቀመጣል። ሚኒስተሩ ሲቪል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለስራው የሚመጥን እውቀት እና ችሎታ ያለው እንዲሆን ይደረጋል።

የጠቅላይ ኤታ ማዡር ሹሙ ስልጣን እና ኃላፊነት ተለይቶ እንዲቀመጥ በማድረግ በሲቪል ስልጣናት እና በወታደራዊ ስልጣናት መሃከል ያለው ድንበር በግልፅ እንዲታወቅ ይደረጋል። የጠቅላይ ኤታ ማዡር ሹመት በሙያ ብቃት፣ ለሃገር እና ለሕገ መንግስቱ ባለው ታማኝነት የተመሰረተ እና የሰራዊቱን የሲኒየሪት ወግ መሰረት ያደረገ ይሆናል። ጠቅላይ ኤታ ማዡር የሚሾምበት እና ከስልጣኑ የሚለቅበት ሁኔታ በሕግ እንዲደነገግ ይደረጋል።

## 9. የኢሚግሬሽን እና ደህንነት ባለስልጣንን በተመለከተ

9.1. የኢሚግሬሽን እና የደህንነት ባለስልጣንም በሕግ አውጪው እይታ እና ክትትል እንዲገባ ይደረጋል። የሃገርንና የዜጎችዋን ደህንነትና ጥቅሞችን በማስጠበቅና መጠበቅ መርህ ላይ የተመሰረተ፤ ከፖለቲካዊ ወገንተኝነት የጸዳ እና የሙያ ጥራት ያለው የደህንነት ተቋም እንዲኖረን ይደረጋል። ለተቋሙ ስራ መነሻ የሚሆኑት

ፖሊሲዎች እና ማስፈጸሚያው መዋቅር ተመክሮባቸው እንዲወጡ እና በሕግ አውጪው ጸድቀው ስራ ላይ እንዲውሉ የደረጋል፡፡

9.2. የባለስልጣኑ ስልጣን እና ኃላፊነት በግልጽ በሕግ እንዲደነገግ ይደረጋል፡፡ የባለስልጣኑ ኃላፊ ሹመት በታወቀ መመዘኛ ላይ የሚመሰረት እና ሕግ አውጪው የሚያጸድቀው ይሆናል፡፡ የጠቅላይ ሚኒስትሩ አመራር እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ተቋሙ በሕገ መንግስቱ እና በተሰጠው ስልጣን ክልል የመስራቱ ኃላፊነት እና ተጠያቂነት የኃላፊው እንደሚሆን ይደረጋል፡፡ የስራው አፈጻጸም ሪፖርት ለሕግ አውጪውም የሚቀርብበት ሁኔታ እንዲኖር ይደረጋል፡፡

9.3. ለሃገር እና ለሕዝብ ደህንነት ተብሎ የሚደረግ መረጃን የመሰብሰብ እና ተጠርጣሪዎችን የመከታተል ስራ መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ይህ ስራ በሰበብ አስባቡ በዜጎች ግላዊ ነጻነት እና ግላዊ ሕይወት ውስጥ ጣልቃ መግባትን በማያስከትል፣ ፍርሃትን እና ሽብር በማይፈጥር መልኩ ይከናወን ዘንድ በሕግ የማይፈቀዱ ክትትሎች ተለይተው ይቀመጣሉ፡፡ በልዩ ሁኔታ የሚፈቀዱት ደግሞ ደረጃቸው እና ይህንኑ የሚፈቅደው አካል ማንነት በግልፅ በተደነገገበት መልኩ እንዲከናወን ይደረጋል፡፡

9.4. በባለስልጣኑ የሚደረግ ቅጥር፣ እድገት እና ተያያዥ ጉዳዮች ከፖለቲካ ወገንተንነት የጸዳ እና ሙያንና ለሃገር ደህንነት ተማኝነትን መሰረት ያደረገ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

### 10. ፖሊስን በተመለከተ

10.1. ከአገር ውስጥ መስተዳደር እና ጥበቃ ስራ የተያያዙ ወንጀልን የመከላከልና ወንጀለኛን የመያዝ ስራዎች በሙሉ በፖሊስ ስራ ውስጥ እንዲወድቁ እና ከእነዚህ ስራዎች በተያያዘ የሃገር መከላከያ ስራዊት ተሳታፊ እንዳይሆን ይደረጋል፡፡ እንደ ፌደራል ፖሊስና የፌዴፋል ማረምያ ቤቶች ፖሊስ ሁሉ እንደአስፈላጊነቱ የድንበር ጥበቃ ፖሊስ፣ የኢኮኖሚ (ፊናንስ) ፖሊስ፣ እንዲቋቋሙ ያደረጋል፡፡ ሁሉም ለስራው የሚያስፈልገውን እውቀት እና ክህሎት ኖሯቸው የተሰጣቸውን ግዴታ መፈጸም እንዲችሉ ይደረጋል፡፡ ማንኛውም የፖሊስ አካል ከፖለቲካ ወገንተኝነት በጸዳ ሙያን መሰረት ያደረገ አሰራር እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

10.2.የፌዴራል ፖሊስ ተልእኮ የዜጎችን ሰብአዊ እና ዴሞክራስያዊ መብቶች ሕጉ በሚደነግገው መሰረት መተግበራቸውን ማረጋገጥ እንጂ ዜጎች በእነዚህ መብቶች መጠቀማቸውን መከልከል እንዳልሆነ መሰረት ያደረገ ስራ እንዲሰራ ይደረጋል፡፡ ወንጀልን ለመከላከል እና ወንጀለኞችን ተከታትሎ ለመያዝ የሚያስችለው የሙያ ጥራት ያለው ሆኖ ተመጣጣኝ ብሄራዊ ተዋጽኦ እንዲኖሮውም ይደረጋል፡፡ እንዲሁም ለዚሁ የሚያስፈልገውን ትጥቅና ድርጅት እንዲኖረው ይደረጋል፡፡ ሕግ አውጪው በጸጥታ ተቋማት በኩል በዜጎች ላይ የሚፈጸሙ የሰብአዊና ዴሞክራስያዊ መብቶች ጥሰቶችን የሚከታተልበት ስርዓት እንዲኖረው ይደረጋል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው መርማሪ አካል በማቋቋም ማጣራት ያደርጋል፡፡

በክልሎችም የፖሊስ ተቋማት ከሚጠበቅባቸው ሕገ መንግስታዊ ኃላፊነት ውጪ የሆነ ድርጊት ላይ እንዳይሰማሩ፤ ይህ ለመሆኑም የክልል ምክር ቤቶች ክትትል እንዲኖር ይደረጋል፡፡

10.3. ሚልሽያም ሆነ ተጠባባቂ ጦር ከፓርቲዎች ፖለቲካ ገለልተኛ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

### 11. የውጭ ግንኙነት እና የአከባቢያዊ ሰላምን በተመለከተ

11.1. የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ እና አጠቃላይ ግንኙነታችንን በሚመለከት መድረኩ የሚከተሉት መመርያዎች ይኖሩታል፤

11.1.1. የአገራችን የውጭ ግንኙነት የአገርን ጥቅም ማእከል ያላደረገ እና የረጅም ጊዜ ራዕይ የሌለው ሆኖ ቆይቷል፡፡ ሚኒስቴር መስርያ ቤቱ ለሚጠበቅበት ድርሻ የሚመጥን የሙያተኛ ጥንቅር ሊያካብት አልቻለም፡፡ በሚኒስቴር መስርያ ቤቱ ያለው ሹመት የሚሰጥበት ስርኣት ለአገራዊ ጥቅም ያለ ታማኝነት፤ ሙያ እና ልምድ ያደረገ ሳይሆን ለፓርቲ እና የበላይ ባለስልጣናት ባለ ታማኝነት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጪ ያለውን የመስሪያ ቤቱ ተአማኒነት እና አጠቃላይ ገጽታው የተበላሸ እንዲሆን አድርጎታል፡፡

በዚህ መልኩ የተበላሸው የአገሪቱ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ተገቢው የማሻሻያ ለ□ሁዓ □□ረፅበ□ል፡፡ □□ሁጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ከፍተኛ ሹማምንት እና የአምባሳደሮች ሹመት በአለምአቀፍ መድረኮች የኢትዮጵያን ጥቅም በብቃት ሊያስጠብቁ፣ ሊወክሉ እና ሊያንጸባርቁ የሚችሉ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

11.1.2. የሃገራችን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ በአካባቢያችን እየተደቀኑብን ያሉትን ስጋቶች በሚገባ የተገነዘበ፤ ከዚሁ አንጻርም የአገራችንን ጥቅም በሚገባ ለማስጠበቅ የሚያስችል እንዲሆን ይደረጋል፡፡

11.1.3. ሃገራችን ኢትዮጵያ የአፍሪካ አንድነት ግምባር ቀደም መስራች፤ አፍሪቃውያን ለነጻነት ያደረጉትን ተጋድሎ ተምሳሌት መሆኗ ይታወቃል፡፡ በዚሁ ስሟ እና ታሪኳ ምክንያትም የአፍሪካ ሕብረት እና የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን መቀመጫ ለመሆን መብቃትዋ ይታወቃል፡፡

እንደድሮው ሁሉ በአሁኑ ዘመንም ኢትዮጵያ የጥሩ አፍሪካዊነት ተምሳሌት ሆና መገኘት ይኖርባታል፡፡ በመሆኑም ሃገራችን ኢትዮጵያ ሰብአዊ እና ዴሞክራስያዊ መብቶች የተከበሩባት፤ ስልጣን በነጻና ፍትሃዊ ምርጫ ብቻ የሚያዝባት፤ የሕግ የበላይነት የሰፈነባት፣ ነጻነት የተላበሰ ሰላም እና ውስጣዊ መረጋጋት የሰፈነባት አገር እንድትሆን እንሰራለን፡፡

11.1.4. አገራችን ኢትዮጵያ በአለም ከታወቁት እጅግ ድሃ ሃገሮች አንዷ እንደሆነች እና ከዚሁ ለመውጣት ከፍተኛ የውጭ እርዳታ እንደሚያስፈልጋት ይታወቃል፡፡ ይህ ሊሆን ከቻለባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ የውስጥ ፖለቲካዊ ችግሮችዋን በሰላም እና በዴሞክራሲ ለመፍታት ባለመቻልዋ ነው፡፡ አገራችን ከድህነት እና ከውጪ እርዳታ ጠባቂነት ትወጣ ዘንድ ዋና መፍትሄው ኢትዮጵያውያን እውቀታቸውን፤ ሃብታቸውን እና መላ ቀልባቸውን ለሃገራቸው ልማት እንዲያውሉ የሚያደረግ የተመቻቸ የፖለቲካ እና የፖሊሲ ሁኔታ መፍጠር እንደሆነ መድረኩ ያምናል፡፡

ይህ እንደተጠቀ ሆኖ ሃገራችን የአለም አቀፉ ማህበረ ሰብ አካል መሆንዋን እና አለማቀፋዊ ሁኔታውን ያጤነ፤ ከዚሁ ተጠቃሚ እንድትሆን የሚያደርግ፣ አቅሟ የፈቀደውን ያክል በጎ አስተዋጽኦዋን ለማበርከት የሚያስችላት፤ የውጪ ግንኙነት እንዲኖራት ይደረጋል፡፡

11.1.5. ከሌሎች አገሮች እና መንግስታት ጋር የምታደርገው ገንኙነት በጋራ ጥቅም፣ በእኩልነት፣ በመከባበር እና በእርስ በርስ የውስጥ ጉዳዮች ጣልቃ ባለመግባት መርሆች ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡

## 11.2. ከጎረቤት ሃገሮች ጋር ያሉትን የድንበር ጉዳዮች በሚመለከት

11.2.1. ኢትዮጵያ ከጎረቤቶችዋ ጋር ያላትን ድንበሮች ሁሉ በሚገባ ለመለየት ከሁሉም ከሚመለከተው ጎረቤት ሃገሮች ጋር በአጠቃላይ ድርድር እናካሄዳለን

11.2.2. የአልጀርስ ስምምነት የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም የማያስከብር ስለሆነ ስምምነቶቹን እንቃወማለን፡፡ የኤርትራ መንግስት በፈጠረው አስቸጋሪ ሁኔታ የተባበሩት መንግስታት የሰላም አስከባሪ ሃይል እንዲወጣ በተደረገበት፤ይብሱኑ ደግሞ የኤርትራ ሰራዊት የሰላም ቀጠናውን በተቆጣጠረበት እና የኤርትራ መንግስት በኢትየጵያ ላይ የሚያደረገውን የጠብ አጫሪነት ተግባር ባላቆመበት ሁኔታ የኢህአዴግ መንግስት ስምምነቱ በኤርትራ በኩል መፍረሱን እና ራሱን ከዚሁ ስምምነት ለማግለል አለመወሰኑ አሁንም ባለፈው ከፈጸማቸው ስህተቶች ለመማር እና ለማረም ዝግጁ አለመሆኑኑ ያመለክታል፡፡ መድረኩ ስምምነቱ ስህተት በመሆኑ እና በኤርትራ እንደተጣሰ በመገንዘብ ከኤርትራ ጋራ  እንደአዲስ በመደራደር ሌላ እና የሁለቱን አገሮች ጥቅሞች እና ስጋቶች ግምት ውስጥ ያስገባ ሁሉን አቀፍ ስምምነት ላይ ለመድረስ አስፈላጊ መሆኑን በማመን ለዚሁ እውን መሆን አጥብቆ ይሰራል፡፡

11.2.3. የኢትዮጵያና የሱዳንን የቀድሞ መንግስታት ስምምነቶች እና የሁለቱ ሃገሮች ሕዝቦች በአካባቢው የነበራቸውን ይዞታዎች በተክክል ያገናዘበ ዘላቂ መፍትሄ እንዲያገኝ ድርድር ማድረግና ይህም በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ታውቆና ይሁንታ አግኝቶ ሊሰራበት እንደሚገባ እናምናለን፡፡

## 11.3. የባህር በርን በተመለከት

11.3.1. ከዓለም አቀፍ ሕግጋትና ከታሪክ አንጻር አገራችን ራስዋ ባለቤት ሆና የምታስተዳድረው የባህር በር እና መተላለፍያ (ኮሪዶር) የማግኘት መብት እንዳላት መድረኩ ይገነዘባል፡፡ ከአካባብያችን እና ከሃገራችን ልዩ ሁኔታ አንጻር ሲታይ ደግሞ ይህን መብት የማስከበር ጉዳይ የኢኮኖሚ እድገት ብቻ ሳይሆን የሃገር ደህንነት እና የሃገር ህልውና ጉዳይ መሆኑን ይገነዘባል፡፡ ሆኖም የኢህአዴግ መንግስት ይህን ኢትዮጵያ በአሰብ ወደብ ላይ ያላትን ከታሪክ፣ከአለምአቀፍ ሕግጋት እና ከፍትሃዊነት አንጻር የባለቤትነት መብቷን ሳያስከብር ቀርቷል፡፡ ይህም በመሆኑ ሃገራችን ወደብ አልባ በመሆንዋ ምክንያት በአስጊ ኢኮኖምያዊና የጽጥታ ችግሮች ውስጥ እንድትገባ አድረጓል፡፡

11.3.2. ሃገራችን በአሁኑ ጊዜ የወደብ ባለቤትነት ባለመሆና በወደብ አገልግሎች አጠቃቀም ዙርያ እያጋጠምዋት ያሉትን ችግሮችም በውል ይገነዘባል፡፡

በመሆኑም

1.1.3.3. መድረኩ የአሰብ ወደብ ለኢትዮጵያ የምትገባ የባህር በር መሆኗን በመገንዘብ ሰለማዊና ሕጋዊ በሆነ አግባብ ዲፕሎማሲያዊ ትግሉን ያካሂዳል፡፡ በዚሁ ጉዳይ ከኤርትራ ጋር የጋራ ጥቅምንና ዓለም ዓቀፍ ሕግጋትን መሰረት ያደረገ ሰላማዊና ሕጋዊ ድርድሮች ማካሄድና ዘላቂ ስምምነት ላይ መድረስ እንደሚገባም በጽኑ ያምናል፡፡ ለዚህ ስኬትም ኢትዮጵያውያን በዲፕሎማሲያዊውና ሰላማዊው ትግል በጽናት እንዲቆሙ ያለመታከት ይሰራል፡፡ ኤርትራውያን ከዚህ ጋር በተያያዘ ሊኖራቸው የሚችለውን ስጋት ለመቅረፍ እና ሁለቱም ወገኖች ተጠቃሚ ሆኖው የሚወጣበትን የመፍትሄ አማራጮችን ያፈላልጋል፡

1.1.3.4. ከአጭር ጊዜ አንጻርም የምንጠቀምባቸውን የወደብ አገልግሎት አማራጮች እንዲሰፉ ለማድረግ ወደብ ካላቸው ሁሉም ጎረቤት ሃገሮች ጋር ያለንን ግንኙነት ማሻሻልና ድርድሮችን አካሂዶ ስምምነቶች ላይ መድረስ አንገብጋቢ መሆኑን ያምናል፡፡

## 11.4 የወሰን ተሻጋሪ ወንዞችን በሚመለከት

11.4.1. በአባይ ወንዝ ላይ፤ በተለያዩ የጎረቤት መንግስታት እና በኢትዮጵያ መንግስታት መካከል፤ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም በአግባቡ የሚያስጠብቁ ስምምነቶች አለመኖራቸውን በመገንዘብ፤ ለሃገራችን ሆነ ለጎረቤቶቻችን ፍትሃዊ የውሃ ሃብት አጠቃቀም የሚያረጋግጡ ድርድሮች በጥልቀት እንዲካሄዱና ፍትሃዊ ስምምነቶች እንዲፈረሙ ተግተን እንሰራለን፡፡

በሌሎች ወሰን ተሻጋሪ ወንዞች ላይም እንደአባይ ሁሉ ተገቢ ትኩረት ሰጥቶ መደራደር የሚገባ መሆኑን እናምናለን፤ ለዚህ ተግባራዊነትም ተግተን እንሰራለን፡፡

11.4.2. ኢትዮጵያ ወንዞቹ የሚፈልቁባት አገር እንደመሆንዋ መጠን ኢትዮጵያም እንደነርሱ የሚገባት ያህል ድርሻ የመጠቀም ተፈጥሮአዊ መብት ያላት ስለሆነ በድህነትዋ በማሳበብ ሆነ በሃይል በማስፈራራት የተጠቃሚነት መብትዋን የሚጻረር አካሄድ ለሁሉም እንደማይበጅ እናምናለን፡፡ ስለዚህም ኢትዮጵያ ወንዞችዋን መጠቀም ለቅራኔዎች ሳይሆን ለትብብርና ለጋራ ልማት እንቅስቃሴዎች መሰረት እንዲሆን የበኩላችንን ጥረት እናደርጋለን፡፡

11.4.3. ወንዞቹ በሁሉም አቅጣጫ ወደአሉት ጎረቤቶቻችን ስለሚፈሱና ከግንዛቤ ማጣትም ሆነ የራስን ጥቅም ብቻ ከማራመድ የሚነሱ አለመግባባቶች ግጭቶች እንዳይከሰቱ እየተከላከልን፤ መሰረታዊ የሕዝባችንን ጥቅም አሳልፈን ሳንሰጥ እና ወንዞቹን አቅማችን በፈቀደ ደረጃ እየተጠቀምን፤ ከሚመለከታቸው ወገኖች ጋር መደራደሩንና በሁኔታዎች ላይ ትክክለኛ ግንዛቤ ማስጨበጡን በሰፊው እንገፋበታለን፡፡

# Ìv፡ ክፍል ሁለት፡ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች

## 12. አጠቃላይ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችን በተመለከተ

### 12.1 የተመጣጠነ (balanced) የኢኮኖሚ ልማት ፖሊሲን መከተል፣

- ላለፉት 18 ዓመታት አገራችን ስትመራበት የቆየው ግብርና መር ኢንዱስትሪያዊ ልማት ፖሊሲ በአጠቃላይ ሲታይ ሀገራችንን ከምግብ እጥረት እንኳ ያላላቀቃትና ከፍተኛ መጠን ያለው የምግብ ሰብል ከውጭ እንድታስገባ ያስገደዳት በመሆኑ፣

- ፖሊሲው በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎቻችንን ለከፋ ረሃብና ችግር ያጋለጠና ለእልቂት የዳረገ በመሆኑ፣

- ፖሊሲው በከተማ ብቻ ሳይሆን በገጠርም ከፍተኛ ሥራ አጥነትንና የኑሮ መመሰቃቀልን ማስከተሉ፣

- ግብርናው የኢንዱስትሪውን ልማት ሊመራ ቀርቶ በከፍተኛ መጠን እየጨመረ ያለውን ያገሪቱን ህዝብ እንኳ ለመመገብ ያለመቻሉ፣

-ግብርናው ከፍተኛ ተረፈ ሀብትን ማመንጨት ቀርቶ ራሱም ከፍተኛ ዕግዳት (Stagnation) ውስጥ ዘቅጦ መገኘቱ፣

- አሁን አገራችን ባለችበት ዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ቀርቶ በአደጉትና ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በሚጠቀሙ አገሮች እንኳ ግብርና ከሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች በሚገኝ ገቢ እየተደጎመ ባለበት ሁኔታ ኢንዱስትሪውን ይመራል የሚል አቅጣጫ የተሳሳተ መሆኑ፣

አማራጭ የፖሊሲ አቅጣጫ እንድንከተል የግድ ይላል፡፡ ስለሆነም ይህን የተሳሳተ የኢኮኖሚ ልማትና የዕድገት አቅጣጫ በመተካት የተመጣጠነ (balanced) የኢኮኖሚ ልማትና ዕድገት ፖሊሲን ተግባራዊ እናደርጋለን፡፡ በዚህ መሠረትም፣

12.1.1 የአገራችን ግብርና አሁን ከገባበት ከፍተኛ ቀውስ ተላቆ ምርታማነቱ እንዲጨምር በማድረግ አስተማማኝና ዘላቂ ዕድገት የሚያሳይበትን ሁኔታ ለመፍጠር እንሠራለን፡፡ ይህን እውን ለማድረግም ግብርናውን አሁን ከሚጠቀምበት ኋላ ቀር ቴክኖሎጂ አላቅቀን ዘመናዊ ቴክኖሎጂን ተጠቃሚ እናደርገዋለን፡፡ ለግብርናው ግብአት የሚሆኑ እንደ ማዳበሪያና ምርጥ ዘር ያሉትን ተወዳዳሪ በሆነ ዋጋ በአገር ውስጥ የሚመረቱበትን ሁኔታ እንፈጥራለን፡፡ ግብርናው ከዝናብ ጥገኝነት ተላቆ የመስኖ ልማት በከፍተኛ ደረጃ የሚስፋፋበትን ሁኔታ እናመቻቻለን፡፡ በቁጥር ላይ ያተኮረ ሳይሆን ከፍተኛ የእንስሳት ተዋጽኦ ምርቶችን ሊያስገኙ የሚችሉ የእንስሳት ሀብት ልማት ተግባራዊ እናደርጋለን፡፡

12.1.2 በኢንዱስትሪው ዘርፍም ከግብርና ክፍለ ኢኮኖሚው ጋር የግብአት አቅርቦት ጥብቅ ቁርኝት ያለው ማለትም ከግብርና ግብአቶችን የሚቀበል ብቻ ሳይሆን ለግብርና ግብአቶችን የሚያቀርብ ኢንዱስትሪ በአገራችን በማስፋፋት እርስ በእርሱ የሚደጋገፍ ኢኮኖሚ የመገንባት ፖሊሲን እንከተላለን፡፡ ከአግሮ-ፕሮሰሲንግ በተጨማሪ አዋጭነታቸው እየታየ የብረታ ብረትና የኬሚካል የመሳሰሉት ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ እናደርጋልን፡፡ በማዕድን ጥናትና ልማት ሥራዎች ላይም ትኩረት ሰጥተን እንሠራለን፡፡ በልማት ሂደት ከፍተኛ ሚና የሚጫወተውና ለበርካታ ወገኖች የሥራ ዕድል የሚከፍተው የኮንስትራክሽን ዘርፍም ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት እንዲስፋፋ ይደረጋል፡፡

12.1.3 ከግብርናና ኢንዱስትሪ በተጓዳኝ ለበርካታ ዜጎች ሥራ በሚያስገኙና ልማቱን በሚያፋጥኑ የአግልግሎት ዘርፎች ትኩረት ሰጥተን እንንቀሳቀሳለን፡፡ በዚህ መሠረትም እንደ ቱሪዝም፣ ፋይናንስ፣ መገናኛ፣ መጓጓዣና ንግድ የመሳሰሉ አገልግሎቶች ላይ ልዩ ትኩረት ሰጥተን እንሠራለን፡፡ የአገልግሎት ዘርፉ በተቀናጀ መንግድ የግብርናውንና የኢንዱስትሪውን ልማት እንዲረዳ በማድረግ ይቀየሳል፡፡ እንዲሁም ግብርናና ኢንዱስትሪ የአገልግሎት ዘርፉን የሚያጠናክሩበት አቅጣጫ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

### 12.2 መንግሥት በልማት የሚኖረውን ሚና በተመለከተ

- አሁን መንግሥት እያራመደ ያለው ልማታዊ መንግሥት የሚለው ንድፈ ሐሳብና ፖሊሲ ገዥው ፓርቲ ኢኮኖሚውን ለመቆጣጠርና በዚሁም ኅብረተሰቡን ለመቆጣጠር የተቀየሰ ስልት ሰለሆነ ዘላቂ ዕድገትና ልማት ያረጋግጠል ብለን ስለማናምን
- የልማታዊ መንግሥት ፖሊሲ ገዥው ፓርቲ የሥልጣኑ መሠረት ይሆናሉ የሚላቸውን ወገኖች በተለየ የሚያጠናክርብት አቅጣጫ በመሆኑ
- ፖሊሲው ዜጎችን በዜግነታቸው ተመልክቶ በልማት የሚያሳትፍ ሳይሆን ደጋፊዎችን ልማታዊ በማለት የሚቃወሙትን ደግሞ ጥገኛና ኪራይ ሰብሳቢ ብሎ በመፈረጅ በመካከላቸው ልዩነቶችን የሚፈጥር በመሆኑ
- ገዥው ፓርቲ በሕጋዊ መንገድ የዜግነት መብታቸውን ተጠቅመው ለሚንቀሳቀሱ የሀገር ውስጥ ባሀብቶች አድሎ በማድረግ ከፓርቲው ጋር የተለየ ቁርኝት ያላቸውንና አባላቱን በተለየ ሁኔታ የሚጠቅም ሲሆን ገዥውን ፓርቲ አይደግፉም ብሎ

የሚጠረጥራቸውን ግን በቁጥጥሩ ሥር ያለውን መሬትና የብድር አገልግሎት በመከልከል በአገር ውስጥ ባለሀብቶች ተሳትፎ ላይ አሉታዊ ተፅኖ በማሳደር ላይ መሆኑና ይህ አድሎአዊ አያያዝ በፍጥነት መስተካከል የሚገባው መሆኑን በማመን፣

- በልማታዊ መንግሥት ፖሊሲ መሠረት ገዥው ፓርቲ የራሱን የንግድ ተቋማት የተለያዩ ሰሞች እየሰጠ በሕገ ወጥ መንገድ በኢኮኖሚው እንቅስቃሴ የሚያደርገው አድሎኦ የተሞላበት አካሄድ መሆኑን በመገንዘብ፣

አሁን መንግሥት እየተጫወተ ያለውን ሚና በመለወጥ አማራጩን እንደሚከተለው እንዲሆን እናደርጋለን።

12.2.1 መንግሥት ዜጎች በልማት መስክ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የተለያዩ ስልቶችን ቀይሶ ያበረታታል። ለሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ከአድሎ ነፃ የሆነ ድጋፍ እንዲደረግ ይሠራል ። በተለይ ባለሀብቶችንና አነስተኛ ተቋማትን በመርዳት ረገድ ሃለፊነቱን መወጣት ይኖርበታል ብሎ ያምናል ። የአገራችን ባለ ሀብቶች ከሌላው ዓለም ባለሀበት ጋር ተወዳዳሪ ሆነው የሚወጡበትንና የልማት ተነሳሽነታቸው የሚጎለብትበትን ስልት በመቀየስ ድጋፍ ይሰጣል ።

12.2.2 የውጭ አገር ባለሀብቶች የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች ሊሸፍኗቸው በማይችሉ ከፍተኛ የልማት ፕሮግራሞች እንዲሳተፉ የሚያበረታታ ይሆናል። ይህም የአገራችንን ብሄራዊ ጥቅም በሚያስጠብቅና በማይጎዳ መልኩ እንዲሰፋፉ መበረታታት ይገባዋል ብሎ መድረኩ ያምናል።

12.2.3 መንግሥት ለዘላቂ ልማታችን ስትራተጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸውና የግል ባለ ሀብቶች ደፍረው በማይገቡባቸው ከባድ ኢንዱስትሪዎችና ሌሎች የመሠረት ልማት አውታሮች ልማቶች ላይ መሳተፍ የሚገባው መሆኑን መድረኩ በጽኑ ያምናል፤ ሆኖም የግል ባለ ሀብቶች መሳተፍ ሲጀምሩ ዘርፉ ለነእርሱ በማስተላለፍ የሚከናወን ይሆናል።

12.2.4 ገዥው ፓርቲ ራሱ ኢንደውመንትና ሌሎች የተለያዩ ሰሞችን እየሰጠ ከሚያንቀሳቅሳቸው የኢኮኖሚ ተቋማት እጁን እንዲያስወጣ እናደርጋለን። ማንኛውም ፓርቲም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የሀብት ማፍሪያ ተቋም ባለቤት እንዳይሆን ይደረጋል።

## 12.3 የኢኮኖሚው ቀውስና መፍትሔዎቹ በተመለከተ

መንግሥት አገራችን በከፍተኛ የዕድገትና ልማት ሂደት ላይ ትገኛለች ቢልም በተጨባጭ በአገራችን ከፍተኛ የኢኮኖሚ ቀውስ ሰፍኖ ይገኛል። ለዚህ ማስረጃ የሚሆነውም፣

- ሥራ አጥነት በከፍተኛ ደረጃ በከተሞች መንሰራፋቱ ብቻ ሳይሆን በገጠሩ የግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ውስጥም የእርሻ ቦታ በማጣት ከፍተኛ ሥራ አጥነት መፈጠሩና የሥራ አጡ ቁጥር ከዕለት ወደ ዕለት እተበራከተ መሆኑ
- በአገሪቱ የተፈጠረው ከፍተኛ የዋጋ ንረት ከተሜውን በቻ ሳይሆን ገጠሩንም ጭምር ከፍተኛ ችግር ውስጥ የከተተው መሆኑ
- የወጪና የገቢ ንግዳችን ሚዛን በከፍተኛ ደረጃ መዛባቱና ይህን ተከትሎም የውጭ ምንዛሪ እጥረት ተከስቶ አገራችን ከውጭ በምታስገባቸው ጥሬ ዕቃዎች፣ መሠረታዊ የፍጆታ ዕቃዎችና የማምረቻ መሠሪያዎች ላይ ከፍተኛ ተጽኖ በማሳደሩ ኢኮኖሚው ለከፍተኛ የዋጋ ንረትና ለጥቁር ገበያ መጋለጡ
- የሀገራችን ገንዘብ የመግዛት ዓቅም በዓለም ዓቀፍ ደረጃ ብቻ ሳይሆን ከጎረቤቶቻችን የአፍሪቃ አገሮች ገንዘቦች ጋር የነበረው የምንዛሬ ምጣኔ ዓቅም ጭምር በጣም የወረደበት ሁኔታ ውስጥ የከተተን ሰለሆነና በዋጋ ንረቱና በሀብት ይዞታ ላይ ተጽኖ አያሳደረ መሆኑ
- ኢኮኖሚው በአግባቡ አለመሥራቱና ሥርዓቱ በከፍተኛ አስተዳደራዊ ብልሹነትና በሙሰና በመዘፈቁ በኢኮኖሚው ቀውስ ላይ የበኩሉን ከፍተኛ ተጽኖ ማሳደሩ
- ምርታማነት ባለመታየቱና ኢኮኖሚው በአግባቡ ባለማደጉ ምክንያት ለዋጋ ንረትና የኢኮኖሚ ቀውስ መባባስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጉ
- የተፈጠረው የኢኮኖሚ ቀውስ በመንተራስ በጣት ሚቆጠሩ እጅግ እየበለጸጉና የሀገሪቱን ሀብት እየጠቀለሉ ሲሄዱ ብዙሀኑ የገጠር ይሁን የከተማ ኗሪ ግን ቀውሱን ተቋቁሞ ህይወቱን ለማቆየት እንኳ አሰቸጋ ሁኔታ ተፈጥሮ በሥቃይ ላይ መሆኑ

የተከሰተውን ቀውስ ለመግታት የተሻለ ፖሊሲ መቀየስ ለአገራችን ዘለቄታዊ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት ወሳኝ መሆኑ አምነንበታል። በዚህ መሠረትም

### 12.3.1 በአገራችን ስላለው የዋጋ ንረትና የኢኮኖሚው ቀውስ ገዥው ፓርቲ የሚያቀርባቸው ምክንያቶች ከእውነታው የራቁና መፍትሔ ሊያስገኙ የማይችሉ

በመሆናቸው የአገራችንን ማክሮ ኢኮኖሚያዊና አጠቃላይ ኢኮኖሚውን በሚገባ በማጤን ነጻ በሆኑ ምሁራን አማካይነት በሚደረጉ ጥናቶች ላይ የተመሠረቱና የተቀናጁ የፖሊሲ እርምጃዎች እንወስዳልን፡፡

12.3.2 የእርሻ ክፍለ ኢኮኖሚውን ከማሳደግ ባሻገር የተለያዩ ገቢ የሚያስገኙና ሰፊ የሰው ኃይል የሚያሳትፉትን የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፎችን እናስፋፋለን፡፡ የከተማ ልማትና የሥራ አጦችን ችግሮች በከተማ ውስጥ ለመቀነስ ገዥው ፓርቲ ቀጣይነት በሌላቸውና ለአጭር ጊዜ ፖለቲካዊ ጠቀሜታ ብቻ ብሎ የሚያካሂዳቸውን እንቅስቃሴዎች ዓይነት ሳይሆን የገጠርን ትናንሽ ከተሞች፣ የወረዳ፣ የዞንና የክልል ከተሞች ልማት በማፋጠን ቀጣይነት ያላቸው የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ማዕከላት እንዲሆኑ ለማድረግ እንሠራለን፡፡

12.3.3 ልማቱ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ያሉትን ዜጎች ሕይወተ በማሻሻል ትኩረት የሚሰጥ እንጂ አሁን እንደሚታየው ከኑራቸው የሚያፈናቅላቸውና ተገቢ ጥበቃ የማያደርግላቸው እንዳይሆን ትኩረት ሰጥተን እንሠራለን፡፡

12.3.4 የከተሞች መሠረተ ልማት በተለይ የውኃ፣ የኤሌክትሪክና የመንገድ መሠረተ ልማቶች በአንስተኛ ወጪና ረጅም አገልግሎት ሊሰጡ በሚችሉ የመንገድ ሥራዎችና ሌሎችም የመሠረተ ልማት ሥራዎች ማስፋፋት፣ ከገጠር የእርሻ ውጤቶችና ጥሬ ዕቃዎችን ወደ ከተሞች ለማምጣትና የኢንዱስትሪ ውጤቶችም ወደ ገጠር መንደሮች ለማዳረስ የሚችሉ መገናኛ መንገዶችን ለማስፋፋት እንሠራለን ፡፡ በዚህም መሰረት አሁን ከመሬት ጥበትና በህዝብ ቁጥር መጨመር ምክንያት ወደ ትላልቅ ከተሞች የሚፈልሰው የሰው ኃይል በአካባቢው ከተሞች የሥራ መስኮችን በመፍጠር ላይ ያተኮረ የልማት ስትራተጂ ሥራ ላይ እንዲውል እናደረጋልን፡፡ የከተሞች ልማትም በፕላን የተመሠረት እንዲሆን እናደርጋለን፡፡

12.3.5 በአገራችን ለልማት ፀር የሆነውን ሙሰና በቁርጠኝነት በመዋጋት በኢህአዴግ መንግሥት ብልሹ አስተዳደር ምክንያት በተለይም በኮንስትራክሽን ሥራዎች፣ በማዕድን ኮንሰሽኖች፣ በጨረታ ውሎች፣ በመሬት አጠቃቀም፣ በጉምርክ አገልግሎት፣ ወዘተ. በከፍተኛ ደረጃ ተንሰራፍቶ የሚገኘውን ሙስና ለመቆጣጠር ጠንክረን እንሠራለን ፡፡

## 12.4 **የባህር በር ባለቤት ባለመሆናችን በኢኮኖሚያዊ ልማታችን ላይ የሚያደርሰውን ተጽኖ መቋቋምን በተመለከተ**

የባህር በር ባለቤት ባለመሆናችን በኢኮኖሚ ዕድገታችን ላይ ከፍተኛ ተጽኖ እየደረሰ ይገኛል፡፡ በተደጋጋሚ በሚደረጉ የታሪፍ ጭማሪዎች የተነሣ ከውጭ የምናስገባቸው ሸቀጦች ዋጋ ከፍ ከማለቱ ባሻገር ዋስትናውም አስተማማኝ ሊሆን አልቻለም፡፡ በሀገር ውስጥ ተመርተው ወደ ውጭ የሚላኩት ዕቃዎችም ተወዳዳሪ እንዳይሆኑ እያደረጋቸው ይገኛል፡፡ ይህን የአገራችንን አስቸጋሪ ሁኔታ በማገናዘብ የሚከተለው ፖሊሲ ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ መሆኑን መድረኩ ያምናል፡፡

የሀገር ውስጥና የአካባቢያዊ ኢኮኖሚ ትስስሮችን በማስፋፋት ረገድ የመንገድ ሥራ ብቻ ሳይሆን የክልል ከተሞችን እርስ በእርስ የሚያገናኙና የአገር ውስጥ ንግድን የሚያጠናክሩ የባቡር ሀዲደ መገናኛ መሥመሮችን የመገንባትና የኤሌክትሪክ ኃይል የሚጠቀሙ ባቡሮችን ቶሎ አገልግሎት ላይ ማዋል ፡፡

እነዚህም መገናኛዎች በወደብ አገልግሎት ብቻ ሳይሆን በመሬት ከምናዋስናቸው ጎረቤት አገሮች ጋር በምናደርገው የንግድ ግኑኙነትም ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ ማድርግ ፡፡ በዚህም የውጭ ንግዳችን በርቀት ባሉ አገሮች ጥገኝነት እንዳይወሰንና የሀገር ውስጥና የአካባቢያዊ ራስን መቻል መርህ እንዲስፋፋ ማድረግ እንደሚገባ በመገንዘብ እንሠራለን ፡፡

## 12.5 **የበረሃነት መሰፋፋት፣ የተፈጥሮ ሃብት መከላትና የአካባቢ ብከላን መከላከል በተመለከተ**

የበረሃማነት መስፋፋትና የተፈጥሮ ሀብት መከላት በልማታችን ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽኖ እያሳደረ ይገኛል፡፡ ደኖች በከፍተኛ ደረጃ እየተራቆቱና መሬት በከፍተኛ ደረጃ እየተሸረሸረ በመሄዱ ለእርሻ አመችነት የነበራቸው አካባቢዎች ወደ በረሃማነት እየተለወጡ በመሄድ ላይ ናቸው፡፡ ምንጮች እየደረቁ ለሰውና ለእንስሳት የሚሆን ውኃ እያጠረ በመሄድ ላይ ነው፡፡ የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተም ብቁ ክትትልና ቁጥጥር ስለማይደረግበት ለም መሬቶችና ምንጮች በኬሚካሎች እየተበከሉ ከጥቅም ውጭ እየሆኑ ይገኛሉ ፡፡

ይህን አሳሰቢ ክስተት ለመግታትና በተቻለም ለመለውጥ በስፋትና በተቀናጀ መንገድ መሥራት ተገቢ እንደሆነ እናምናለን፡፡ በመሆኑም

12.5.1 የበረሃማነትን መስፋፋት ለመግታትና የተፈጥሮ ሀብትን ከውድመት ለመከላከል በተለይ እጅግ እየባከነ የሚገኘውን የአፈርና የውሃ ሀብት በቀጣይነት ለመንከባከብና ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችሉ እርምጃዎች ህዝቡን በሚያሳትፍና በተጨባጭም ከልማቱ ከፍተኛ ተጠቃሚ በሚሆንበት መልኩ የደን ልማትና የአፈርና ውሃ ጥበቃ ስትራተጂ ተቀይሶ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል ፡፡

ገበሬው በውኃ ተሸርሽረው በተጎዱ የእርሻ መሬቶች ላይ የመሬት ባለቤት ሆኖ የእርከንና የደን ልማት ሥራዎች እንዲያካሂድና ራሱም ቀጥተኛ ተጠቃሚ እንዲሆን ተገቢውን እገዛና ማበረታቻ ይደረጋል፡፡

12.5.2 ለዕርዳታ የሚሰጠውን ሀብት ለአካባቢ ጥበቃና ለዘላቂ ጥቅሞች በማዋል ፋንታ ለጊዚያዊ የፖለቲካ ጠቀሜታ ደጋፊዎችን ለማሰባሰብ ብቻ በመጠቀም የሚፈፅመውን የሀብት መባከን በማስወገድ የሴፍቲኔትና የዕርዳታ ሀብት ለተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤና ለእሴት መፍጠሪያ እንዲውል ትኩረት ሰጥተን እንሠራለን ፡፡

12.5.3 በገጠርም ሆነ በከተማ የደን ሀብት ለማገዶና ለከሰል በብዛት ጥቅም ላይ እንዲውል በመደረጉ በደን ሀብታችን ላይ እየደረሰ ካለው ጉዳት ለመታደግ እንደ ንፋስና የጸሐይ ብርሃን የመሳሰሉ አማረጭ የኃይል ምንጮች በአገራችን ውስጥ የሚመረቱብትንና በተመጣጣኝ ዋጋ ለህዝብ እንዲቀርቡ የሚደረግበትን ስልት ቀይሶ ሥራ ላይ ማዋል ስለሚገባ ይህን በተጠናከረ መንገድ እንገፋበታልን፡፡ ሥርዓት ባጣ መንገድ ደኖችን በማውደም ከሰል በማክሰል ሥራ የተሰማሩት ወገኖችን በአግባቡ መቆጣጠር የሚቻልበትን እርምጃ በመውሰድ ውድመቱን ለመቀነስ እንሠራለን፡፡ አሁን ያሉት የተፈጥሮ ደኖች እንዳይጠፉ ተገቢውን ትኩረት ሰጥተን እንሠራለን፡፡ በደን ተክል ላይ በስፋት መሰማራት ብቻ ሳይሆን ከተተከሉም በኋላ በቂ እንክብካቤ በማድረግ የሚያድጉበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

12.5.4 የአካባቢ ብክለትን ለመከላከል ተገቢ ትኩረት ስላልተሰጠ አሁን ያሉት ትንንሽ ኢንዱስትሪዎች እንኳ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ ስለሆነ የአካባቢ ብክለትን ለመከላከል የሚያስችል በቂ ሥራ የሚሠራና ተገቢውን ቀጥጥር የሚደረግ ይሆናል ፡፡

12.5.5 የዓለም አቀፍ (ግሎባል) የአየር ሙቀት መጨመርና መዛባት ሁሉንም አገሮች የሚጎዳ ቢሆንም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ አገሮች የሚያመጣውን መጠነ ሰፊ ጉዳት ለመቋቋም ብቃት ስለማይኖረው የሚከሰቱትን አደገኛ ሁኔታዎች እንደ ጎርፍ፣ የበሽታዎች ቀጽበታዊ መስፋፋት፣ ወዘተ.. ለማስቀረት የሚያስችል ብሄራዊና ክልላዊ አቅም እንዲገነባ ይደረጋል።

13. **የመሬት ጥያቄን በተመለከተ**

መሬት በአገራችን ለልማት እጅግ ወሳኝ ከሆኑት የተፈጥሮ ሀብቶች አንዱ ነው ። በገጠር ለግብርናና ለከብት ርቢ እንዲሁም ለደን ልማት ሲውል በከተማም ለተለያዩ የልማት ሥራዎች ይውላል። መሬት በልማት ረገድ ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ቢሆንም በአገራችን በተገቢው መንገድ ጥቅም ላይ አልዋለም።

-መንግሥት መሬትን እንደ ግል ንብረቱ በመቆጠር በቂ ባልሆኑ የተለያዩ ምክንያቶች አርሶ አደሮችንና አርብቶ አደሮችን እንዲሁም በርካታ የከተማ ኗሪዎችን ከመሬታቸው እንዲፈናቀሉ በማደረግ ለድህነትና ለችግር እየዳረጋቸው ይገኛል።

-መሬት ህዝቡ የሚቆጣጠረውና የሚያዝበት ሳይሆን ካድሬዎችና ሹማምንት እየቸረቸሩ ሀብት የሚያካብቱትበት ሆኗል። ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናት ከሕገ መንግሥቱ ውጭ በልዩ ውሳኔ የሚቀራመቱት ሁብትም ሆኗል። ይህን አሳሳቢ ሁኔታ የተገነዘቡ የተለያዩ ፓርቲዎች በመሬት አጠቃቀምና ይዞታ ላይ ከፍተኛ ክርክሮች ሲያካሂዱ ቆይተዋል። እኛም በዚህ ዙርያ ሰፊ ውይይት ካካሄድን በኋላ የሚከተሉትን አቅጣጫዎች ተግባራዊ ለማደረግ ተስማምተናል ።

13.1 ባለፉት የደርግና በአሁኑ የኢህአዴግ መንግሥታት መሬት የመንግሥት ነው ተብሎ ለፖለቲካ መሣርያነት በመጠቀም ሥራ ላይ የቆየው ፖሊሲ መቀየር የሚገባው መሆኑንና ይህም አርሶ አደሩ የሚጠቀምባቸው መሬቶች በራሱ በአርሶ አደሩ በግል ባለቤትነት የሚያዝና አርሶ አደሩ ከመሬት የማይፈናቀልበትን ሁኔታ የሚያረጋግጥ ይሆናል።

13.2 በአርሶ አደሮች የግል ይዞታ ሥር ያልሆኑትና ኅብረተ ሰቡ በጋራ ለከብት እርባታም ሆነ ለሌሎች አገልግሎቶች የሚጠቀምባቸው መሬቶች እንዲሁም የአርብቶ አደሩ መሬቶች የአካባቢው ኅብረተ ሰብ የጋራ ሀብት ሆነው በአካባቢው ህዝብ ስምምነት መሠረት በጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል ።

13.3 ከአርሶ አደሮችና አርብቶ አደሮች የግልና የጋራ ይዞታ ውጭ የሆኑና መንግሥት ለኅብረተ ሰብ አገልግሎት የሚጠቀምባቸው መሬቶች የመንግሥት እንዲሆኑና የግል ኢንቨስተመንት ከአርሶ አደሩ አርብቶ አደሩና ከኅብረተሰቡ ውጭ ሆኖ በመንግሥት የተከለለ ወይም ኢንቨስተሮች ከአርሶ አደሮች በግል ከያዙት በመከራየት የሚያለሙት እንዲሆን ሊደረግ ይገባል፡፡

13.4 የግል ይዞታ ያላቸው አርሶ አደሮች መሬታቸውን በዋስትና አስይዘው ከባንክ ብድር ሊያገኙ የሚችሉበትንና አበዳሪዎችም ዋስትና የሚያገኙበት ሁኔታዎች ይመቻቻሉ ፡፡

## 14. በውጭ አገር ስለሚኖሩ ዜጎቻችን የልማት ተሳትፎ

- የኢሕአዴግ መንግስት በፓለቲካ አመለካከታቸው ከእሱ የተለዩ ዜጐችን በተለያዩ መንገዶች፣ በማሠር፣ በማስፈራራት፣ ከሥራ በማፈናቀል ከሀገር እንዲወጡ አድርጓል፡፡
- በሀገሪቷ የሥራ መስክ ለሥርዓቱ ደጋፊ በማድላት የሚሰጥ በመሆኑና በቂ የሥራ ዕድል ባለመፈጠሩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ዜጐች ለሥራ ፍለጋ ወደተለያዩ ሀገራት በመስደድ ለከፍተኛ አደጋ በመደረግ ላይ ይገኛሉ፡፡
- ኢሕአዴግ በውጭ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንን የሚፈልጋቸውን ወደ ሀገር መጥተው ኢንቬስት እንዲያደርጉ ወይም የውጭ ምንዛሪ እንዲልኩ እንጂ በዜግነታቸው መብታቸው እንዲከበር ያለው ፍላጐት አናሳ መሆኑን፡-

በመገንዘብ፡-

14.1 ዜጐች በፖለቲካ አመለካከታቸው ተገፍተው ከሀገራቸው እንዳይወጡ በሀገሪቷ የዴሞክራሲ ሥርዓት እንዲከበር በማድረግ በውጭ ያሉትም ወደ ሀገራቸው ገብተው በፓለቲካውና በኢኮኖሚ ልማቱ እንዲሳተፉ ይደረጋል፡፡

14.2 በተለያዩ ሀገሮች የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ሰብአዊ መብታቸው ተከብሮ ሠርተው በሕይወት መኖር እንዲችሉ በኃላፊነት የሚከታተል አካል እንዲኖር ይደረጋል፡፡

14.3 ዜጐች በሀገራቸው ሠርተው መኖር ሲችሉ በስደት ለአደጋ የሚጋለጡበት ሁኔታ እንዲቃለል የሥራ ዕድል ያለ አድልዎ እንዲደረስ እንደዚሁም አዳዲስ የሥራ መስኮች እንዲፈጠሩ ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡

## v፡ የሴክተር ፖሊሲዎች

### 15. የግብርና ልማት

### 15.1 አጠቃላይ የግብርና ልማት

- በሀገሪቱ ለመስኖ ልማት አመቺ የሆኑ አካባቢዎች ያሉ ቢሆንም ለዚሁ ጉዳይ ኢሕአዴግ የሰጠው ትኩረት እጅግ አናሳ መሆኑና ቀጣይነት ያለው ሥራ ባለመሥራቱ የሀገራችን ግብርና ከዝናብ ጥገኝነት ሊላቀቅ አልቻለም፡፡

- ለግብርና ምርት እድገት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችሉት እንደማደበሪያና ፀረ ተባይ ያሉ ግብአቶች በገዥው ፓርቲ በስመ ኢንደውመንት በሚንቀሳቀሱ የንግድ ድርጅቶች በምኖፓል በመያዛቸው የዋጋ ውድድር እንዳይኖር ተደርጐ ዋጋውም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ የተወሰኑ ገበሬዎች በውድ ዋጋ እንዲገዙ ከመገደዳቸው በላይ ብዙሃኑ ገበሬ ለመግዛት ባለመቻሉ በቂ ምርት ለማምረት አልተቻለም፡፡

- የገበሬውን ነባር የእህል ዘሮች በተለያዩ ዘዴዎች ምርታማነታቸው እንዲያድግ ማድረግ ሲቻል ገበሬው አቆይቶ ሊጠቀምባቸው በማይችሉ ዲቃላ ዘሮች በመተካታቸው ገበሬውም በምርጥ ዘር ላይ ሙሉ በሙሉ ጥገኛ ሆኖ እንዲቀር ከመገደዱ በላይ ይህም ቢሆን በበቂ መጠን አለመገኘቱ

- ገበሬው እነዚህን ግብዓቶች ከመንግስት በብድር የሚወስዳቸው በመሆኑ በሰው ሠራሽም ሆነ በተፈጥሮ አደጋ ምርቱ ከጠፋ የዕዳ ቅነሳ ሳይደረግ የእርሻ በሬውን ሽጦ ዕዳ እንዲከፍል መደረጉ፡-

- በበለፀጉ ሀገሮች እንኳን ገበሬው ትርፍ ምርት አምርቶ የዋጋ መውደቅ እንዳይደርስበት መንግስት ተመጣጣኝ ዋጋ በመክፈል ምርቱን በመረከብ ድጐማ ያደርጋል፡፡ ኢሕአዴግ ግን ዜጐችን ለመመገብ ለማይችል ግብርና የድጐማ ሥርዓት መከልከሉ፡፡

- ኢሕአዴግ ገበሬው ዘመናዊና አዳዲስ የእርሻ ቴክኖሎጂዎችን ቢጠቀም ሥራ ይፈታል በማለት ዘመናዊና አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን እንዳይጠቀም ማድረጉ፡፡

- የግብርና ልማት ሠራተኞች በስለጠኑበት ሙያ ለገበሬው የምክር አገልግሎት ከመስጠት ፋንታ ለገዥው ፓርቲ በካድሬነት እንዲያገለግሉ በመደረጋቸው ከገበሬው ጋር ቅራኔ ውስጥ እንዲገቡ ማድረጉን፡-

በመገንዘብ በመድረኩ የሚከተሉት የመፍትሔ ሀሳቦች ተግባራዊ እንዲሆኑ ይደረጋል።

15.1.1 የግብርናው ምርት ከዝናብ ጥገኝነት ተላቆ በቂ ምርት ለማምረት እንዲቻል ለመስኖ ልማት በቂ በጀት በመመደብ የመስኖ እርሻ በከፍተኛ ደረጃ እንዲስፋፋ ይደረጋል። የግል ባለሀብቶችም በመስኖ ሊለሙ በሚችሉ አካባቢዎች በስፋት ተሠማርተው እንዲያመርቱ አስፈላጊው የማበረታቻና አስተማማኝ ዋስትና እንዲኖር ይደረጋል።

15.1.2 ለግብርና ምርት እድገት ወሳኝ የሆኑ ግብአቶች እንደ የአፈር ማዳበሪያ ያሉት አሁን በገዥው ፓርቲ የንግድ ድርጅቶች በሞኖፓል የተያዙትን በማስቀረት ሕጋዊ የሆኑ የግል ባለሀብቶች በዘርፉ ሥራ የሚሳተፉበት አሠራር እንዲኖርና ገበሬው በተመጣጣኝ ዋጋና በወቅቱ የሚያገኝበት ሁኔታ ይመቻቻል።

15.1.3 ምርጥ ዘርንም በተመለከተ ገበሬው የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም ነባሩን የራሱን የእህል ዘር ተጠቅሞ ምርቱን እንዲያሳድግና ሙሉ በሙሉ በምርጥ ዘር (Hybrid seed) ላይ ተወስኖ እንዳይቀር ይደረጋል።

15.1.4 ገበሬው በብድር በሚወስዳቸው ምርጥ ዘሮች ችግርና በተፈጥሮ አደጋ ምርቱን በሚያጠበት ጊዜ ገበሬው ያለውን ንብረት ሸጦ የብድር ዕዳ የሚከፍልበት አሠራር እንዲቀር የዕዳ ሥረዛ ሥርዓት ይዘረጋል።

15.5.5 ለዘመናት በባህላዊ ማረሻ በመታረሱ ለምነቱ ተሟጦ ያለቀው መሬት ለምርት መቀነስ አንዱ ምክንያት በመሆኑ ገበሬው መሬቱን በጥልቀት በወቅቱ አርሶ ለተክሉ ምቹ የአፈር ዝግጅት እንዲያደርግ ትራክተሮችን በኪራይ የሚያገኝበት ሁኔታ ይመቻቻል። እንደዚሁም የምርት ብክነትን በመቀነስ ገበሬው ተጠቃሚ እንዲሆን ለማጨጃ የኮምባይነሮች ሥምሪት አመቺ በሆኑባቸው አካባቢዎች ገበሬው በኪራይ አግኝቶ ምርቱን በወቅቱ ሰብስቦ እንዲያሳገባ አስፈላጊው ይደረጋል።

15.1.6 በሀገር ሀብት እንዲሰለጥኑ የተደረጉት የልማት ሠራተኞች ገበሬው ምርቱን እንዲያሳድግ ምክርና እገዛ እንዲያደርጉ ተብሎ ስለሆነ ኢሕአዴግ የልማት ሠራተኞቹን በፓለቲካ ካድሬነት በመቀጠም በቡድንና በጕጥ ያደራጃቸውን ገበሬዎች እንዲቆጣጠሩለት እያደረገ ያለውን አሠራር በመለወጥ ሠራተኞቹ በሠለጠኑበት ሙያ ብቻ ነፃ ሆነው ለገበሬው አገልግሎት እንዲሰጡ ይደረጋል።

15.1.7 ሀገሪቷ በምግብ እህል እራሷን ችላ ከተመፅዋችነት አዙሪት እንድትላቀቅ ለማስቻል መንግስት ከዓለም አበዳሪ ድርጅቶች የዕዳ ቅነሳ ድጐማ እንደሚያገኝ ሁሉ ለገበሬውም የግብርና ሥራ ድጐማ ይደረጋል፡፡

**15.2 አርበቶ አደሮችን በሚመለከት**

በሚልዮኖች የሚቆጠር የአገራችን ህዝብ በከብት አርቢነት የሚተዳደር መሆኑን በመገንዛብ

የአርበቶ አደሩም ኑሮ ልክ እንደ አርሶ አደሩ እጅግ ዝቅተኛና ለካፋ ችገሮች የተጋለጠ መሆኑን በማስተዋል

የአርብ አደሩን የኑሮ ደረጃ የሚያሻሽሉ ፈጣን እርምጃዎች ካልተወሰዱ ኑሮው አሁን ካለበት የከፋ ሊሆን እንደሚችል በማሰብ

15.2.1. መድረኩ የአርብቶ አደሩ የኢኮኖሚ መሠረት የሆነውን የእንስሳት ሃብት ልማት ለማፋጠን የመኖ፣ የውሃና የጤና ችግሮችን ለመፍታት በበቂ ጥናትና በሕብረተሰቡ ፍላጎትና ተሳትፎ ላይ የተመሰረቱ እርምጃዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

15.2.2 አርብቶ አደሩ በሚኖርባቸው አካባቢዎች የሚገኙትን እንደ ውሃና መዓድን የመሳሰሉትን የተፈጥሮ ሀብቶች በመጠቀም የህዝቡን ኑሮ ለማሻሻል ጥረት ያደረጋል፡፡

15.2.3 አርብቶ አደሮችን ያላሳተፈና ተጠቃሚ ያላደረገ የልማት ፕሮጀክት ተገባራዊ እንዳይሆን ጥረት ያደረጋል፡፡

**15.3 ዘመናዊ እርሻዎችን ማሰፋፋት**

- በአገራችን ዘመናዊ የሚባሉ እርሻዎች በዘፈቀደ እየተስፋፉ መሆናቸው የሚያሳስበን በመሆኑ
- እነዚህ እርሻዎች ካአገራችን የምግብ ፍላጎት ጋር ያልተቆራኙ መሆናቸው
- እርሻዎቹ በአካባቢያዊ ስነምህዳር ላይ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደሩና መሆናቸው
- በእርሻዎቹ ላይ ተቀጥረው በሚሠሩ ወገኖች ላይም የጤንነት ችግር እያስከተሉ መሆናቸው
- እነዚሀ እርሻዎች በሚስፋፉበት ወቅት በርካታ አርሶ አደሮች ከኑሯቸው እየተፈናቀሉ ለችግር እየተጋለጡ መሆናቸውን ግንዛቤ በመውሰድ

15.3.1 የአገራችንን የምግብ ፍጆታ በአስተማማኝ ለማቅረብ የሚያስችሉና ለኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃዎችን የሚያቀርቡ ዘመናዊ እርሻዎች እንዲስፋፉ ልዩ ትኩረት ይደረጋል፡፡

15.3.2 ለውጭ ባለሀብቶች የሚሠጡ ሰፋፊ እርሻዎች ለአገራችን አዲስ ቴክኖሎጂን የሚያስተዋውቁ፣ ሥራ አጥነትን ለመቅረፍ የሚያስችሉና የአካባቢ ብክለትን የማያስከትሉ መሆናቸውን እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡

15.3.3 የአገር ውስጥ ባለ ሀብቶች ከመንግሥት ድጋፍ እንዲያገኙ በማድረግ በሰፋፊና ዘመናዊ እርሻዎች ልማት እንዲሳተፉ እናበረታታለን፡፡

15.3.4 በሰፋፊ እርሻዎች የተሰማሩ ሠራተኞች ጤንነታቸው የተጠበቀ ይሆን ዘንድ አስፈላጊው ቁጥጥርና ክትትል ይደረጋል፡፡

15.3.5 መንግሥት ትላልቅ ግድቦችን በመሥራት ባለሀብቶችና ገበሬዎች የውሃ ዋጋ እየከፈሉ በመጠቀም ዘመናዊ እርሻ እንዲያስፋፉ ይደረጋል፡፡

15.3.6 ከአገራችን ልማትና ዕድገት ጋር ጠንካራ ቁርኝት የሌላቸውና ለውጭ ምንዛሪ ግኝት ብቻ ተብለው የሚመረቱ ምርቶች ለምግብ ምርት የምንጠቀምባቸውን ማሳዎች እየተሻሙ ስለሆነ የእንቅስቃሴ አቅጣጫቸው እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡

## 15.4 የደን ሀብት ልማት

- የደን ሀብታችን በከፍተኛ ደረጃ እየተመናመነና እየተሟጠጠ በመሄድ ላይ በመሆኑ
- ቀሪው የደን ሀብታችንም አግባብ ባለው መንገድ ጥቅም ላይ እየዋለ ባለመሆኑ
- ደኖቻችን የነበራቸው ከፍተኛ የበዝሀ ህይወት ሀብትም እየጠፋና እየተመናመነ በመሄድ ላይ መሆኑ
- የደን ባለሙያዎቻችን የተበታተኑና ሙያዊ ዓቅማቸውን ሥራ ላይ የሚያወሉበት የተመቻቸ ሁኔታ የሌለ በመሆኑ፣ በመፍትሔነት የሚከተሉትን አቅጫዎችን ተግባራዊ እናደርጋለን፡፡

15.4.1 እየተመናመነ በመሄድ ላይ ያለውን የደን ሀብታችን ጨርሶ ከመውደም የምንከላከልበትን  ስተራተጂ በመቀየስ የተቀናጁ እንቅስቃሴዎችን እናደርጋለን፡፡

15.4.2 የደን ሀብታችን የሚጠቀሙ የተለያዩ ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ እናደርጋለን፡፡ በተለይ ቀርቀሃን የመሳሰሉ የደን ሀብቶቻችን በመጠቀም የግንባታና የቤት ቁሳቁሶችን የሚያመርቱ የማምረቻ ተቋማት እንዲስፋፉ ብርቱ ጥረት

እናደርጋለን፡፡ ከዚህ ሌላ የደን ውጤቶቻችንን የሚጠቀሙ የተላያዩ መድሃኒቶች እንዲመረቱ እናበረታታለን፡፡

15.4.3 የደን ሀብታችን በመንግስት፣ በህብረተሰብና በግለ ሰብ ባለቤትነት ሥር የሚሆን ሆነው የተቀናጁ ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች እየተቀረጹ እንዲለሙ ይደረጋል፡፡

15.4.4 የደን ባለሙያዎቻችን በምናደርጋቸው የደነ ሀብታችን መልሶ የማዳንና የማልማት እንቅስቃሴዎች ተሳታፊ ሆነው የድርሻቸውን እንዲያበረክቱ ልዩ ትኩረት እንሰጣለን፡፡

## 16. ኢንዱስትሪ

- ገጠርን ማዕከል ያደረገ የልማት ፓሊስ እከተላለሁ የሚለው ኢህአዴግ የእንዱስትሪ ፓሊስ የሌለው መሆኑ፡-
- ከውጭ የሚመጡ የከባድ እንዱስትሪ ውጤቶችን የሚተኩ ምርቶች በሀገር ውስጥ የሚመረቱበት ሁኔታ አለመመቻቸት፡-
- በቀላሉ አገር ውስጥ ሊመረቱ ይችሉ በነበሩ ርካሽ የውጭ እንዱስትሪ ምርቶች የሀገሪቷን ኢኮኖሚ እንዲጎዳ እያደረገ መሆኑ፡፡
- መንግስት የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ አራምዳለሁ ቢልም ያሉትን ኢንዱስትሪዎች ወደግል ባለማዞሩ መርሁን የሚቃረን አሠራር እየተከተለ መሆኑ
- በመንግስት እጅ የሚገኙ ነባር እንዱስትሪዎችም በጠንካራ ማነጅሜንት ተደራጅተው እንዳይሠሩ በመድረጉ ጥራት ያለው ምርት ለማምረት ካለመቻላቸውም በላይ በጥሬ ዕቃ አቅርቦት እጥረትና ኃላቀር ቴክኖሎጂ ከአቅማቸው በታች እንዲሠሩ እየተደረገ መሆኑ
- ባሉት እንዱስትሪዎች አካባቢ የሚኖረው ሕዝብ ጥቅም የሚያገኝበት አሠራር ካለመዘርጋቱም በላይ አካባቢያቸውን በመበከል ለጉዳት እየዳረጓቸው መሆኑ፡-

16.1 በሀገሪቷ ኢንዱስትሪ እንዲስፋፋ ለማድረግ የሚያስችሉ ፓሊስዎችን በመንደፍ ተግባራዊ ይደረጋል፡፡

16.2 ከውጭ የምናስመጣቸውን የከባድ ኢንዱስትሪ ውጤቶችን የሚተኩ ምርቶች አዋጭነታቸው እየተጠና በሀገር ውስጥ እንዲመረቱ ይቻለ ዘንድ የከባድ ኢንዱስትሪዎች ግንባታ እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

16.3 በአሁኑ ጊዜ አስተማማኝና ዘላቂ ዕድገት የሚገኘው በዕውቀት ላይ የተመሠረተ የኢኮኖሚና ማሕበራዊ ልማት በማካሄድ ብቻ ስለሆነ ለአጠቃላይ ሳይንስና ትክኖሎጂ ሥራዎች በተለይ ደግሞ ለኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡

16.4 በመንግስት እጅ የሚገኙ ኢንዱስትሪዎች ወደ ግል ባለሀብቶች በአፋጣኝ ተዛውረው በአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ተጠናክረው በሀገሪቷ ኢኮኖሚ ዕድገት ተገቢውን ድርሻ እንዲወጡ ይደረጋል፡፡ በተለያየ ምክንያት ወደ ግል ሊዛወሩ ያልቻሉትም ብቃት ያለው ማኔጅመንት አግኝተው ትርፋማና ውጤታማ ሆነው እንዲቀጥሉ ይደረጋል፡፡

16.5 ከኢንዱስትሪዎች የሚወጡ ቆሻሻዎች በአካባቢ ሕዝብ ላይ ጉዳት እንዳያደርስና የአካባቢ ብክለት ለመከላከል አስፈላጊው የቁጥጥር አሠራር ይዘረጋል፡፡ የአካባቢው ሕዝብም ጥቅም የሚያኝበት አሠራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡ ካሁን በፊት ጉዳት የደረሰባቸውም ካሣ የሚያገኙበት ሁኔታ እንዲኖር ይደረጋል፡፡

## 17. ንግድን በተመለከተ

17.1 የንግዱ ክፍለ ኢኮኖሚ ለበርካታ ኢትዮያውያን ሰፊ የሥራ ዕድልና ገቢ እየፈጠረ በመሆኑና የወደፊት የልማት አስተዋጽኦው ከፍተኛ ስለሚሆን ሁሉንም ዜጎችና ድርጅቶች በእኩልነት እንዲያሳትፉበት ልዩ ትኩረት እንሰጣለን፡፡ የንግዱ ማሕበረ-ሰብም የኩሉን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ተገቢውን ሕጋዊ ድጋፍ ይደረግለታል፡፡

17.2 የንግድ ፈቃድ ማግኘት የሁሉም ዜጋ መብት መሆኑ በመገንዘብ ያለምንም አድልዎ የሚገኝበትን ሁኔታ እንፈጥራለን፤ የግብርና ቀረጥ ከፍያም ፍትሐዊና ከፓርቲ ግንኙነት የጸዳ እንዲሆን እናደርጋለን፡፡

17.3 የንግዱ-ማሕበረሰብ ያሉብትን ችግሮች እንዲፈታና በአገሪቱ ዕድገትና ልማት የላቀ አስተዋጽኦ ያደርግ ዘንድ በነጻ እንዲደራጅ እናደርጋለን፡፡

17.4 የንግዱ ማሕበረ- ሰብ እንቅስቃሴዎች የሚያዳክሙ የመንግሥትና የፓርቲ አላስፈላጊ ጣልቃ ገብነቶችን በማስወገድ ነጻ እንቅስቃሴዎች እንዲኅለብቱ አበክረን እንሠራለን፡፡

## 18. የከተማ ልማትን በተመለከተ

ከተሞቻችን በቂ ትኩረት ተሰጧቸው በፕላን ተመርተው እያደጉ እንዳልሆኑና ችግሮቻቸው መሠረታዊ መፍትሔዎች ማግኘት እንዳለባቸው ቀድም ሲል

ከገለጽናቸው በተጨማሪ የሚከተሉት ከተማ ነክ ጉዳዮች ልዩ ትኩረት የሚሹ ይሆናሉ:: ስለሆነም፣

- የከተማ መሬት አስተዳደር ግልጽነትና ተጠያቂነት የተጓደለበት በመሆኑ ለሙስና ከመዳረጉ ባሻገር የልማት ማነቆ ሆኖ መገኘቱ በእጀጉ የሚያሳስበን መሆኑ፣

- የመኖሪያ ቤት ችግር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ በመሄድ ላይ መሆኑና በተለይ መንግሥትና የቀበሌ መስተዳድሮች የያዟቸው የተወረሱ ቤቶች መቋጫ ስላልተበጀላቸው በከተማ ልማትና በነዋሪው ላይ ከፍተኛ ችግር እያስከተሉ መሆናቸው፣

- በከተሞች በሚካሄዱ ግንባታዎችና በሚደረጉት የከተማ መስፋፋቶች ምክንያት የከተማ ኗሪዎችና የገጠር ገበሬዎች እየተፈናቀሉ ኑሯቸው ዋስትና ያጣበት ሁኔታ መፈጠሩ ፣

- የመኖሪያ ቤቶች አቅርቦት እንዲስፋፋ የሚያገለግሉ ባንኮች (mortgage banks) ያልተደራጁና ያልተጠናከሩ መሆናቸው ከፍተኛ የቤቶች ግንባታ እንዳይካሄድና ዓቅመ ያለው የሕብረተሰቡ ክፍል በብዛት የቤት ባለቤት እንዳይሆን እያስከተለ ያለው ችግር በመገንዘብ፣

የሚከተሉ መፍትሔዎችን ተግባራዊ እናደርጋለን::

18.1 የከተማ መሬት ግልጽና ተጠያቂነት በተላበሰ መንገድ የሚተዳደርበት ሁኔታ እንዲኖር እናመቻቻለን ::

18.2 በከተማ ከሊዝ ውጭ ነባር ይዞታ ተብሎ የሚታወቀው መሬት የባለይዞታዎች መሆኑን ዕውቅና እንሰጣለን:: በመሆኑም ባለይዞታዎች ያለበቂ ምክንያት የማይፈናቀሉበትንና ቢፈናቀሉም ለኑራቸው በቂ የሆነ ካሳ የሚከፈሉበት ሁኔታ እንዲኖር እናደርጋለን:: የሚከፈላቸው ካሳ ቢያንስ ከመሬቱ የሚገኘውን የሊዝ ዋጋ ያነሰ እንዳይሆን ይደረጋል:: ከገጠር የሚፈናቀሉትም ቀጣየ ኑራቸው ዋስትና እንዲያገኙና በከተማ ውስጥ በቂ መሬት እንዲያገኙ ጭምር ይደረጋል::

18.3 በከተሞች የቤቶች ልማት እንዲስፋፋ ይረዳ ዘንድ ዓቅም ያለቸው ዜጎች ተበድርው ቤት የሚሠሩበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የሞርጌጅ ባንኮች እንዲስፋፉ እናደርጋለን:: ዓቅም የሌላቸው ወገኖች ደግሞ የመንግሥት ድጎማ እየተሰጣቸው በአካባቢው ማዘጋጃ ቤቶች እየተሠሩ የሚከራዩና የሚሸጡ ቤቶች እንዲስፋፉ እናደርጋለን::

18.4 በየከተማው ያሉት የመንግሥትና የቀበሌ ቤቶች እያስከተሉ ያሉትን ችግር መፍትሔ ለመስጠት የባለቤትነታቸው ጥያቄ በተመለከተ መቋጫ እንዲያገኝ እናደርጋለን፡፡ እስከዛው ድረስም በመንግሥትና በቀበሌዎች አስተዳድር ሥር ያሉት ቤቶች በተለያዩ ምክንያቶች እንዲፈርሱ ሲደረግ አበል ሲያገኙ የነበሩት የድሮ ባለቤቶች አበላቸው እንዲቀጥል ይደረጋል፤ ተከራዮችም ተለዋጭ መጠለያ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

## 19. የውኃ ልማት

- አገራችን በበርካታ ወንዞች፣ ሐይቆችና የከርሰ-ምድር ውኃ የታደለች ብትሆንም እሁንም በተደጋጋሚ ድርቅ እየተመታች ለረሀብ የምትጋለጥ በመሆኗ
- ከአገራችን የውኃ ሀብት ለመስኖ፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለመጠጥና ለእለት ተእለት አገልግሎት የዋለው መጠን እጅግ አነስተኛ በመሆኑ
- የዕድገት ደረጃችን እጅግ ዝቅተኛ ቢሆንም ያሉን ወንዞች እየተበከሉና ሀይቆችም በደለል እየተሞሉ ስለሆነ አሳሰቢ ሁኔታ ላይ መሆናቸው

-የውኃ ሃብታችን በአግባቡ እንድንጠቀምና እንድንንከባከብ የሚያስችሉን ጠንካራ ተቋሞች አለመገንባታችን

-የውኃ ሀብታችን በመጠቀም ረገድ ከፍተኛ እስተዋጽ ሊኖረው የሚያስችል ጠንካራ አገራዊ የባለሙያዎች ዓቅም ባለመፍጠራችን፣ ለከፍተኛ ችግር ተጋላጭ ሆነናል፡፡ በመሆኑም ይህን ችግር ለመቅረፍ

19.1 የአገራችንን የውኃ ሀብት በተቀናጀና በተጠና መንገድ በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ እንዲውል እናደርጋለን

19.2 በተለይ ካለንብት ረሀብ ለመላቀቅና ራሳችንን ለመመገብ ንችል ዘንድ ወንዞችን በመገደብና የከርሰ ምድር ውሃን በመጠቀም ልማት ላይ እንዲውሉ እናደርጋለን፡፡

19.3 እስካአሁን ድረስ ንፁሕ የመጠጥ ውሃ ያልደረሳቸውን በብዙ ሚልዮን የሚቆጠሩ ወገኖች እንዲዳርሳቸው እናደርጋለን፡፡

19.4 ወንዞቻችንና ሃይቆቻችን ከብክላ እንዲጸዱና በደለል እንዳይሞሉ አስፈላጊውን የመከላከልና የመቆጣጠር እንቅስቃሴ እናደርጋለን፡፡

19.5 የውሃ ሀብታችንን ለማጥናትና በአግባቡ ለመጠቀም የሚያስችል ጠንካራ ተቋም እንዲቋቋም እናደርጋለን፡፡

19.6 የዘርፉ ባለሙያዎች ዓቅማቸውን የሚያጎለብቱበትንና ተደራጅተው የሚሠሩበትን ሁኔታ እንፈጥራለን፡፡ በከፍተኛ ደረጃ የሚሠለጥኑበትንና ልምድ የሚቀስሙበትን ሁኔታም እናመቻቻለን፡፡

## 20 ኢነርጂ፡-

- አማራጭ የኢነርጂ ምንጮችን የማስፋፋት ሥራ ትኩረት ባለማግኘቱ ቀሪው የሀገሪቷ የደን ሀብት ለኢነርጂ ፍጆታ እየዋለ በአሳሰቢ ደረጃ ላይ ይገኛል፡፡
- አገራችን ብዙ የኢነርጂ አማራጮች ቢኖሯትም ጥቅም ላይ የዋለው እጅግ የተወሰነው ብቻ በመሆኑ በየጊዜው የኢነርጂ አቅርቦት ቀውስ ውስጥ ገብታ ትገኛለች፡፡ በመሆኑ

20.1 ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም አማራጭ የኢነርጂ ምንጮች ከጋዝ /ካሉብና ሌሎች/፣ ከነፋስ፣ ከፀሐይ፣ ከባዮ ጋዝና ከሌሎችም የሚገኝበት ሁኔታ ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡

20.2 ዜጎችን የዘመናዊ ኢነርጂ ተጠቃሚ ለማድረግና እያደገ የሚሄደውን የኢንዱስትሪና የሌሎች ዘርፎች የኢነርጂ ጥያቄ ዘላቂነትና ቀጣይነት ባላው መንገድ ለሚሟላት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት ተግባራዊ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

20.3. የሃይድሮ ኤሌክትሪክ ግድቦች ግንባታ የመስኖ ልማትን ግምት ባስገባ መልኩ በስፋት ይቀጥላል፡፡ የግድቦች ግንባታ ከሙስና በፀዳ እና በቂ ጥናት ላይ በመመረኮስ እንዲከናወን ይደረጋል፡፡ በዚህ መስክ በሂደት የራስ ዓቅም ለመገንባት ትልቅ ትኩረት ይሰጠዋል፡፡

## 21. ማዕድን፡-

- የኢሕአዴግ መንግስት ለማዕድን ልማት የሰጠው ትኩረት ዝቅተኛ በመሆኑ ሀገሪቷ ያላትን የማዕድን ሀብት ለይቶ ለማወቅ እንኳ አልተቻለም፡፡
- ለመንግሥት ጥቅም የሚያስገኙ የማዕድናት ልማት በሚካሄድባቸው አካባቢዎች የሚኖረው ሕብረተሰብ ጥቅም የሚያገኝበት አሠራር አለመዘረጋቱና በአካባቢው የተፈጥሮ ሀብት ላይ ጉዳትና ብክለት ማስከተሉ ታሳቢ በማድረግ፡-

21.1 የሀገሪቷ የማዕድን ሀብት እንዲታወቅና ለሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት እንዲውል በቂ በጀት በመመደብ ጥናት በማካሄድ የተሟላ የጂኦሎጂካል ካርታ እንዲሠራ ይደርጋል። እስካሁን የታወቁትም በሀገር ውስጥና በውጭ ባለሀብቶች ተሳትፎ እንዲለሙና በጥቅም ላይ እንዲውሉ አስፈላጊው የማዕድን ልማት ፓሊስ እንዲኖር ይደረጋል።

21.2 ለሀገሪቷ ከፍተኛ ጠቀሜታ የሚሰጡ ከፍተኛ የማዕድን ሀብት እንደ ወርቅ፣ ነዳጅና የመሳሰሉት በሚገኙባቸው አካባቢዎች ለሚኖር ሕብረተሰብ ልዩ ጥቅም (የሮያልቲ መብት) እንዲያገኙና በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚደርሰው ጉዳት ለመታደግ ቁጥጥር ይደረጋል።

**22. አገልግሎት ሰጭ ሰክተሮችን በሚመለከት፡-**

**22.1 ቴሌኮሙኒከሽን፡-**

- የኢትዮጵያ ቴለኮሙኒኬሽን አገልግሎት የኢሕአዴግ መንግሥት ከፍተኛ ገቢ ከሚሰበስብባቸው ተቋሚት ዋነው በመሆኑ የግል ባለሀብቶችን ለማሳተፍ አለመፈለጉ፡-
- ዘመናዊ መገናኛ ቴክኖሎጂዎች ባለመስፋፋታቸው የቴሌኮሙኒኬሽንና ተያያዥ አገልግሎቶች ችግሮች መኖራቸው።
- የቴለኮሙኒከሽን አገልግሎትና የቴክኖሎጂ ጥራቱ ዝቅተኛ ከመሆኑም ባሻገር ከስክተሩ የሚሰበሰበው ገቢ በተገቢው ሁኔታ ለልማትና ለአገልግሎት ጥራት ማሻሻያ አለመዋሉ፡-

እነዚህን ሁኔታዎች ለመለወጥ፡-

22.1.1 የቴለኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ከመንግስት ሞኖፓል ተላቀው አብዛኛው እጅ በመንግስት ሥር የሚቆዩ ሆነው የግል ባለሀብቶች ባለአክስዮን እንዲሆኑ ይደረጋል።

22.1.2 የቴለኮሚኒኬሽን አገልግሎት ጥራትን ለማሻሻል ከዘርፉ የሚሰበሰበው ገቢ ለሀገር ልማትና ጥራት ማሻሻያ እንዲውል አስተዳደሩና አሠራሩ ቀልጣፋ እንዲሆንና ሥራውም ከሙስና ነፃ ሆኖ ቀልጣፋ አግልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል።

22.1.3 ተገቢ ቴክኖሎጂዎችና ተያያዥ አገልግሎቶች እንዲሰፋፉና ሀገራችን የዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ተጠቃሚ እንድትሆን በዚህም ዋጋው ለህዝቡ ተደራሽ እንዲሆን ልዩ ትኩረት ይሰጣል።

22.2 የፖስታ አገልግሎት

የፖስታ አገልግሎት በበቂ ሁኔታና ጥራት አለመስፋፋት መልእክቶች አስተማማኝ ዋስትና ኖራቸው ልማቱን የሚያግዙ ባለመሆናቸው፣

የፖስታ አገልግሎት ጥራት ባለው መልኩ በሀገሪቱ እንዲስፋፋና መልእክቶችም አስተማማኝ ዋስትና እንዲኖራቸው በማድረግ የተቀላጠፈ አገልግሎት እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡

## 22.3 የትራንስፓርት አገልግሎት፡-

- የትራንስፓርት አገልግሎት ሰዎችንና ዕቃዎችን በብዛትና በፍጥነት በማጓጓዝ ለአንድ ሀገር ዕድገት ወሳኝ ቢሆንም ለዘርፉ የተሰጠው ትኩረት አናሳ ነው፡፡ ለዚህ ይረዳ ዘንድ የባቡር ትራንስፖርት ማስፋፋቱ ተገቢ ቢሆንም አዲስ ሊዘረጋ ቀርቶ የነበረውም ባለቤት ባጣ መልኩ እየተዳከመ እንዲሄድ ተደርጓል፡፡
- ዛሬ በአዲስ አበባ ከተማ ዜጐች ተንቀሳቅሰው ለመሥራት የትንስፓርት አገልግሎት በማጣት ውድ የሥራ ጊዜአቸው እየባከነ ይገኛል፡፡
- በአሁኑ ወቅት ያሉት የአይሮፕላን ማረፊያዎች በቂ ካለመሆናቸውም በላይ ባሉት ላይ ለመጠቀምም ለግል ባለሀብቶች የአይሮፕላን የመቀመጫ ብዛት በመወሰኑ በዘርፉ እንዳይሳተፉ እንቅፋት እንዲፈጠር ተደርጓል፡፡

በመሆኑም የትራንስፖርት አገልግሎት ችግሮችን ለማስወገድ፡-

22.3.1 የባቡር ትራንስፓርት መሥመር በሀገሪቷ የትራንስፖርት አገልግሎት ችግሮችን ለማስወገድ በተለያዩ ክልሎች የሚዘረጋበት አሠራር ተግባር ላይ እንዲውል ይደረጋል፡፡

22.3.2 ሕብረተሰቡ እንደልቡ ተንቀሳቅሶ እንዲሠራ በአዲስ አበባና በሌሎች ትላልቅ ከተሞች ህዝብን በአጭር ጊዜ በብዛት የሚያጓጉዙ (mass transport) ዘመናዊ የሆኑ የትራንስፓርት አገልግሎቶች እንዲኖሩ ይደረጋል፡፡ የግል ባለሀብቶች በሰፊው እንዲሳተፉበት በማድረግም ሕብረተሰቡ የተለያዩ አማራጮችን ለመጠቀም እንዲችል ትኩረት ይሰጠዋል፡፡

22.3.3 የግል የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በአየር ትንራስፓርት እንዲሳተፉ አሁን ያለው የግሉ ባለሀብት የሚያንቀሳቅሳቸው አውሮፕላኖች መቀመጫ ገደብ እንዲቀር ይደረጋል፡፡

## 22.4 የፋይናንስ አገልግሎት፡-

- የፋይናንስ አገልግሎት ለማስፋፋት የሚያስችሉ የባንክ አክሰዮን የመግዛት ዓቅም እንዲዳብር አለመደረጉ፡፡

- በኢትዮጵያ ንግድ ባንክና በመሳሰሉ ከፍተኛ የመንግሥት የፋይናስ ተቋማት የሀገር ውስጥ ባለሀብቶች በአክስዮን እንዲሳተፉ አለመደረጉ፡፡
- ከፍተኛ የልማት ሥራዎችን ለማከናወን የሚያስችል የረጅም ጊዜ ብድር የሚሰጡ የልማት ባንኮች አለመስፋፋታቸው
- መንግስት የሚሰበሰባቸው እንደ VAT ያሉ ገቢዎችም የኅብረተሰቡን አቅም ያላገናዘበ ከመሆኑም በላይ ግልፅነት የሚጐድለውና በኅብረተሰቡ ላይም የኑሮ ውድነቱ እንዲባባስ እያደረገ መሆኑ፡፡
- በሕጋዊ ነጋዴዎች ላይ የግብርና የታክስ ጫና እያረፈባቸው የተወሰኑት ደግሞ ተመሳሳይ ግብርና ታክስ ሳይከፍሉ በአቋራጭ የሚከብሩበት አሠራር ሕጋዊ ነጋዴዎችን ከሥራ ውጭ እያደረገ መሆኑ፡-

ችግሮችን ለመፍታት የሚከተሉትን የፋይናንስ መፍትሔዎች እናቀርባለን፡-

22.4.1 የአገር ውስጥ ባለሀብቶችና ባንኮች በሀገሪቷ ባሉ የመንግሥት ባንኮች ባለአክሲዮን ሆነው የሀገሪቷ የፋይናንስ አቅም የሚጐለብትበት ሁኔታ ይፈጠራል፡፡

22.4.2 የረጅም ጊዜ የልማት ሥራ ለሚያከናውኑ ባለሀብቶችና አልሚዎች የረጅም ጊዜ ብድር የሚያቀርቡ የልማት ባንኮች እንዲሰፋፉና እንዲጠናከሩ ይደረጋል፡፡

22.4.2 አሁን በሥራ ላይ ያለው የብድር አሰጣጥ አሠራር በተወሰነ ደረጃ ለቀቅ የሚደረግበትና ዜጐች በቀላሉ ብድር በማግኘት የኢኮኖሚው እንቅስቃሴ የሚስፋፋበት መንገድ ይመቻቻል፡፡

22.4.3 መንግስት የሚሰበሰባቸው እንደ VAT ያሉ ገቢዎች የሕብረተሰቡን ገቢ ያገናዘቡና ግልፅነት ያላቸው እንዲሆን ይደረጋል፡፡ ሕጋዊ ነጋዴዎችን እየጐዳ ያለው በአቋራጭ የመክበር ሁኔታ እንዲገታና ሁሉም ነጋዴ በተመሳሳይ መልኩ የሚፈለግበትን ግብርና ታክስ ከፍሎ እንዲሠራ ይደረጋል፡፡

22.4.4. የአለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት በኢትዮጵያ የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ ለአገሪቱ ልማት ከሚሰጡት ጥቅም እና ጉዳት አንፃር ታይቶ የሚወሰን ይሆናል፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ለመድረስ የሚያስችል ጥናት እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

## 23. ሠፈራ፡-

- የኢሕአዴግ መንግስት የገጠሩን ነዋሪ ሕዝብ ባሉበት እራሳቸውን እንዲችሉ በማድረግ ፋንታ በበቂ ጥናት ላይ ባልተመሠረተ ሁኔታ የዜጐች ሠፈራ

ሲያካሄድና አሁንም እያካሄደ ይገኛል። ይህ አሠራር እጅግ ተመናሞኖ በማለቅ ላይ ያለውን የደን ሀብት በመመንጠር የአካባቢ የአየር መዛባትን ከማስከተሉም በላይ በሠፋሪውና በነባረ ሕዝቦች መካከል ቅራኔ እንዲፈጠር አድርጓል።

በመሆኑም፡-

- የሕዝቡን ችግር ለመፍታት ባለበት ቦታ ሆኖ እራሱን የሚችልበት የተለያዩ የሥራ መስኮችን በመፍጠር ተግባራዊ ይደረጋል። ሕዝቡን ባለበት እራሱን እንዲችል ለማድረግ የማይቻልበት ሁኔታ ቢኖር በግብታዊነት ሳይሆን ዘላቂ ልማትን ሊያመጣ በሚችል መልኩና በአካባቢው ላይ ተጽእኖ በማያመጣ ሁኔታ በበቂ ጥናት ላይ ተመሥርቶ ይከናወናል።

## ባ□□ ክፍል ሦስት½ ማህበራዊ ጉዳዮች

### 24. ሥራ አጥነት፤

በወቅቱ በሀገራችን ከመጠን በላይ እየተሰፋፋ ላለው የሥራ አጥነት ችግር የኢሕአዴግ መንግሥት እየተከተለ ያለው ማህበራዊና ኢኮኖሚዊ ፖሊሲ ችግሩን ዘላቂነት ባለው መልኩ የሚቀርፍና /የሚቆጣጠር/ አይደለም፤ እየሆነ ያለው ግን ሥራ አጥነት በዜጐች ሕይወት ላይ የሚፈጥረውን ውጥረት በመጠቀም፣ ሥራ የማግኘት ዕድልን ለፓርቲ አባልነትና ደጋፊነት የመመልመያ መሣሪያነት ኢሕአዴግ እየተጠቀመበት መሆኑ ነው:: ይህም ሁኔታ በሥራ ላይ ተሰማርቶ ያለውንም ዜጋ የፖለቲካ መስመሬን አልተቀበላችሁም (አልደገፋችሁም) በማለትና የ«ፓርቲዬን ፖሊሲችንና ስትራቴጂችን አልፈፀማችሁም/አላስፈጸማችሁም» በሚል ውንጀላና በአስተዳደር መዋቅር ማሻሻያ (ጉሓሖ) ሰበብ ከሥራ መደባቸው እያፈናቀለ የሥራ አጡን ቁጥር እያሰፋው በመሆኑ ሁኔታው ክፉኛ □□ተባባሰ □□ኛል:: ይህንን አስከፊ ሁኔ□ ለመቆ□□ር አማራጭ መፍትሄቻችን የሚከተሉት ይሆናሉ::

24.1 በፅል ሴ□ተሩና በመንግሥት የሚመሩ □ሥራ ክ□ል □ሚ□ዓ ሩ አነስተኛ እንዱስትሪችንና የዕደ ጥበብ ሥራ ዘርፎችን በመላው ሀገሪቱ ከተማችና በገጠሩም በስፋት መዘርጋትና ይህንንም በሙያ ስልጠና እና በማይክሮ ፋይናንስ በመደገፍ የሥራ መስኮችን ማስፋፋትና እንዲሁም፣ የተለያዩ አገልግሎት ሰጭ (የንግድ፣ የቱሪዝም፣የትራንስፖርት ወዘተ) ዘርፎችን በየከተማቹና በ□□ሩ በስፋት እንዲስፋፉ ማድረግ፣ በግለሰቦችና ቡድኖች በሥራ ፈጠራ ተግባር ላይ እንዲሰማሩ ሁለ□በ እገዛና ድጋፍ መስጠት::

24.2 በ□□ሩ አግሮ እንዱስትሪን በማስፋፋት አርሶ አደሩ በቂ የግብርና ግብዓቶችን □□□ኝ በዘመናዊ የግብርና ስልቶችም በጐልማሶች መሰልጠኛ መርሃ ግብር አማካይነት ስልጠና □□□ኝ በምፅብ እህል የራሱንና የከተማውን ሸማች ፍላጐት ከማርካት አልፎ ለኢንዱስትሪው ግብዓት

የሚሆኑ ምርቶችን በማምረት፣ □□□ሩን ኑሮ ለማሻሻል በቂ ገቢ የሚያስገኝ ሰፊ የሥራ ዕድል የሚፈጠርበት ሁኔታ እንዲዳብር ስልት ቀይሶ መሥራት ::

**24.3** .በሲቪል ሰርቪሱና በሌሎችም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ባሉት ተቋማት ውስጥ ያሉ የሥራ ዕድሎችን ለዜጐች ያለአድልዖ፣ ሥራና ሠራተኛን በማገናኘትና በሙያው እርከኖች ውስጥ የደረጃ ዕድገትን በማረጋገጥ መርህ (ሰሮቄስስቄ ቋቋቄበሰቋበቄስ) ተመስርቶ የሥራን ዕድል በፍትሃዊነት ለማዳረስ የሚያስችል ማህበራዊ/ኢኮኖሚያዊ ፖሊሲን መቀየስና ባአፋጣኝ ሥራ ላ□ ማዃል::

## 25 ድህነት ቅነሳ፣

ለድህነት ቅነሳ ከዓለም አቀፍ ማህበረሰብ ለሀገራችን የሚደረገው ልገሳ መጠኑ በጣም ከፍ ያለ መሆኑ የሚታወቅ ሲሆን፣ ገዥው ፓርቲ ይህንኑ ድጋፍ ከራሱ እንደመጣ አድርጐ በማቅረብ እንደ የሥራ ዕድሉ ሁሉ ለአባላትና ደጋፊች መመልመያነት እየተጠቀመበት መገኘቱ፣ በተለ□ም ምር□ ች በሚካሄዱባቸው ወቅቶች ጐልቶ የሚታይ ነው:: እንደዚሁም፣ ሕዝቡን በሴፍቲኔት ተሳትፎና በአነስተኛ ብድር ወዘተ ተጠቃሚ በማድረግ ድህነት እንቀርፋለን እየተባለ ከዓለም አቀፍ ማህበረሰብ መጠነ ሰፊ ዕርዳታ የሚገኝ ቢሆንም፣ ባለው አድሎአዊ አሠራር ምክንያት ሁሉም ድሃ ዜጋ የዕድሉ ተጠቃሚ መሆን ያለመቻሉ በገሀድ የሚታይ ነው:: በተጨማሪም በሥርዓቱ ውስጥ ተንሰራፍቶ ባለው ሙስና ምክንያት በዕርዳታ ገንዘብ ላይ ከፍተኛ ብክነት እየደረሰ ከመሆኑም በላይ በአስተዳደሩ ብቃት ማነስ ምክንያት የድህነት መቀነሻ ስልቶች ተብለው ዕርዳ□ □ተ□ኘባቸው ዕቅዶች ተግባራዊ ሊሆኑ ያለመቻል ከሀገራችን ድህነትን መቀነስ የማይቻልበትን ሁኔ□ □ዓሮ □□ኛል::

ስለሆነም የሕዝባችንን አማካይ የነፍስ ወከፍ ገቢ አሁን ካለበት በዓለምአቀፍ መመዘኛ ከድህነት □ለል በታች ከሆነበት ለማውጣት የሚከተሉት እርምጃች በሥር ነቀል መልኩ ይወሰዳሉ::

**25.1.** ከውጭ በሚገኘ□ እርዳታ ላይ ብቻ ጥገኛ ባለመሆን፣ ድህነትን መቀነሻ ስልቶችን ለማስፋፋት ልዩ በጀት (ፈንድ) መድቦ በገጠርም ሆነ በከተማ ሕዝባችን ጥቅም በሚያስገኙ የተለያዩ የሥራ ዘርፎች እንዲሰማራ ሰፊ ዕድሎችን መፍጠር:: ለዚህም የራስ አገዝ ማህበሮችን በማቋቋም የማይክሮ ፋይናንስና የሌሎችም አገልግሎቶች ተጠቃሚ እንዲሆን ማስቻል:: ከዓለም አቀፍ ማህበረሰብ የሚገኘውንም ዕርዳታ ከፖለቲካ ወገንተኝነትና ከሙስና ነፃ በሆነ መልኩ ያለ አድልዖ በፍትሃዊነት ተግባር ላይ በማዋል ሀብት የማፍራትና የማድለብ እንቅስቃሴችን በገጠሩና በከተማቹ ሁሉ ማፋጠን:: ድህንትን ለመቅረፍ ከዓለም አቀፍ ማህበረሰብ የሚሰጠው የዕርዳታና

የብድር ገንዘብ ለ□ቀደለት ዓላማ መዋሉን የሚያረጋግጥ ሁሉም ባለድርሻች የሚወከሉበት የቁጥጥርና ክትትል ስርዓት በየወረዳው እንዲቋቋም ማድረግ::

25.2. አርሶ አደሩ የተለያዩ የግብርና ግብዓቶችን በብድር መልክ እየወሰደ በመጠቀም ከድህነት ለመውጣት የሚያደርገው ጥረት በባለሙያ እየታገዘ ለውጤት እንዲያበቃው ማድረግ:: አርሶ አደሩን ከባንክ በመበደር ከጊዜ ወደ ጊዜ በሚያጋጥሙት የተፈጥሮ የአየር ንብረት መዛባት የተነሳ ለኪሳራ □□□ረ□□ ብ□ሩን መመለስ የያለመቻል ሁኔታ እየተከሰተ እንደዚሁም በየከተማው በተለያዩ የሥራ ዘርፎች ተሰማርተው ሥራ ለመፍጠር የሚጥሩ ዜጐችም በተፈጥሮ አደጋ ምክንያት ችግር እየደረሰባቸው ለኪሳራ እየተዳረጉ መሆናቸው ድህነትን እያሰፋው ስለሆነ፣ ይህ ችግር ለሚያጋጥማቸው ሁሉ የዕዳ ስረዛ ይደረግላቸዋል:: በዚህ አሠራርም በዓለም አቀፍ አበዳሪ ሀገሮችና የፋይናንስ ተቋማት ለሀገራችን የተሰጠው የዕዳ ስረዛ ተጠቃሚነት ዕድል፣ ለአርሶ አደሩና በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላለው የከተማ ነዋሪውም ጥቅም እንዲውል ይደረጋል::

## 26. የሰው ሀይል ፍልሰትና ስደት

የሰው ሀይል ፍልሰትንና ስደትን በሚመለከት ያለው ችግር በአመዛኙ በስርዓቱ አምባገነናዊንነትና ማንአህሎኝነት፣ እንደዚሁም የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ እየተባባሰ የመጣ ነው:: ይህም ሁኔ□ በፖለቲካ ላይ ባተኮረ አድሎአዊ የኢሕአዴግ አስተዳደር ምክንያት ዜጐች በሀገራቸው መብታቸው ተከብሮና ጥቅማቸው ተጠብቆ ሠርተው ለመኖር ተስፋ በማጣት የሚሰደዱበትና ወደ ሌላ ሀገር ሄደው ሥራ የሚፈልጉበትን ተንሳፋፊ የሆነ አስተሳሰብ ይዘው እንዲቆዩና አጋጣሚውን ሲያገኙ ወደ ስደት እንዲያመሩ □□□ረ□ □□ኛል::

እንደዚሁም በከፍተኛ □ረጃ የሠለጠኑ ምሁራንን ሙያዊ አስተያየቶችና/ሂሶች ባለመቀበል ኢሕአዴግ በሚፈጽመው የማግለል ተግባር ወይም የፖለቲካው አገልጋይ ብቻ እንዲሆኑ በሚያደርገው ተፅዕኖ ምክንያት በሙያቸው ደህንነት ተሰምቷቸው ሊሠሩ ያለመቻላቸው፣ ለሚያበረክቱትም አገልግሎት የሚከፈላቸው ክፍያ ተመጣጣኝ ሙያ ካላቸው የውጭ ዜጐች ጋር ተመጣጣኝ ያለመሆኑና የሚሰሩባቸውም ተቋማትዩኒቨርስቲች፣ ኮሌጆች፣ የጤና ተቋማት፣ የምርምር ተቋማት ወዘተ አመራርና የአስተዳደር ሁኔታ የሙያ ነፃነታቸው ላይ ተፅዕኖ የሚያደርግ መሆኑ፣ ዜጐችን ለስደት □□□ረ□ □□ኛል::

ከዚህ በተጨማሪ በጉልበታቸው ሠርተው በሀገራቸው ሊኖሩና ለሀገራቸው ልማትም ድርሻቸውን ሊያበረክቱ የሚችሉ ወጣት፣ሴቶችና ወንዶች፣ እንዲሁም ጐልማሶች ጭምር ከምን ጊዜውም በላይ ለስደት □□ተ□ረ□ □□ኛሉ:: እነዚህም ወገኖች በየተሰደዱባቸው ሀገራትም ለከፍተኛ የሞራል ውድቀትና ብሔራዊ ሀፍረት ተዳርገው እንደሚኖሩና ተሰደው ሌላ ሀገር እስኪደርሱ ድረስም በየመንገዱ አሰቃቂ ችግሮች እየደረሱባቸው ሕይወታቸውን እስከማጣት ድረስ ለአደጋ እየተጋለጡ መሆናቸው፣ የኢትዮጵያዊ ዜግነትን እያዋረደ ያለ ጉዳይ ነው::

በገጠር የሚኖረው ሕዝባችንም በሕዝብ ብዛት ምክንያት በሚከሰተው የመሬት ጥበት፣ ኋላ ቀር የአመራረት ስልትና በተደጋጋሚ የሚያጋጥም የተፈጥሮ አየር ሚዛን መዛባት የተነሳ በሚከሰተው በኑሮ ችግር ምክንያት ወደ ከተማች እየተሰደደ በሥራ አጥነት የሚጉሳቆልበት የሀገር ውስጥ ፍልሰት ሁኔ□ም □□ፊ መሪ መሄ□ ብ□ችን ለጉስቁልና ኑሮ እየዳረገ በየከተማው ህፃናት አዝሎ ልመና ጭምር እየሰፋ እንዲሄድ እያደረገ ይገኛል::

ስለሆነም የሰው ሀይል ፍልሰትንና ስደትን ለመቀነስ የሚከተሉት የመፍትሔ □ርም□ች □□ሰ□ሉ፣

**26.1** ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ላይ የተመሠረተ ሁሉንም ዜጐች፣ ብሔር/ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዕኩልነት የሚያስተዳድር ስርዓት በመዘርጋት፣በተለይ ወደ ውጭ ሀገራት የሚፈልሰውንና የሚሰደደውን በከፍተኛ ደረጃ የሠለጠነ ዜጋ በሀገሩ ሠርቶ በመኖር ለዕድገቷና ልማቷ አስተዋጽዖ እንዲያደርግ ማስቻል:: በተለይም በከፍተኛ ደረጃ የሠለጠኑ ምሁራንን ሀኪሞች፣ ሳይንትስቶች፣የቴክኒክ ሰች ወዘተ በሀገሪቱ ወሳኝ ፖሊሲ ቀረፃና ትግበራች ላይ ከፖለቲካ ተፅዕኖ ውጭ ማሳተፍ፤ ለአገልግሎታቸውም ከሌሎች ከውጭ ሀገር ተቀጣሪ የሙያ ባልደረቦቻቸው ጋር የሚመጣጠን ክፍያ በመስጠት፣ ለኑሯቸው ምቹ ሁኔ□ መ□□ር::

**26.2** በሀገሪቱ በተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች የሥራ ዕድሎችን በማስፋፋት ዜጐች በጉልበታቸው ሠርተው ለኑሯቸው መተዳደሪያ የሚያገኙበትን ሁኔ□ች በመፍጠር ለአስከፊና አዋራጅ ስደት እንዳይዳረጉ መከላከል እና በስደት ላይ ሆነው መከራ የደረሰባቸውን ዜጐችንም መብትና ክብር በዓለም አቀፍ የስደተኞች ኮንቬንሺን መሠረት ማስከበር::

**26.3** በ□□ሩ የመሬት ጥበትና በሌሎች የኢኮኖሚ ቀውሶች ምክንያት ወደ ከተማ የሚፈልሰውን ወገን በተለይ ወጣቱን በ□□□ሩ ሰ□□ □እርሻ ልማቶችን በባለሀብቶች አማካይነትና እንደዚሁም በየከተማው (ከወረዳው አንስቶ ባሉት ሁሉ) የልማት ተቋማትን በመዘርጋት የሥራ ዕድል ፈጥሮ አምራች ዜጋ የሚሆንበትን ሁኔ□ መ□□ር::

## 27. ትምህርት

ኖ ትምህርትን በሚመለከት ያለው ችግር መጠነ ሰፊ ሆኖ፣ ተገቢነቱም ጭምር ጥያቄ እያስነሳ □□ኛል:: ከነዚህም ውስጥ አንደኛው በበቂ ጥናት ላይ ያልተመሰረቱ ፕሮግራሞችን ሥራ ላይ በማዃል እስከ 12ኛ ክፍል ሲሰጥ የነበረው የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ወደ አሥረኛ □□ል □ቅ መደረጉና የኮሌጅ ትምህርት ለመጀመሪ ዲግሪ በሦስት ዓመት እንዲጠናቀቅ መደረጉ በትምህርት ጥራት ላይ ብዙ ችግሮችን በማስከተል ላይ መሆኑ ነው:: ሌላው፣ የትምህርት አስተዳደር በሙያና በብቃት ላይ ተመስርቶ ሳይሆን በሹመት በሚሰየሙ ባብዛኛ□ □□□ □ □ርቲ ታማኝ

ካ□ሬች እንዲመራ መደረጉ በትምህርት ጥራት ላይ አሉታዊ ተጥዕኖ በማድረግ ላይ መሆኑ፣ ነው::

ኖ እንደዚሁም ተገቢው ስልጠና ያላቸው በቂ መምህራን በሌሉበት እና ለመማር ማስተማሩ ሂደት ተፈላጊ ቁሳዊና ነባራዊ ሁኔ□ች ባልተመቻቹበት፣ ኮሌጆችንና ዩኒቨርሲቲችን ለፖለቲካ □ቀሜታ ሲባል ካለዕቅድ በማስፋፋት ላይ ብቻ በማተኮር፣ ከተቋማቱ ይዘው የሚወጡትን □□ሎማም ሆነ ዲግሪ ደረጃ የማይመጥን ክህሎት ይዘው ወደ ሥራው ዓለም እንዲገቡ እየተደረገ መሆኑ ሀገሪቱን በእጅጉ እየጐዳት መሆኑንና ከእነዚህም መሃከል በየትምህርት እርከኑ በአስተማሪነት የሚሰማሩ መምህራን መሆናቸው፤ እንደዚሁም በትምህርት አሰጣጡ ሂደት በአጋዥነት ማገልገል ያለባቸው እንደ ፕላዝማ ቲቪ ያሉ ቴክኖሎጂች መምህሩን እንዲተካ እየተደረገ ያለው አሠራርና በሌሎችም ግድፈቶች ምክንያት ሀገሪቱን ለመገንባት ብቃት ያለው ትውልድ ለማፍራት በማያስችል ደረጃ የትምህረት ጥራቱ እየወረዳ መሆኑ እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ ሆኗል::

ኖ በተጨማሪም በሀገር ውስጥ በመንግሥት የሚሰጥም ሆነ በዓለም አቀፍ ዕርዳ□ ሰ□ ች የሚሰጡ ነፃ የትምህርት ዕድሎችን ተጠቃሚ የገኘው ፓርቲ አባላትና ደጋፊች እንዲሆኑ እየተደረገ መሆኑ ፣የትምህርት ዕድል ተጠቃሚነትም ለፓርቲ አባላት መመልመያ መሣሪያነት መዋሉ፣ በትምህርቱ ስርዓት ውስጥም አድሎአዊነት ሥር መስደዱን ያሳያል::

ኖ የመጀመሪያ ደረጃ የአንደኛ ዙር ትምህርት በየብሔር ብሔረሰቡ የአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲሰጥ የወጣው የትምህርት ቋንቋ ፖሊሲ በወጥነት ተግባር ላይ ያለመዋሉ፣ እንደዚሁም ፌዴራላዊ መንግሥት የሥራ ቋንቋ የሆነው አማርኛም ሆነ በዓለም አቀፍ ቋንቋነት ሥራ ላይ ያለው እንጊሊዘኛ እንደ አንድ ትምህርት በመንግሥትና በግል ት/ቤቶች በተመሳሳይ መልክ □ለመሰ□ታቸው፤ በሀገር ደረጃ የጋራ መግባቢያ ቋንቋ እያሳጣና በከፍተኛ ደረጃ የተመጣጠነ ትምህርት በመከታተል ረገድም ከፍተኛ ተ□እኖ እያሳደረ ይገኛል::

ኖ የጐልማሶች ትምህርት ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶት እየተካሄደ ያለመሆኑ፣መሀይምነትን ከሀገሪቱ ለማጥፋትና የሙያ ክህሎት ለሰፊው አርሶ አደሩና ሠራተኛ□ ለማ□ረስ □ርም□ እየተወሰደ ያለመሆኑ፣ በዚህ ረገድ ሀገራችንን ብዙ እርምጃች ወደኋላ እየመለሳት ይገኛል::

ኖ የትምህርት ወጪን በሚመለከት የዩኒቨርስቲ ትምህርት በመንግሥትና በተማሪች ዋጋን በመጋራት እየተከናወነ መሆኑ፣ ምሩቃኑ ሥራ የማግኘት ዕድላቸው በጠበበት በአሁኑ ሁኔ□ ዕዳውን ለመክፈል ያለመቻላቸው ለሌሎች ዕድሎች በር እየተዘጋባቸው መሆኑ፣ ከከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሚመረቁ ወጣቶች ትልቅ የኑሮ ቀውስ እየፈጠረባቸው መሆኑ አሳሳቢ ሆኗል::

ኖ የግል የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ተቋማት ያለበቂ ቁጥጥርና ክትትል እየተስፋፉ ደረጃውን □□በቀ □ተማሪች ቅበላ (ሮሳቂሽቋቋሽቂቃ) መስፈርቶች ወጥነት ባለመከተል ትምህርት የሚሰጡበት ሁኔታ ሰፍኖ መገኘቱ፣ በሀገሪቱ የተማረ ሰው ሀይል ጥራት ላይ አፍራሽ ተፅዕኖ የሚያሳድር ከመሆኑም በላይ የተጠቃሚውን ዜጐች ጥቅም የሚጐዳ ሆኖ ይገኛል::

ኖ በመላው የሀገሪቱ የትምህርት ሥርዓት ውስጥ በሲቪክስ አማካኝቶ የገዥውን ፓርቲ የፖለቲካ አይዲኦሎጂ የማስፋፋቱ ተግባር፣ ት/ቤቶችን ነፃ የዕውቀት ማስፋፍያ ማዕከላት እንዳይሆኑ እያደረጋቸው ከመሆኑ በተጨማሪ በየትምህርት ተቋማቱ ነፃ የተማሪችና የመምህራን ማህበራት እንዳይንቀሳቀሱ ተፅዕኖ መደረጉና የአካዳሚክ ነፃነት እንዳይኖር የገዥው ፓርቲ ጣልቃ ገብነት ጐልቶ መታየት፣ ነፃ የመማር ማስተማር ስርዓቱ እንዳይጐለብት (እንዳይዳብር) በማድረግ ሁኔታውን በእጅጉ የከፋ አድርጐታል::

ስለሆነም የትምህርትን ሥርዓት ለማሻሻል የሚከተሉት የመፍትሔ □ርም□ች ይወሰዳሉ፣

*27.1 □2ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያን እስከ 12ኛ ክፍል ድረስ ከፍ ማድረግና የመጀመሪያ ዲግሪ የዩኒቬርስቲ ትምህርት ቢያንስ በ4 ዓመት እንዲጠናቀቅ ማድረግና የትምህርት አስተዳደር ሃላፊነት የሚያዘውም የሙያ ብቃትና የሥራ ልምድን ባገናዘበ መልኩ ተወዳድሮ በማሸነፍ እንዲሆን ማድረግ::*
*27.2 የከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን ከታችኛ□ እስከ ላይኛው ዕርከን ድረስ ደረጃ በደረጃ እያደራጁና የሰው ሀይሉንም በማሰልጠን ብቃትና ልምድ እንዲያገኝ ጊዜ በመስጠት፣ የስልጠና መርሃ ግብሮችንም ደረጃ በደረጃ □□ሳ□□ በመሄ□፣ □ለም አቀፍ ደረጃን የጠበቀ ስልጠና እና ክህሎት የሚሰጡ ተቋማት እንዲሆኑ ከመገንባት በተጨማሪ፣ የሀገር ውስጥም ሆነ የውጭ ከፍተኛ ደረጃ ትምህርትና ስልጠና ዕድሎችን በግልጽ ውድድር፣ ከፖለቲካ ነፃ በሆነ መልኩ ለዜጐች ክፍት እንዲሆኑ ማድረግ:: የፓርቲ አባላትን ለመጥቀም ተብሎ የመግቢያ ነጥብ አወሳሰን ማዛባት ተገቢ አይደለም፤ ሕገ ወጥም ነው:: በተለይ ለማስተርስና ዶክተሬት ዲግሪዎች የሚመለመሉ ሰዎች በውጤታቸው መሆን ይገባዋል:: ለፓርቲ አባላት የሚደረግ የተለየ የመግቢያ ነጥብም ሆነ አስተያየት እንዲቀር ይደረጋል:: በከፍተኛ ትምህርት ተቋማትና ከዚያም ውጭ ምርምርና ጥናት በተለያዩ የሀገሪቱ ችግሮች ላይ እንዲካሄዱ በቂ ድጋፍ መስጠት::*

27.3 የሕብረተሰቡና የተማሪው ፈላጎት በውል ሳይጤንና አሰፈላጊው ቅድመ ዝግጅት ሳይደረግ ወደ ዩኒቨርስቲ የሚገቡ ተማሪዎች 70 ከመቶ በተፈጥሮ ሳይንስ 30 ከመቶው ደግሞ በማሕበራዊ ሳይንስ እንዲደለደሉ የሚያደርገው ፖሊሲ ቀርቶ የሕብረተሰቡንና የተማሪውን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ድልድል እንዲኖር ይደረጋል::

27.4. አስፈላጊ ቅድመ-ሁንታዎች ባልተመቻቹበት ሁኔታ በአንደኛ ደረጃ መጀመሪያ ሳይከል እየተሰጠ ያለው አሃዳዊ የትምህርት አሰጣጥ (self-contained class) በትምህርት ጥራት ላይ ከፍተኛ አሉታዊ ተጽእኖ እያሳደረ በመሆኑ እንዲቀር ይደረጋል::

*27.5 የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ዙር የትምህርት ቋንቋ አጠቃቀም ፖሊሲን በመላው ሀገር ወጥነት እንዲኖረው ማድረግ:: የአማርኛና ሌላም በፌዴራል የሥራ ቋንቋነት እንዲያገለግል የሚመረጥ ቋንቋ በመንገሥት ትምህርት ቤቶች እንዲሰጡ መንግሥት ለሰፊሳጊውን ሁሉ ያደርጋል□ ተማሪዎች ከነዚህ የሥራ ቋንቋዎች የመረጡትን ወይም ሁለቱንም ይወስዳሉ:: እነዚህ ቋንቋዎች የእንግሊዝኛን ትምህርት ጨምሮ በመንግሥትና በግል ት/ቤቶች በመላው ሀገሪቱ በአንድ አይነት በወጥነት እንዲሰጡ ማድረግ::: ሌሎችን የየብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቋንቋች ቋንቋው በሚነገርባቸው በየአስተዳደር ዕርከኑ በትምህርትነት የሚሰጡበትን ሁኔ□ ማመቻቸት፤ ቋንቋ-ቹንም በትምህርት መስጫነትና ለሥራ መጠቀም ለሚፈለረጉ አስተዳደሮችም ተገቢውን ድጋፍ መስጠት::*

*27.6 ከሀገር መሃይምነትን ለማጥፋትና ተግባራዊ የሙያ ክህሎትን በሰፊው አርሶ አደሩና ሠራተኛው ውስጥ ለማስፋፋት መጠነ ሰፊ የሆነ ሀገር አቀፍ የጐልማሶች ማሠልጠኛ ትምህርት መርሃ ግብር ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ::*

*27.7 እስከ 12ኛ ክፍል የሚሰጠው ትምህረት (መደበኛና የሙያ) ነፃ ሆኖ የመቀጠል ሁኔ□ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከ12ኛ ክፍል በላይ የሚሰጡ የቴክኒክና ሙያ ስልጠናችም ነፃ ይሆናሉ:: የዩኒቨርስቲ ትምህርት ወጭ በመንግሥትና በተማሪው በወጭ መጋራት ስልት የሚካሄድ ሆኖ ምሩቃኑ ሥራ ይዘው የትምህረት ብድሩን ለመክፈል ሁኔታው እስካላበቃቸው ድረስ ግን ብድሩን ያለመክፈላቸው ለቀጣይ የሥልጠና እና ሌሎች  እድሎች በር እንዳይዘጋባቸው ማድረግ::*

*27.8 የግል ትምህርት ተቋማት (መደበኛና ከፍተኛ) የትምህርት ጥራታቸው ደረጃን የጠበቀ እንዲሆን አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል በማድረግ ተቋማቱ ትውልድን በዕውቀት የማነጽ ሃላፊነትን እንዲወጡ ማገዝ::*

*26.9 የሲቪክስ ትምህርት የሙያ ብቃት ባላቸው መምህራን ከፖለቲካ ነፃ በሆነ አግባብ እንዲሰጥ ማድረግ:: እንደዚሁም የተማሪና የመምህራን ማህበራት በየተቋማቱም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ በነፃነት ተቋቁመው እንዲንቀሳቀሱ ሁኔታችን ማመቻቸት፣ በየትምህርት ተቋማቱም የአካዳሚክ ነፃነት መከበሩን ማረ□□ጓ ::*

## *28. <u>የጤና አገልግሎት</u>*

*የሀገራችን የጤና አገልግሎት ያለበት  ችግር ፈርጀ ብዙ ነው:: ከጉድለቶቹ ዋነኛ□ ፡ በሽታን በመከላከል መርህ ላይ የተመሠረተው የሀገሪቱ የጤና ፖሊሲ በሀገር አቀፍ ደረጃ በተደራጀና*

ሁሉን ክልሎች በሸፈነ መልክ እየተከናወነ ያለመሆኑ ሲሆን፣ ክንውኖቹ ይካሄዳሉ በሚባልባቸው ክልሎችም ቢሆን ለእቅዱ ማስፈጸሚያ መጠኑም ከፍተኛ □ሆነ ከውጭ ለጋሽ አገሮችና ድርጅቶች የሚገኘውን፣ የገንዘብ እርዳታ በመጠቀም የተወሰኑ የመከላከል እርምጃችን በተወሰኑ በሽ□ች ላይ ብቻ ከመውሰድ አልፎ በቀጣይነት ብቃትና ጥራት ያላቸው አገልግሎቶች ስለማይሰጡ ሰፊው ሕዝብ ለከፍተኛ የጤና ጉድለት ተዳርጐ ይገኛል። እንደዚሁም በሽታን ከመከላከል ስልቶች በተጨማሪ አክሞ ለማዳን (ሰቁሽቃሽሰሮቁ ሰሮቈስ) አገልግሎትም ተገቢው ትኩረት መስጠት ሲገባው በቂ የሙያ ብቃት በሌላቸው ሠራተኞችና በቂ የህክምና መገልገያች በሌላቸው ሆስፒታሎች፣ የጤና ጣቢያችና የጤና ኬላች ደረጃውን ሳይጠብቅ ሕ□ቡ እንዲገለገልባቸው የተያዘው ዕቅድ ለከፍተኛ የጤና ጉዳት ሕዝቡን □□□ለ□□ □□ኛል።

በከተማቹ እየተስፋፉ ያሉት የግል ሕክምና መስጫ አገልግሎቶች ብቃትና ጥራታቸው በቂ ክትትልና ቁጥጥር ካለመደረጉም በላይ የአገልግሎቶቹ ክፍያ ከዜጐች የመክፈል ዐቅም ጋር የማይመጣጠንበት ደረጃ ላይ መድረሱና በተለይም የመድሃነቶች ዋጋ እጅግ እየናረ መሆኑ ሰፊውን ሕዝብ ዘመናዊ ህክምና ጠቃሚ የመሆኑን ዕድል □□ራቀ□ □□ኛል። ይህንንም ሁኔ□ ከሚከፈላቸው ደመወዝ ማነስና የሥራ አካባቢ ያለመመቻቸት የተነሳ የጤና ባለሙያች ፍልሰት እየሰፋ መሄዱ እጅግ የከፋ እያደረገው ይገኛል። በተፊ ማሪም የዘመናዊ ህክምና ለሠ□□ ሕዝብ ተደራሽነት ሁኔታ ከፍተኛ ችግር ላይ ወድቆ በሚገኝበት በአሁኑ ወቅት በሀገራችን ብዛት ያለው ሕዝብ የሚጠቀምባቸው ባህላዊ መድሃኒቶችና የህክምና ዘዴች በበቂ ምርምርና ጥናት እየተደገፉ ጥቅም ላይ ያለመዋላቸው፣ የጤና አገልግሎቶች ሥርዓቱ አንዱ ጉድለት ነው። ከዚህም በተጨማሪ በጤና አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ተንሰራፍቶ የሚገኘውን የሥነ-ምግባር ጉድለት ለማስቀረት ጐልቶ የሚታይ እርምጃ በመንግሥት እየተወሰደ ያለመሆኑም እጅግ አሳሳቢና የዜችን ሰብዓዊ መብትና ክብር እየጐዳ ያለ አሳፋሪ ጉዳይ ነው።

ስለሆነም ከፍ ብለው የተጠቀሱትንና ሌሎች ተዛማጅ የጤና አገልግሎቶች ጉድለቶች ለማሻሻል የሚከተሉትን □ርም□ች እንወስዳለን፣

28.1 ተከታታይነት ያላቸው በሽታን የመከላከልና የቁጥጥር ተግባራትን በሁሉም የሀ□ሪቱ ክልሎች ማከናወንና ከዚሁ ጋር በተጓዳኝነት ለአክሞ የማዳን (ሰቁሽቃሽሰሮቁ ሰሮቈስ) አገልግሎት በቂ ትኩረት በመስጠት በመንግሥት ይዞታ ሥር ያሉትን የጤና ተቋማት ብቃት ባለው፣ የባለሙያ፣ የጤና መገልገያ መሣሪያችና መድሃኒት አቅርቦት ማደራጀት። አካባቢን ጤናን ጐጂ ከሆኑ ብክለቶች መጠበቅ፤ የአካባቢው ንፅህናን በሀገሪቱ በከተማም ሆነ በገጠሩ ማስፋፋት፤ ንፁህ የመጠጥ ውሃን ለመላው ሕዝብ ለማዳረስ ቅድሚያ ሰጥቶ መንቀሳቀስና □□ሃ □ለ□ በሽ□ችን መከላከል።

**28.2** በየከተማው □□ተስ□□ ያሉትን አክሞ የማዳን (ሰቁሽቃሽሰሮቁ ሰሮቁስ) የግል ተቋማትን ብቃት፣ ጥራትና የአገልግሎት ክፍያቹም በሕዝቡ የመክፈል አቅም ክልል ውስጥ እንዲሆን ክትትል፣ ቁጥጥርና ድጋፍ ከመስጠት በተጨማሪ ለመድሃኒት ዋጋ ልዩ ድጐማ ከመንግሥት □□□ ማ□ረፅ ። እንዲሁም ሀኪሞችና ሌሎች የጤና ባለሙያች ለሚያበረክቱት አገልግሎት የሚመጥን ክፍያችን መስጠትና ለሥራቸው አመቺ ሁኔ□ችን መፍጠር።

28.3 በኤች አይ ቪ/ኤይድስ የሚደርሰው ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግር አገሪቱ ካሉባት ችግሮች መካከል አንዱ ነው፤ በመሆኑም ይህን በሽታ ለመግታት ተገቢ የትምህርትና የመከላከያ እርምጃዎች ይወሰዳሉ። እንዲሁም በከፍተኛ ደረጃ ሞትን በሚያስከተሉ እንደ ወባና የሳንባ ነቀርሳ በመሳሰሉ ተላላፊ በሽታዎች ላይ ሰፊ የመከላከል ሥራዎች እናካሂዳለን።

**28.4** በስፋት በሚጠቀምባቸው ባህላዊ መድሃኒቶችና የህክምና ዘዴች ላይ ጥናትና መርምር በማድረግ የአጠቃቀሙን ደረጃ የማሻሻል □ርም□ችን በመውሰድ አጠቃላዩን የጤና አገልግሎት ሁኔታ ለሰፊው ሕዝብ በተሻለ ሁኔታ ተደራሽ ማድረግ።

**28.5** የጤና አገልግሎቶች የሙያው ስነ ምግባር በሚያዘው መሠረት ስለመከናወናቸው □ማረ□□ □ርም□ች መውሰድና የስነ ምግባር ጥሰቶች ሲከሰቱም ሕጋዊ ተጠያቂነት የሚኖርበትን ስርዓት መዘርጋት።

## 29. ማህበራዊ ዋስትና

ኖ ማህበራዊ ዋስትናን ለሕዝባችን በማረጋገጥ ረገድ የለው ችግር በስርዓቱ የተሳሳተ ፖሊሲና አስተዳደራዊ ድክምነት ምክንያት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ በመሄድ ላይ ይገኛል። ለ□ህም ምክንቶቹ ፈርጀ ብዙ ቢሆኑም፣ዋነኛው ግን ስልጣን ላይ ያለው መንግሥት የማህበራዊ ዋስትና ችግሮችን ለማርገብ ለሚያስችሉ የፖሊሲና የአፈጻጸም □ርም□ች ትኩረት ሳይሰጣቸው መቅረትና፣ ይባስ ብሎም ራሱ የችግሩ ፈጣሪና አወሳሳቢ መሆኑ ነው። በዚህም ረገድ ተጠቃሽ የሚሆነው በየመሥሪያ ቤቱ የተቀጠሩ ሠራተኞችን ከሥራ የመቀነስና ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ ከሥራ የማባረር ሂደቶችን ሥራዬ ብሎ አንድ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በማቋቋም፣ በተለይም በመንግሥት ሠራተኛ□ ላ□ እየዘመተ መሆኑና ከሥራ ካሰናበተም በኋላ የማህበራዊ ዋስትናው አካል የሆኑትን ክፍያች (ጡረታና የአገልግሎት ካሣ) በወቅቱ የማይፈጸሙ መሆናቸው ነው። ይህንን የዜጐችን ሕገ-መንግሥታዊ መብቶች የጣሰ □ርም□ ሕ□ቡ እንዳይከላከል ነፃ የሠራተኛ ማህበራትና የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅቶች በነፃነት ተደራጅተው እንዳይንቀሳቀሱ ክቀባ □□ረ□ አምባ ገነናዊ ሥርዓት መስፈኑ ማህበራዊ ዋስትናን ለማረጋገጥ ታላቅ ደንቃራ ሆኖ ይገኛል።

ኖ በሴተኛ አዳሪነትና በልመና የተሰማሩ ዜጐች በተደራጀ መልክ የሚረዱበትና የሚቋቋሙበት አሠራር አለመዘርጋቱና የአካል ጉዳተኞች የሚረዱበት፣ በሞትና በሞርኮ የሚለዩ የሀገር መከላከያ ሠራዊት አባላት ቤተሰቦች በዘላቂነት የሚደጉሙበት፣ የማህበራዊ ዋስትና ሥርዓት ያለመኖር፣ ሌላው ጉልቶ የሚታይ ዜጐች የተጋለጡበት ችግር ነው።

ስለሆነም የማህበራዊ ዋስትና ችግሮችን ለመቆጣጠርና ለማርገብ የሚከተሉት □ርም□ች □□ሰ□ሉ፣

**29.1** በሀገራችን ባለው ኋላቀር ኤኮኖሚያዊ ነባራዊ ሁኔታ ማህበራዊ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚቻለው፣ ጉዳዩ በህብረተሰብና በመንግሥት ተገቢውን ትኩረት አግኝቶ፣ ሁሉም የሀገሪቱ ዜጐች ሀገሪቱ ካላት ሀብት መሠረ□ዊ ለሆኑ የምግብ፣ የመጠለያ፣ የልብስ፣ የጤና ወዘተ አገልግሎቶች የሚሆኑ ድጋፎች እንዲያገኙ□□ረ□ል::

**29.2** ከሥራቸው የሚፈናቀሉም ሆነ ዕድሜያቸው ለጡረ□ ሳይደርስ በተለያዩ ምክንያቶች ከሥራ የሚሰናበቱ ዜጐች ከሰጡት አገልግሎቶች ጋር የሚመጣጠን ክፍያ (የጡረ□፣ የአገልግሎት ካሣ) ወዲያውኑ እንዲያገኙ □□ረ□ል::

29.3 በተፈጥሮም ሆነ በሌሎች አደጋች የአካል ጉዳተኝነት ለደረሰባቸው ወገኖች በአምራች ዜግነት ራሳቸውን የሚያስተዳድሩበት ሁኔ□ችን ማመቻቸትና ለኑሯቸው በቂ የሆነ ድጐማችን በሁለንተናዊ መልኩ መሥጠት::

29.4 ለጡረተኞች የሚከፈለው አበል በየወቅቱ የሚከሰተውን የዋጋ ንረትና የኑሮ ውድነት በማገናዘብ እንዲስተካከል ይደረጋል::

**29.5** የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋችን ለመከላከልና ጉዳት የደረሰባቸውን ተጐጂች ለመርዳት ከሀገር ውስጥም ሆነ ከውጭ ዕርዳ□ችን ለማስተባበር የሚችል ተቋም ሃላፊነት ተሰጥቶት እንዲሠራ ማድረግ::

**29.6** ሠራተኛው መብቱንና ጥቅሞቹን የሚያስከብርባቸው ነፃ መህበራት እንዲኖሩ ማ□ረፅ፤ እንደዚሁም ሲቪክ ማህበረሰቦችና ሌሎች መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በነፃነት ተደራጅተው እንዲንቀሳቀሱ ሁኔታችን ማመቻቸት::

## 30. ሴቶችን በተመለከተ

-ሴቶች በረጅም የታሪክ ሂዴት በደረሳቸው ጭቆናና አድሎኦ የተነሣ በሁሉም የሕብረተሰብ መስኮች እኩል ተሳታፊና ተጠቀሚ ያልሆኑ መሆናቸውን በመገንዘብ
-ይህን ሁኔታቸውን ባገናዘበ መልኩ ለችግሮቻቸው መፍትሄ በመስጠት ፈንታ ለፖለቲካ ፍጆታ ሲባል ከፍላጎታቸው ውጭ በማሕበራት እንዲደራጁና በካባድ ሥራዎች እንዲጠመዱ ጫና በማድረግ በኑራቸውና በአጠቃላይ ዕደገታቸው ተጽኖ እየደረሰባቸው መሆኑ በማመን፣ የሚከተሉትን የመፍትሄ ሐሳቦች ተግባራዊ እናደረጋለን::

30.1 ሴቶች ከወንዶች እኩል ሀብትን የማፍራት፣ የንብረት ባለቤት መሆንንና የመውረስ መብት ይኖራቸዋል።

30.2 ሴቶች ከወንዶች እኩል ሥራ የማግኘት ዕድል እንዲኖራቸው ይደረጋል፤ በፆታቸው ምክንያት ልዩነት አይደረግም።

30.3 ሴት ሠራተኞች በእርግዝናና በወሊድ ወቅት መብታቸው ተጠብቆ በቂ ዕረፍት የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል።
29.4 ብቸኛ እናቶች (single mothers) የሚያጋጥሟቸውን ችግር ለማቃለል ይቻል ዘንድ ልዩ ድጋፍ ይደረጋል።

30.5 የሴቶች እኩልነትና መብት በማጎልበት ረገድ ጠቃሚ የሆኑ እንደ ትምህርት ሥልጠናና በሥፋት በመሰጠት ዓቅም የሚገነቡበትን ሁኔታ ልዩ ትኩረት ይሰጠዋል።

30.6 በተለያዩ እምነቶችና ባህሎች በሴቶች ላይ የሚደርሱባቸውን ስነልቦናዊና አካላዊ ጉዳቶች ለማስወገድ ይቻል ዘንድ አስፈላጊውን ሁሉ ይደረጋል፤ በተለይ በአጉል ባህሎችና እምነቶች የተነሳ በሴት ልጆች ላይ የሚደርሱትን ያለዕድሜ ጋብቻና ግርዛትን የመሳሰሉ እጥባቀን እንቃወማለን።

30.7 የሴቶች ማሕበራትንና ድርጅቶችን በገዥው ፓርቲ ወይንም በመንግስት ቁጥጥር ሥር ለማሰገባት የሚደረገው ጥረት ፈርጀ ብዙ ትግላቸውን የሚያኮላሽና ተነሳሽነታቸውን የሚገድል ሰለሆነ ሴቶች ችግሮቻቸውን ይፈቱ ዘንድ ከመንግስትና ከፖለቲካ ድርጅቶች ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆነው እንዲደራጁ ይደረጋል።

30.8 ሴቶች በሁሉም ሕብረተሰባዊ እንቅስቃሴዎች የሚኖራቸው ተሳትፎ ይጣናከር ዘንድ በፖለቲካው መስክ የቁጥርና የይስሙላ ብቻ ሳይሆን እውነተኛ የመወሰን ሥልጣን እንዲኖራቸው ይደረጋል።

**31. ወጣቶችን በተመለከ**

-የአገራችን ወጣቶች ከቀን ወደ ቀን እየተባባሰ የመጣውን ሥራ-አጥነት፣ አጉል ሱሶችና የኑሮ ችግር ሰለባ እየሆኑ መሆናቸውን በማስተዋል

- ወጣቶች የሥራ ዕድል የሚያገኙት በትምህርት ውጤታቸው፣ በሙያቸውና በዕውቀታቸው ሳይሆን በገዥው ፓርቲና ገዢው ፓርቲ በሚያደራጃቸው ማሕበራት ሲደራጁ ብቻ መሆኑ ኢ-ፍትሃዊና አግባብነት የሌለው መሆኑን በመገነዘብ

- ወጣቶች በነጻ ተደራጅተው ችግሮቻቸውን እንዳይፈቱ ገደብና ጫና እየተደረገባቸው መሆኑን በማስተዋል

31.1 በአሁኑ ጊዜ ወጣቶችን የሚያጋጥሟቸው ከፍተኛ የሥራ አጥነት ችግሮች ለመቋቋም ዘርፈ ብዙ መርሀ ግብሮችንና ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ መፍትሔ እንዲያገኙ እንጥራለን።

31.2 ወጣቶች የመንግሥት ሥራን የሚያገኙት በትምህርት ውጤታቸው፣ በሙያዊ ብቃታቸውና በክህሎታቸው ተወዳዳሪ ሆነው ሲገኙ ብቻ እንጂ በፓርቲ ወይም በማሕበር አባልነታቸው እንደማይሆን ይደረጋል፡፡
31.3 ወጣቶች የገዥው ፓርቲ ወይም ከገዥው ፓርቲ ጋር ቁርኝት ያላቸው ማሕበራት አባላት ባለመሆናቸው ብቻ የሚደርስባቸው የሥራና የአገልግሎት አድሎን እናስቀራለን፡፡
31.4 ወጣቶች የተለያዩ አጉል ሱሶች ሰላባ እንዳይሆኑ ብርቱ ጥረት ይደረጋል፤ ለዚህ ሲባልም ወጣቶችን በአእምሮና በአካል እንዲዳብሩ የሚያገለግሉ የመዝናኛ፣ የስፖርትና ዕውቀት ማእከላት እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡
31.5 መላ ወጣቶችን በገዥው ፓርቲ ቁጥጥር ሥር ለማዋል የሚደረጉትን አደረጃጀቶችን በመቃወም ወጣቶች በፍፁም ነፃነት ተደራጅተው የጋራ ችግሮቻቸውን የሚፈቱበትንና በአገራቸው ጉዳይ ተዋንያን የሚሆኑበትን ሁኔታ እንፈጥራለን፡፡

## 32.አካል ጉዳተኞችን በተመለከት

-በአገራችን በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ በሆኑ የጦርነት አደጋዎች ምክንያት በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ዜጎች ለአካል ጉዳተኝነት የተዳረጉ መሆናቸውን በማጤን

-እነዚህ ወገኖቻችን ላሉባቸው የተለዩ ችግሮች የተለዩ መፍትሄዎች እንደሚሹ በማመን

32.1 አካል ጉዳተኞች በአካል ጉዳተኝነታቸው ምክንያት የሥራ ዕድል በማግኘት ረገድ ልዩነት አይደረግባቸውም፤ ዓቀማቸው በፈቀደው መጠን ከሌላው ዜጋ እኩል ሠርተው የሚኖሩበት ሁኔታ እንዲመቻች ይደረጋል፡፡
32.2 የመኖሪያ አካባቢዎች፣ የሥራ ቦታዎች፣ መንገዶች፣ አደባባዮችና ማጓጓዣዎች በሚቀየሱበትና በሚሠሩበት ወቅት የአካል ጉዳቶኞችን ችግሮች ባገናዘቡ መልኮች እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡
32.3 አካል ጉዳተኞች ችግሮቻቸውን ያገናዘቡ የተለያዩ ልዩ የትምህርትና የሙያ ሥልጣናዎች እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡
32.4 በትምህርት በሚሰማሩበት ወቅት የሚያጋጥሟችውን የተለያዩ የቁሳቁስና ልዩ የትምህርት መሳሪያዎች እጦቶች እንዲቃለሉ ጥረት ይደረጋል፡፡

## 33. አረጋውያንና ህጻናትን በተመለከተ

33.1 ጧሪ ያጡ አረጋዊያን በመንግስትና በተለያዩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አማካኝነት እንክብካቤ እንዲደረግላቸው ትኩረት ይሰጠዋል ፡፡

33.2 አረጋዊያን ጊዚያቸውን የሚሳሉፉባቸው ማእከላት እንዲስፋፉ ይደረጋል ፡፡

33.3 አረጋውያን ለተተኪው ተውልደ ልምዳቸውን የሚያስተላልፉበት ሁኔታ ይመቻቻል ፡፡

33.4 የአገሪቱ የወደፊት ተስፋ የሆኑት ህጻናት ስነ- ምግባራቸውና ጤንነታቸው ተጠብቆ ያድጉ ዘንድ ልዩ ትኩረት ሰጥተን እንሠራለን ፡፡

33.5 ወላጅ አለባ የሆኑ ህጻናት በእንክብካቤ ያድጉ ዘንድ ልዩ ልዩ ስልቶችን ነድፈን እንንቀሳቀሳለን ፡፡

## 34. ስነ ሕዝብን በተመለከተ

ስነ ሕዝብ ለአንድ አገር የማሕበራዊና ኢኮኖሚዊ ዕድገትና እንቅስቃሴ ትላቅ ቦታ ያለው ነው የኢኮኖሚ ዕድገትና የሕዝብ ዕድገት መመጣጠን ይገባዋል ፡፡ በመሆኑም የእናቶች የቤተሰብ ምጣኔና የወሊድ መቆጣጠርያ አገልግሎት ፕሮግራም ተጠናክሮ ሥራ ላይ እንዲውል ይደረጋል ፡፡

## 35. ቅርሶችና ብሄራዊ ፓርኮችን በተመለከተ

አገራችን የበርካታ ጥንታዊ ቅርሶችና መስህቦች ባለቤት ናት፡፡ እንዲሁም የበርካታ ብርቀየ እንስሳት መጠለያ የሆኑ ፓርኮች ባለቤት ናት ፡፡ ሆኖም እነዚህ ሀብቶቻችን ተንከባካቢ በማጣት ለዝርፍያ፣ ለብክነትና ለውድመት ታጋልጠው ይገኛሉ ፡፡

መድረክ እነዚህን መተኪያ የሌላቸው ብሄራዊ ሀብቶቻችን ተገቢ እንክብካቤ፣ ጥበቃና ትኩረት እንዲያገኙ በከፍተኛ ደረጃ ይንቀሳቀሳል፡፡